በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት

የፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች

የ2015/16 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት

የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

ጥራዝ 1

ሰኔ / 2016

አዲስ አበባ

ማውጫ ገጽ

1. መግቢያ 1

2. ኦዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report/ 5

3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በዘርፍ የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት 36

3.1 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት 36

3.2 ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት 67

3.3 በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት 78

3.4 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የተጠቃለለ ሪፖርት 132

3.5 የልማትና ማህበራዊ የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት 162

3.6 የንግድ እና አስተዳደር መ/ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት 183

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

1. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 (አዋጅ ቁጥር 1146/2011 እንደተሻሻለው) የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ እገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

በማቋቋሚያ አዋጁ የተሰጡትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ስርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመ/ቤታቸውን ሂሳብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገልጹለት ሊያድረግ ይችላል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር እንዳስፈላጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ይሰጣል፤

- አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ፤ ይህን ሂሳብ የሚመለከቱ ጽሑፎች፤ መዘክሮች፤ መዝገቦች ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ላይ ያሽጋል፤
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለገንዘብ አያያዝ፤ አጠባበቅ፤ የሂሳብ አያያዝና ንብረት አስተዳደር በሚያዘጋጀው መመሪያዎች ላይ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፤
- ከሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ጋር የፌዴራልና ክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤
- የፌዴራል መንግስት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ እና ልዩ ድጎማዎችን ኦዲት ያደርጋል፡ ያስደርጋል።
- ከክልል የኦዲት መ/ቤቶች እና ቁጥጥር ቢሮዎች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የስራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል።

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በ6 የኦዲት ዳይሬክቶሬቶች የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፣ የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች፣ የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች እና የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ስራዎች ተከናውኗል፡፡ እራሱን ችሎ በተቋቋመ አንድ የልዩ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ደግሞ ከሚመለከታቸው አካላት በሚቀርቡ ጥቆማዎችና በመ/ቤታችን በልዩ ኦዲት እንዲታዩ የታቀዱ ኦዲቶች ሪፖርትም ተካቷል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት የስጋት ደረጃ እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፣ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም ስጋትን ያማከለ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት **(Exit Conference)** ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መንግስት መ/ቤት እየተላከ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን ምላሽና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡

በ2015 በጀት አመት በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ ስድስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፣ የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት እና በ1 የልዩ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በአጠቃላይ በ8 ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ ከየካቲት/2015 እስከ ጥር 30/2016 ድረስ በ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 173 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 162 መ/ቤቶችን እና 58 ቅርንጫፎች በመስሪያ ቤታችን፤ የተቀሩትን 11ዱን ደግሞ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማስቀጠል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 4 መ/ቤቶች በጸጥታ ምክንያት ኦዲታቸው ያልተጀመረ፤ 1 መ/ቤት የቢሮ እድሳት ላይ ነኝ በማለት ለኦዲተሮች ቢሮ ባለማቅረቡ፣ 7 መ/ቤቶች እና 4 ቅርንጫፎች ስራው ተጀምሮ በጸጥታ ምክንያት ኦዲቱ የተቋረጠ ሲሆን አፈጻጸሙም የ151 መ/ቤቶች አንድ የተጠቃለለ የመንግስት ሂሳብ እና 54 ቅርንጫፎች ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርቱ ወጪ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም ከአጠቃላይ የመንግሰት ሂሳብ ኦዲትን ጨምሮ 94.44% ሆኗል፡፡

2. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 37 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

1. **የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች**

   የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

   ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ2 መ/ቤቶች ብር 383,238.48 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 2/1 ተመልክቷል/

   በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

   - የገንዘብ ሚኒስቴር ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ከብር 5,000.00 ብር በላይ የሆኑ ወጪዎች መከፈል ያለባቸው በቼክ/ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመጠቀም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 149,846,00 በቼክ/ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመጠቀም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ መፈጸም ሲገባቸው በግዥ ሰራተኞች ሥም ቼክ እየተዘጋጀ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ አባሪ 2/1 ሀ ተመልክቷል፡፡

   - በቤተመንግሥት አስተዳደር በድምሩ ብር 190,579.77 በካዝና ከተፈቀደው በላይ ተቀምጦ ተገኝቷል ፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 2/1 ለ ተመልክቷል)

- የቤተ-መንግስት አስተዳደር በድምር ብር 642,587.41 የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይሆን መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 2/1 ሐ ተመልክቷል)

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የፌደራል መንግስት የሂሰብ አያያዝ መመሪያ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ማለትም በሰኔ 30/2015 በጀት ዓመት እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

  መደበኛ ሚዛኑን ያልጠበቀ **የተጣራ ሀብት** ክሬዲት መያዝ ሲገባው በሂሳብ ሪፖርት ላይ በዴቢት ተመዝግቦ የሚታይበት በገቢዎች ሚኒስቴር ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 80,702,549.07 ስለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 2/2 ተመልክቷል)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ረጅም ዓመታት ፈሰስ ሳይደረግ በባንክ ውስጥ የተጠራቀመ የገቢ ሂሳብ ምክንያቱ የማይታወቅ ብር 110,444.01 የሚታይ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 2/2 ለ ተመልክቷል)

በ1 መ/ቤት በድምር 226,243.88 የፕሮጀክት ስራቸው ተጠናቆ የባንክ ሂሳባቸው ያልተዘጋ የፕሮጀክት ባንክ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በአንድ ሌላ መ/ቤት ደግሞ በግንባታ ሂሳብ ላይ ጥሬ ገንዘብ የምዝገባ ስህተት በብልጫ የተመዘገበ ብር 13,401,497.56፣ ያልተከፈለ ጥሬ ገንዘብ ብር 2,807,684.81 እና የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት የግሬስ ፔሬድ ሂሳብ ብር 4,185,776.49 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 2/3 ሀ እና ለ ተመልክቷል)

መ/ቤቶች መንግሥት የዘረጋውን የክፍያ ሥርዓት እንዲተገብሩ እንዲሁም የገንዘብ ዝውውሩን ለመቆጣጠር መንግስት ያወጣው መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው፣ እንቅስቃሴ የሌላቸው የፕሮጀክት ሂሳቦች በሌጀር ሚዛን ላይ የሚታዩ ቋሚ ሂሳቦች ማለትም የሳጥንና የባንክ የጥሬ ገንዘብ ሂሳቦች ሚዛናቸውንና ትክክለኛነታቸውን በተገቢው መንገድ በማጣራት በተደረሰው

ውጤት መሰረት እና በፕሮጀክቶቹ የውል ስምምነት መሰረት ሂሳቡ በትክክል ተዘግቶ ሪፖርት መደረግ እንዳለበትና ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በ124 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 14,119,173,104.23 በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	34,932,377.61
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	1,100,725,598.39
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	1,992,899,328.99
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	2,410,782,443.36
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	8,171,141,833.28
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	408,691,522.60
ጠ/ድምር	ብር	14,119,173,104.23

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት ብር 1,193,674,117.88፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 10,957,913,180.42፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 1,722,681,309.82 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 139,093,398.22 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 105,801,097.89 በቆይታ ጊዜው ያልተተነተነ ነው፡፡ (አባሪ 3/1 ተመልክቷል)

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሒሳብ ከተገኘባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ጤና ሚኒስቴር ብር 6,005,511,975.43፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 1,159,744,050፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 1,012,583,714፣ በፌዴራል መንግስት

ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ብር 970,941,401፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ ብር 756,353,005.5፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 433,597,818.5፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 286,886,896.20፣ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ብር 272,499,071.2፣ የመንግስት ግዥ አገልግሎት ብር 265,228,072.78፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 250,766,953.97 እና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 218,363,536.2 ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 514,525,280.43 በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ የፕሮጀክት ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 30020ዘ/2 ተመልክቷል)

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁንና በ15 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 363,101,215.10 ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋጥ አልተቻለም፡፡

የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው መ/ቤቶች መካከል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 253,373,189.31፣ የመንግስት ግዥ አገልግሎት ብር 39,163,790.17 እና የጤና ሚኒስቴር ብር 28,002,059.43 ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ (አባሪ 3/3 ተመልክቷል)።

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መባከን በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ሌሎች ችግሮች

ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ3 መ/ቤቶች ብር 3,443,374.21 መሆኑ፣

በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ በ4 መ/ቤቶች ብር 7,016,570.32 መሆኑ፤ በ4 መ/ቤቶች የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 7,016,570.32 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፣ በሁለት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 292,579,579.73 የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ መገኘቱ፣ በሁለት መ/ቤቶች ከግንባታ ክፍያዎች ያልተቀነሰ (ተመላሽ ያልተደረገ) የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 17,482,830.27 መገኘቱ፤ በአንድ መ/ቤት ደግሞ ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለት ተሰብሳቢ ሂሳብ/ተቀጽላ ሌጀር የሌለው በመሆኑ ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ ብር 1,136,040.83 መገኘቱ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ (አባሪ 3/4 ተመልክቷል)

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ/እንዲሰበሰቡ፣ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብላቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሳብ

3.1 በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ የተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር ስር ባሉ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች የአክስዮን ትርፍ ድርሻ የገቢ ግብር ብር 5,147,319.06 እና ንግድ ትርፍ ግብር ብር 220,311,281.08 በድምሩ ብር 225,458,600.14፣ እንዲሁም በሌሎች 6 መ/ቤቶች እና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 14,613,015.45 ንግድ ትርፍ ግብር፣ የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ለመሰብሰብ በሚያስገድዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩም በአባሪ-4/3 ተመልክቷል)

ገቢ ለመሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበው ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	12,391.8
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	2,721,571.33
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	11,879,052.32
ጠ/ድምር	ብር	14,613,015.45

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል፣ በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ብር 99,161,281.58፣ ሃዋሳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት 71,270,654.47፣ አዳማ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የሀገር ውስጥ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ ወለድና መቀጫን በመጨመር ከአስመጪዎችና ግብር ከፋዮች መሰብሰብ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ከገቢ አሰባሰብ አንፃር የሚከተሉት ሌሎች የኦዲት ግኝቶች ተገኝተዋል

ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 8,136,001.98 መገኘቱ፣

በቫውቸር ሥርዓት ከቀረጥ ነጻ ገብተው በጊዜ ገደቡ ምርት ላይ ስለመዋሉና ምርቱም ለውጭ ገበያ የቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበለት በመሆኑ አስቀድሞ በቫውቸር የተመዘገበው የቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ በአንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 13,596,147.01 መገኘቱ፣

በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ወደ ሀገር የገባው ዕቃ ቀረጥና ታክሱ የተሰላ ቢሆንም ክፍያ ሳይፈጸምበት የቆየ (assessed but not paid) በ2 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብር 297,075.06 መገኘቱ፣

- በአንድ መ/ቤት የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ከስፖንሰር ድርጅቶች የተሰበሰበ ገንዘብ ብር 8,693,749.27 መገኘቱ፣

- የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ወይም ያልቀረበለት የገቢ ሂሳብ በ1 መ/ቤት 1,708,998 መገኘቱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ (ዝርዝሩን ከአባሪ 4/4-4/9 ተመልክቷል)

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸውና በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በ9 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችና በ10 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ኦዲት/በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ውሳኔ መሰረት/ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ በድምሩ ብር 4,491,040,372.61 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 4/1 ተመልክተል)

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም በተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወስዱ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በ3 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በግብር ከፋዮች ወይም በአስመጪዎች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ወይም የቀረጥና ታክስ ዕዳ አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ዕዳ በድምሩ ብር 410,440,931.1 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ (አባሪ 4/2 ተመልክቷል)

ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች በገቢዎች ሚኒስቴር መካከለኛ ቁ. 1 ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 964,956,028.91፣ ሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 135,926,265.24፣ ምዕራብ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት 79,744,389.82፣ ምስራቅ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 72,754,393.40፣ ጂማ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 67,486,115.39፣ የጉምሩክ ኮሚሽን የቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,280,162,351.67፣ አዳማ

ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 254,652,942.43 ጂግጂጋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 246,330,900.06፣ ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት ብር 162,359,936.94 እና ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 119,959,763.52 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ-ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ሀገሪቱ የልማት ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፣ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ

በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 ሀ እና ለ መሰረት አቅራቢው ሳይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግስት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10% ሳይበልጥ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት መ/ቤቶች በገቡት ውል መሰረት ባልፈፀሙት አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጭዎች ላይ በመመሪያው መሰረት ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ7 መ/ቤቶች እና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ብር 1,017,192.80 ብር ተገኝቷል፡፡(ዝርዝሩ በአባሪ 4/14 ለ ተመልክቷል)

በመሆኑም መ/ቤቶች በተቀመጠው መመሪያና ውል መሰረት ያልሰበሰቡትን ገቢና የጉዳት ካሳ እንዲሰበሰቡ እና ለወደፊቱም መመሪያው በሚጠይቀው መሰረት እንዲፈጽሙ አሳስበናል፡፡

3.4 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2 መ/ቤቶች ከተለያዩ የገቢ ማመንጫ የተሰበሰበው ገቢ ብር 910,656.04 እና በ7 የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤት ቅ/ጽ/ቤት ብር 289,819,699.74 በድምሩ ብር 290,730,355.78 የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። እንዲሁም በአንድ መ/ቤት በዶላር 1,374,914 ዩኤስ ዶላር የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ-4/10 ተመልክቷል)

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.5 በገቢ ያልተመዘገበና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ2 መ/ቤቶች ብር 86,881,039.48 የገቢ ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መሆኑ በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ በአባሪ-4/12 ተመልክቷል/

የተሰበሰበን ገቢ በሪፖርት አለማካተት በመ/ቤቶች የሚዘጋጁ የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች በእለቱ ተሰብስቦ ወደ ባንክ ያልገባ የገቢ ሂሳብ ብር 6,254,795.15 ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም በ8 መ/ቤቶች በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 187,189,294.74፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 10 ቅ/ጽ/ቤቶች በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለባቸው ወጪዎች ባለመካታተቸው ያልተሰበሰበሰ ቀረጥና ታክስ ብር 255,138,107.83 መገኘቱ፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 8 ቅ/ጽ/ቤቶች በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለባቸው የኢንሹራንስ ወጪዎች ባለመካተታቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 118,188,418.62 መገኘቱ፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ክፍያ በተፈጸመበት ቀን ባለው የምንዛሬ ምጣኔ መሰረት ባለመሰራቱ ያልተሰበሰበሰ ቀረጥና ታክስ ብር 1,004,072.13 መገኘቱ፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 3 ቅ/ጽ/ቤቶች የግብይት ዋጋ ከጉምሩክ የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት በመኖሩ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 104,644,448.95 መገኘቱ፣ አባሪ 4/12 ሀ፣ 4/15 ከሀ-ሰ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በትክክል በመመዝገብና በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገንዘብ ሚ/ር ሪፖርት እንዲያደርጉ፤ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም የተጠቀሱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.6 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና አሠራር

የመንግስት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- በ6 መ/ቤቶች በገቡት የውል ግዴታ መሰረት ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ገበታቸው ባልተመለሱ መምህራን ላይ በገቡት ውል መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ ብር 14,263,345.98 መገኘቱ፤ (ዝርዝሩ አባሪ 4/6 ተመልክቷል)
    - ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ኤክሳይስ ታክስና ተርንኦቨር ታክስ በወቅቱ ያላሳወቁ ድርጅቶች ቫት/ቲኦቲ ያላሳወቁ ብዛት 284 እና የንግድ ትርፍ ያላሳወቁ ብዛት 122 በድምሩ 406 በኦዲቱ መገኘታቸው፣ (ዝርዝሩ በአባሪ 4/11 ተመልክቷል)
    - በሁለት መ/ቤቶች የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በገቢ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ ብር 137,504,239.86፣ (ዝርዝሩን በአባሪ 4/14 ተመልክቷል)
    - ያልተሰበሰበ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ብር 110,890,720.22 መገኘቱ፣
    - በ1 መ/ቤት ቦሎና ቀረጥ ሳይከፈል ባልተሟላ ማስረጃ የተፈፀመ የተሽከርካሪ ሽያጭ ገቢ ብር 14,487,711.44 ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 10/1 ረ ተመልክቷል)
    - በአንድ መ/ቤት ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራ ግብር ብር 26,521,701.84 መኖሩ፣
    - በሁለት መ/ቤቶች የገቢ ሂሳብ ዕቅድና ክንውን ችግር መኖሩ፣
    - በሁለት መ/ቤቶች የገቢ ዕቅድ በዝርዝር ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

  ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 4/5 ሐ ሸ፣ ቀ ተመልክቷል)

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም ከላይ የተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መ/ቤቶች ብር 43,545,036.91 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ- 5/2 ሀ ተመልክቷል)

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	17,544,125.03
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		2,445,750
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	5,703,029.6
የልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች	"	38,790.00
ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		17,813,342.28
በድምሩ	ብር	43,545,036.91

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 17,474,125.03፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ብር 8,794,834.49፣ የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ብር 8,746,697.81 የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,406,764.6፣ የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ብር 3,325,475.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ፣ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.2 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ48 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 44,540,734.65 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 5/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	7,722,647.08
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		981,500
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	17,465,026.87
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	10,804,694.62
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	7,566,866.08
በድምሩ	ብር	44,540,734.65

ሆኖ ተገኝቷል።

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ማዕድን ሚኒስቴር ብር 5,719,611.76፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,716,485.82፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 4,677,134.45፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ 3,034,625.64፣ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገዋኔ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ብር 2,455,915.5፣ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ብር 2,185,589.00፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 1,956,014.99፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር ብር 1,718,205 እና የኢትዮጵ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ብር 1,713,089.61 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 5/1 ተመልክቷል)

ለክፍያዎች የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በተጨማሪ የወጪ የሂሳቡን ተዓማኒነት ሊያሳጣ የሚችል በመሆኑ የወጪ ማስረጃ ላልቀረበላቸው ክፍያዎች የወጪ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.3 <u>ደንብና መመሪያ ውጪ አላግባብ የተፈፀሙ ወጪ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ30 መ/ቤቶች 16,407,985.47 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-5/3 ተመልክቷል/ ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ11 መ/ቤቶች ያለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ደረሰኝ የተፈጸመ ክፍያ ብር 37,367,913.29 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/16 ተመልክቷል፡፡

ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ወጪ ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	3,852,206.43
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	5,564,901.29
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,880,779.32
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	512,769.22
ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		4,597,329.21
በድምሩ	ብር	16,407,985.47

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 3,001,220፣ የመንግስት ኮምንኬሽን አገልግሎት ብር 2,889,321.58፣ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ብር 2,442,200፣ የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,156,500.00፣ ማሪታይም ባለስልጣን ብር 1,023,138.90 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

መሥሪያ ቤቶች የሚፈጽሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ካልተከተሉ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቶች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው እና አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችም ተመላሽ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ</u>

የፌደራል የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 'ሀ' ለደመወዝ ዝግጅት የሚከተሉት መረጃዎች መሟላት አለባቸው በሚለው ውስጥ የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሠራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ የደመወዝ ክፍያ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ16 መ/ቤቶች በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ ብር 485,183.59 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ክፍያዎች መመሪያን ተከትለው እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 5/4 ተመላክቷል)

4.5 <u>በሲቪል ሰርቪስ ኮሚን ባልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ</u>

በመ/ቤቶች የሚፈፀመው ቅጥር በስቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ደንብና መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሰደረግ፣

በ10 መ/ቤቶች ብር 42,748,121.67 በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 5/5 ተመላክቷል)

የኮንትራት ሠራተኞች ለመቅጠር አስገዳጅ የሆኑ የስራ ክፍሎች ተለይተው ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማስፈቀድ መሆን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.6 <u>በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

በመ/ቤቶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ6 መ/ቤቶች እና በገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች ስር በሚገኙ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 66,727,252.62 አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ / ዝርዝሩ በአባሪ 5/6 ተመላክቷል/

ማንኛውንም ክፍያ ሲያከናውን ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን እንደሚገባና የክፍያ ተመን ላልወጣላቸው ክፍያዎች የሚመለከተው አካል የክፍያ ተመን እንዲያወጣላቸው ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.7 አላግባብ የተከፈለ የግብር መቀጫ፤የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት አላግባብ የተከፈለ ቅጣት

በ8 መ/ቤቶች ብር 16,346,989.68 አላግባብ የተከፈለ የግብር መቀጫ፤የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት አላግባብ የተከፈለ የወለድ ቅጣት ተገኝቷል፡፡ በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት አላግባብ የተወረሰ ተሽከርካሪን ለባለቤቱ እንዲመልስ በፍርድ ቤት የተሰጠው ጊዜ ገደብ በማለፉ ፍርድ ቤቱ የተሽከርካሪውን ግምታዊ ዋጋ እንዲያቀርብለት ለጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መ/ቤት በጠየቀው መሰረት በአዲስ ተሽከርካሪ ከፍተኛ ዋጋ ቀረጥና ታክስን ጨምሮ ዋጋ በመስጠቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብር 10,070,064.95 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ 5/8 ተመላክቷል)

በ1 መ/ቤት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ ሁለት ጊዜ የተመዘገበ ወጪ ብር 734,284.94፣

በ8 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,497,114,515.14 እና 7 የኦዲት ፋይሎች ለኦዲት ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፡፡ / ዝርዝሩ በአባሪ 5/11 ተመላክቷል/

በ1 መ/ቤት በቁጥር 55 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ምደባ የተፈፀመ መሆኑ፣ በሌላ አንድ መ/ቤት ደግሞ በዕቅዱ መሰረት መሰራት ሲኖርበት ለትርፍ ሰዓት የተከፈለ ብር 346,545.81 መሆኑ፣ አባሪ 5/13 እና 5/14 ተመልክቷል፡፡

ወጪዎች አፈፃፀም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.8 በብልጫ አላግባብ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት

ሲደረግ፡- በ32 መ/ቤቶች እና በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 4,968,408.26 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 57,683,793.41 በድምር ብር 62,652,201.67 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-5/17 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡትን ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፣ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.9 ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ

ለግንባታ ስራዎች የተፈቀደው በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም ለተቋራጮቹ የሚሰጡ ማናቸውም ቅድሚያ ክፍያዎች በሚቀርበው የተቋራጮች ክፍያ ላይ ለቅድመ ክፍያ በተቀመጠው ፐርሰንት ልክ ተቀናሽ እየተደረገ ለመንግስት ተመላሽ መደረግ እንደሚኖርበት የፋይናንስ ህጉ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ 2 መቤቶች ለቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ በድምሩ ብር 133,555,459.90 ከተቋራጮች ተመላሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ እንዲሁም በ1 መ/ቤት ውል ከተቋረጠ በኋላ ተመላሽ ያልተደረገ ብር 15,411,224.99 በድምሩ ብር 148,966,684.89 በኦዲት ወቅት ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ-5/18 ተመልክቷል)

የተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ ለመንግስት ፈሰስ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ73 መ/ቤቶችና በ15 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,573,435,682.25 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 5/20 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	320,446,681.80
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	192,9594,963
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	157,438,256.7

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	49,074,744.72
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	58,650,294.43
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	58,230,741.3
በድምር	ብር	2,573,435,682.25

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡ ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 2,219,952,785.14፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 108,781,488.62፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 96,187,579.93፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር 13,840,367.55 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 134,673,461.01 ናቸው፡፡

ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ገቢዎች ሚኒስቴር ዋናው መ/ቤት ብር 1,845,081,624.67፣ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ብር 91,059,356.22፣ የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 65,505,288.81፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 62,911,764.97፣ የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩንቨርሲቲ ብር 57,185,359.91፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 37,430,081.28፣ ምዕራብ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ፅ/ቤት ብር 30,909,250.85፣ የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ብር 23,179,483.60፣ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ብር 20,724,803.5 እና ጉምሩክ ኮሚሽን ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ብር 20,388,811.7 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ በ14 መ/ቤቶች የብር 96,429,644.41 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ 5/21 ተመልክቷል፡፡/

በሌላ በኩል ከሚያዝያ በኋላ በቀሩት ሁለት ወራት ውስጥ፣ የግዥው አንገብጋቢነትና የበላይ ኃላፊ ሳይፈቅድ ግዥዎች መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት የብር 32,771,637.95 ግዥዎች ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/16 ተመልክቷል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀም ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም የሚያሳጣ ነው፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ ግዥዎች ሲፈፀሙ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

4.11 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ9 መ/ቤቶች በብር 2,196,501.19 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ2 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 58,653,155.12 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርብላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ በአባሪ 5/22 ሀ እና ለ ተመልክቷል/

ንብረቶቹ ለመደረጋቸው ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበው በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	743,913.00
አቅን ግንባታ መ/ቤቶች	"	931,089.25
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	521,498.94
በድምሩ	ብር	2,196,501.19

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ላወጠው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶች በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.12 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ4 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 6,751,884.15 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-5/27 ተመልክቷል/

የቅድሚያ ክፍያን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች፡- የፌዴራሉ ሪፐብሊካን ጥበቃ ኃይል ብር 2,217,300.00፣ የቤተ-መንግስት አስተዳደር ብር 705,985.25፣ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,202,966.00 እና የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ብር 625,632.90 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ የግንባታ ክፍያዎችም በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት ከእያንዳንዱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተቀንሶ ለመንግሥት ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.13 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ71 መ/ቤቶች እና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 293,470,433.15 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ- 5/25 ተመልክቷል)

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	47,185,246.29
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		7,570,847.33
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	56,442,824.95

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	38,349,758.27
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	129,731,502.40
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	14,190,253.91
በድምር	ብር	293,470,433.15

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል፡-

አማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 108,749,200.18፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 27,190,058.66፣ የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ብር 25,065,959.85፣ ኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ብር 11,778,519.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.14 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ21 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 4,4894,644.74 የወጪ ሒሳብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግቦ ተገኝጣል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ- 5/24 ተመልክቷል)

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስን ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	8,445,860.71
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		30,072,138.92
ልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	128,340.95
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	6,248,304.16
በድምሩ	ብር	44,894,644.74

የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት ዓመቱ ለተገኘ አገልግሎት ወጪውም በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.15 <u>በአግባቡ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ</u>

የወጪ ሂሳብ በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት በአግባቡ መፈጸሙንና በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ1 መ/ቤት ብር 56,178,158.97 የወጪ ሂሳብ በድጋሚ የተመዘገበ መሆኑ፤ በ2 መ/ቤት ብር 721,743.72 የወጪ ሂሳብ በብልጫ የተመዘገበ መሆኑ፣ በ2 መ/ቤቶች ብር 7,815,207.57 በማነስ የተመዘገበ እና በ2 መ/ቤቶች ብር 1,222,117.91 የወጪ ሂሳብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 5/23 ተመልክቷል)

ለሂሳቦቹ ተገቢ የሂሳብ ማስተካከያ መስራት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግስት መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙና በትክክል እንዲመዘገቡ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.16 <u>በወጪ አፈፃፀም ላይ በተለያዩ መ/ቤቶች የታዩ ሌሎች ችግሮች</u>

- በ1 መ/ቤት አላግባብ በወጪ የተመዘገበ የግንባታ መያዣ ተመላሽ ክፍያ ብር 44,755,532.47 መገኘቱ፣
- በ2 መ/ቤቶች በአማካሪ መሐንዲስ የክፍያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 170,394,448.47 መከፈሉ፣
- በ1 መ/ቤት መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ ለስራ ተቋራጭ የተሰጠ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ ብር 16,618,007.30 መገኘቱ፣
- በ1 መ/ቤትና በ2 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽቤቶች በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደና በወጪ የተመዘገበ 3,255,857.08 መገኘቱ፣
- በ2 መ/ቤቶች አግባብ ባለው ባለሥልጣንና ቦርድ ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ ብር 430,560.00 ክፍያ መፈፀሙ፣ (አባሪ 5/26 ተመልክቷል)

- በ4 መ/ቤቶች በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 6,751,884.15 መገኘቱ፣
- በ2 መ/ቤቶች በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ ወጪ ሂሳብ ብር 924,505.86 መገኘቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/28 ስር ሀ-ከ ተመልክቷል፡፡
- በ1 መ/ቤት የቀን ሰራኞችን እንደ ኮንትራት ሰራተኛ በመቅጠርና በማሰራት የተፈጸመ ክፍያ ብር 13,520,250.17 መገኘቱ፣ (ዝርዝሩ አባሪ 10/1 ሀ ተመልክቷል)

በተጨማሪም የሚከተሉት ከወጪ ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ግኝቶች ታይተዋል፡፡

- በመ/ቤቱ ኃላፊ ያልተፈቀደ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በ2 መ/ቤቶች ብር 530,102.75 መገኘቱ፣
- በ1 መ/ቤት የስራ ዝርዝር መግለጫ (Bill of quantity) ሳይቀርብ ለቢሮ እድሳት ወጪ የሆነ ብር 7,300,000.02 መገኘቱ፣
- በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 279,915.90 መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡

ወጪዎች መንግስት ባወጣቸው ድንብና መመሪያዎች እንዲፈፀሙ እንዲሁም የምዝገባ ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ከላይ የተጠቀሱ የክፍያ ችግሮችም አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5 የተከፋይ ሂሣብ

5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-በ81 መ/ቤቶችና በ14 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,052,366,599.87 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-6/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	559,128,479.90
የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	7,390,605.16
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	79,473,085.21

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	85,536339.55
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	104,047,903.47
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	216,790,186.6
ድምር	ብር	1,052,366,599.87

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡

የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታ ጊዜው ሲተነተን፡- ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት ብር 226,938,553.05፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 5,089,75,623.31፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 29,599,360.42 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 284,952,444.76 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 1,900,618.33 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡

እንዲሁም በ4 መ/ቤቶች ደግሞ ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት ብር 12,443,978.09፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 104,60,115.82፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 1,090,309.21 በድምሩ ብር 23,994,403.12 የፕሮጀክት ተከፋይ ሂሳብ በኦዲቱ ታይቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ-6/2 ተመልክቷል)

በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡-

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ብር 268,067,702.92፣ የመንግስት ግዥ አገልግሎት ብር 194,872,813.34፣ የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ብር 90,066,409፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 77,496,027.43፣ የግብርና ሚኒስቴር ብር 6,788,0451.11 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑን በማጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ሌሎች ድክመቶች

- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ3 መ/ቤቶች ብር 3,636,445.73 መኖሩ፣
- በ2 መ/ቤቶች ያለአግባብ የተመዘገበ የተከፋይ ሂሳብ ብር 23,027,175.36፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት በ1 መ/ቤት ብር 84,820,262.99 ተገኝቷል፡፡
- በ1 መ/ቤት በገቢ መታየት የነበረበት በተከፋይ ሂሳብ የያዘ መ/ቤት ብር 457,643,809.64 መገኘቱ፣
- በ1 መ/ቤት በወጪ መታየት የነበረበት በተከፋይ ሂሳብ የሚታይ ፕሮጀክት ሂሳብ ብር 64,846,538.71 መኖሩ፣
- በ1 መ/ቤት የፕሮጀክት ወጪን ከመደበኛ ሂሳብ ጋር 5054 በተከፋይ ሂሳብ የያዘ መ/ቤት ብር 144,455,549.86፣
- በ1 መ/ቤት ያልተመዘገበ የግንባታ መያዣ **(Retention)** ተከፋይ ሂሳብ ብር 9,025,910.00 ያልተያዘ፣
- በ1 መ/ቤት የግንባታ ሥራ የጥራት ዋስትና መያዣ (Retention) ሳይቀነስ የተፈጸመ ክፍያ ብር 966,197.34 መኖሩ፣
- ባለመብቱ ማንና ለማን እንደሚከፈል ያልታወቀ በ14 መ/ቤቶች ብር 1,754,048,466.57 መኖሩ፣
- ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ያልተደረገ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 649,497.42፣ ቅድሚያ ክፍያ ብር 554,459.57፣ የመያዣ ሂሳብ ብር 413,054.68፣ የስራ ግብር ብር 84,600.00፣
- (ዊይዝሆልድ ታክስ) ብር 32,883.06 በሌላ በኩል ደግሞ በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 5,118.44 መገኘቱ፣(ዝርዝሩ በአባሪ 6/3 ሀ-ተ ተመልክቷል)

በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮችን ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ምዝገባዎች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ተጠብቆ መከናወን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 በበጀት ኮዱ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ20 መ/ቤቶች በልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 524,796,213.55፣ ከውስጥ ገቢ ብር 288,998,079.52 እና ከካፒታል በጀት ብር 489,429,895.62 በድምሩ ብር 1,303,224,188.69 ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩም በአባሪ 7/1 ተመልክቷል)

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	112,746,859.27
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	92,137,714.58
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,050,380,663
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		19,355,851.11
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	28,603,101.15
ጠ/ድምር	ብር	1,303,224,188.69

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፡- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 322,547,520.3፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ተጠሪ ተቋማቱ ብር 267,930,274.6፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 173,212,241.4፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 128,153,771.3፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 109,533,570.54፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 91,376,175.48፣ የአምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 83,386,864.29 እና የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ 75,107,915.65 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ብር 9,741,854.73 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣ (ዝርዝሩ በአባሪ- 7/2 ተመልክቷል)

መ/ቤቶች በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደረግ እንደሚገባ እና የበጀት እጥረት ካጋጠመም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ መጠቀመቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተጠቀሙበትን ብቻ በመውሰድ በ101 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 5,357,361,315.89፣ የውስጥ ገቢ ብር 207,644,481.79 እና ካፒታል ብር 13,725,126,257.26 በድምሩ ብር 19,290,132,054.94 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡(ዝርዝሩም በአባሪ-7/1 ተመልክቷል)

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	10,249,945,604.40
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	648,789,176.6
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	4,215,004,662.
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	609,738,799.7
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	2,855,149,467.
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	711,504,346.
ጠ/ድምር	ብር	19,290,132,054.94

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች መካከል የገንዘብ ሚኒስቴር ብር 8,018,899,476.47፣ ጤና ሚኒስቴር ብር 1,993,400,893፣ የግብርና ሚኒስቴር ብር 1,202,273,994፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 818,498,803.75፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 727,839,708.8፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 724,283,117.7፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 613,657,992.1፣ ጉምሩክ ኮሚሽን ብር 531,634,478.4፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 449,507,901፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ተጠሪ ተቋማቱ ብር 398,128,357.8፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር ብር 346,223,039.46 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 <u>የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች</u>

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች መኖራቸውን በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 8/1 ሀ እስከ ደ ተመልክቷል)

ንብረት አስተዳደር

የግኝት መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	15	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	9	4
ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	14	
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ/ስቶር ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	6	3
የአላቂ የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ	21	2
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	44	3
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግስት መመሪያ መሰረት ሳይወደጉ የተገኘባቸው	56	8

የግኝት መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	15	
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ	10	2
የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ያልተረጋገጠ	3	
የንብረት ጥበቃ ላይ ተመድበው ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች	1	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸውና ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገ/32 ተሽከርካሪዎችናሌሎች የተለያዩ ዕቃዎች/		6
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸው (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለፁ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር 5,789,078.63 ይገኙበታል)	15	3
በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎቸ ዋጋ ያልተመኑ መ/ቤቶች	1	2
አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ዕቃዎች ተለይተው የማይቀመጡ መሆኑ		6
ጊዜው ያለፈበት መድሃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ	15	1

(ዝርዝሩ በአባሪ 8/1 ከሀ እስከ የ ተመልክቷል)

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል። የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በእያንዳንዱ የኦዲት ሪፖርት በዝርዝር እና ዋና ዋናዎቹም በየዘርፉ የንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 <u>ተሽከርካሪ</u>

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

የግኝት መግለጫ	የተሽከርካሪዎች ብዛት		
	የመ/ቤቶች/ቅ*	መኪና	ሞተር ብስክሌቶች/**
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	13/3*	85	11/6**
በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆሙ	37/4*	473	27/65**
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	2/2*	5	11
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መ/ቤቶችና ድርጅቶች ስም የሆነ	21/4*	188	20

የሞተር ቁጥር የሌላቸው	1	5	4
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት ያለው	1	8	
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው /ጌጅ/ የማይሰራ	9	85	4
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው / የማያደረጁ	10/1*	89	4
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1/1*	1	4

ቅ*- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ** ሌሎች- ሎቤድ፣ ትራክተር የቁፋሮ ማሽን፣ ኮምፕሬሰር…መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 8/2 ከሀ እስከ ፐ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፣ ሊብሬ እና ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት እርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ

በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት እና ቀደም ባሉት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ90 መ/ቤቶች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት ከተሰጠበት ሒሳብ ብር 443,023,846.91 እና 23,230.43 የአሜሪካ ዶላር ውስጥ ብር 394,805,880.56 እና

23,230.43 የአሜሪካ ዶላር እርምጃ ያልተወሰደበት ቀሪ ሂሳብ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ብር 48,217,965.67 ተመላሽ መደረጉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በገቢዎች ሚኒስቴር በሚገኙ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች እና በጉምሩክ ኮሚሽን ስር በሚገኙ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ ብር **18,397,938,661.00** እርምጃ እንዳልተወሰደ ታውቋል፡፡

2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ላይ እርምጃ አወሳሰድ የተሟላ ማስረጃ ሰነድ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ17 መ/ቤቶችና በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ከተሰጠው ብር 5,061,185,100.80 ውስጥ ብር 508,157,756.13 የሰነድ ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን ብር 4,553,027,344.67 ደግሞ የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑን ማረጋገጥ ተችላል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 9/1ለ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሒሳብ በዘርፍ የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት

3.1 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግስት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግስት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብን ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የ35 መ/ቤቶች፤ 4 ቅርንጫፎች እና የመንግስት የተጠቃለለ የገቢና የውጪ ሂሳብ ጨምሮ በድምሩ 36 መ/ቤቶች እና 4 ቅርንጫፎች በዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡

የዳይሬክቶሬቱ የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ከመንግስት የተጠቃለለ የገቢና የውጪ ሁሉም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኦዲቱ ተጠናቆ የኦዲት ሪፖርትና የመጨረሻ የስራ አመራር ሪፖርት ከተላከው በኋላ የተዘጋጀ በመሆኑ በግኝቶችም ይሆን በኦዲት አስተያየቶች ላይ የሚቀየር አይኖርም፡፡ የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ ዝርዝር ስራው ተጠናቆ ረቂቅ የስራ አመራር ሪፖርት ክለሳ ላይ በመሆኑ ሙሉ ኦዲቱ ሲጠናቀቅ የኦዲት ሪፖርቱን ያሟላ ይሆናል፡፡

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቶች ዕቅድና ክንውን

1.1 የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			መግለጫ
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር	
1	ገንዘብ ሚኒስቴር	30/12/2015	2,053,944,544.82	7,130,347,838.78	9,184,292,383.60	
2	የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት	25/12/2015	320,238,114.26	169,588,255.65	489,826,369.91	
3	የኢት. ዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለስልጣን	12/03/2016	138,318,035.71	30,300,000.00	168,618,035.71	
4	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት	12/02/2016	346,229,539.91	0.00	346,229,539.91	
5	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	23/12/2015	117,254,810.17	0.00	117,254,810.17	
6	የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ	12/12/2015	31,988,370.00	0.00	31,988,370.00	
7	የፌዴራል ሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል	25/04/2016	261,256,846.00	0.00	261,256,846.00	
8	የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	29/12/2015	155,679,752.92	0.00	155679752.92	
9	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	11/03/2015	6,645,451,269.00	734,145,722.00	7,379,596,991.00	
10	የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት	23/02/2016	784,480,138.70	184,381,807.36	968,861,946.06	
11	የቤተ-መንግሥት አስተዳደር	26/11/2015	389,077,661.00	1,075,243,366.72	1,464,321,027.72	
12	የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር	12/12/2015	76,977,999	0.00	76,977,999	
13	የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልገሎት	21/02/16	822,775,480	0.00	822,775,480	
14	የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ	5/1/2016	150,000,000	433,650,000	583,650,000	
15	የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን	10/2/2016	176,881,425	0.00	176,881,425	
16	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	25/03/16	107,915,000	0.00	107,915,000	
17	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንት አስተዳደር	15/12/15	934,561,512	484,555,121.34	1,419,116,633.34	

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			መግለጫ
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር	
18	የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት	23/12/15	42,927,270	0.00	42,927,270	
19	የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት	11/1/2016	153,391,862.98	0.00	153,391,862.98	
20	የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ	8/2/2016	607,280,268	897,905,268	1,505,185,536	
21	የፕላንና ልማት ሚኒስቴር	15/03/16	94,459,527.01	0.00	94,459,527.01	
22	የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን	15/12/15	23,922,800	0.00	23,922,800	
23	የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር	27/03/16	349,227,668.38	629,726,503	978,954,171.38	
24	ቱሪዝም ሚኒስቴር	18/03/2016	206,213,830.00	400,000,000.00	606,213,830.00	
25	የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	23/12/2015	95,009,128.68	0.00	95,009,128.68	
26	የመንግሥት ግዥ አገልግሎት	23/12/2015	81,801,643.01	0.00	81,801,643.01	
27	የኢዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን	9/2/2016	135,098,000.00	0.00	135,098,000.00	
28	የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት	14/04/16	240,000,000.00	300,000,000.00	540,000,000.00	
29	የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	14/01/2016	88,848,453.56	41,865,697.98	130,714,151.54	
30	የኢትዮያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ	6/3/2016	708,311,884.29	0.00	708,311,884.29	
31	የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት	16/05/2016	323,246,848.49	281,487,200.00	604,734,048.49	
32	የመንግስት ኮመኒኬሽን አገልግሎት	11/12/2015	107,031,440.00	0.00	107,031,440.00	
33	የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን	02/13/2015	69,554,000.00	9,233,000.00	78,787,000.00	
34	የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን	12/12/2015	75,222,106.46	0.00	75,222,106.46	
35	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንሲቲትዩት	11/4/2016	1,599,804,023.76	61,553,412.38	1,661,357,436.14	

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			መግለጫ
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር	
36	የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ	01/05/2016				በመንግስት የተጠቃለለ የገቢና የውጪ ሂሳብ የታዩ
	የበጀት ድጋፍ					
36.1	የአገር ውስጥ ዕዳ		70,000,000,000.00		70,000,000,000.00	
36.2	የውጪ አገር ዕዳ		55,956,330,000.00		55,956,330,000.00	
36.3	ግዴታዎች		1,000,000,000.00		1,000,000,000.00	
36.4	የደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ወጪ መጠባበቂያ		23,077,830,000.00		23,077,830,000.00	
36.5	የባንክ ወጪዎች መጠባበቂያ		10,000,000.00		10,000,000.00	
ጠቅላላ ድምር			**168,558,541,253.00**	**12,863,983,193.00**	**181,422,524,446.32**	

1.2 የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

ተ.ቁ	የኦዲት የተደራጊው መ/ቤት ስም	የተሰጠው የኦዲት አስተያየት			
		ነቀፌታ የሌለበት Clean Opinion	በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት(Except for opinion)	የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse opinion/	ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች (Disclaimer opinion)
1	ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት				✓
2	የፌዴራሉ ሪፐብሊካን ጥበቃ ኃይል				✓
3	የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን				✓
4	የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት				✓
5	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር				✓
6	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ			✓	
7	የመንግስት ግዥ አገልግሎት			✓	
8	የኢትዩጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ			✓	
9	ኢሚግሬሽነና ዜግነት አገልግሎት			✓	
10	ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር			✓	
11	የገንዘብ ሚኒስቴር የተጠቃለለ የገቢና ወጪ ሪፖርት		✓		
12	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት		✓		
13	የቤተ-መንግስት አስተዳደር		✓		
14	የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር		✓		
15	ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር		✓		
16	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን		✓		
17	ቱሪዝም ሚኒስቴር		✓		
18	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ከምሽን	✓			
19	የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ	✓			
20	የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት	✓			

ተ.ቁ	የኦዲት የተደራጊው መ/ቤት ስም	የተሰጠው የኦዲት አስተያየት			
		ነቀፌታ የሌለበት Clean Opinion	በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት(Except for opinion)	የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse opinion/	ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች (Disclaimer opinion)
21	የኢትዮጵያ ዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለስልጣን	✓			
22	የገንዘብ ሚኒስቴር	✓			
23	የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት	✓			
24	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት	✓			
25	የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	✓			
26	የመንግስት ኮምንኬሽን አገልግሎት	✓			
27	የኢትዮጲያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን	✓			
28	የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	✓			
29	የኢትዩጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን	✓			
30	የኢትዮጳያ ኮሚዩኒኬሽን ባለሥልጣን	✓			
31	የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት	✓			
32	የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት	✓			
33	የፕላንና ልማት ሚኒስቴር	✓			
34	ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት	✓			
35	የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን	✓			
36	የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ	✓			

የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኦዲት ከተደረጉት ውስጥ ከመንግስት የተጠቃለለ የገቢና የውጪ ሂሳብ ውጪ 35 የሂሳብ ሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻ የስራ አመራር ሪፖርት የተላከ ሲሆን ቀጥሎ የተመለከተው የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

- ነቀፌታ የሌለበት **Clean Opinion** 19 (**አስራ ዘጠኝ**) መ/ቤቶች፤
- በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት (**Except for opinion** 6 (**ስድስት**) መ/ቤቶች፤
- የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (**Adverse opinion**) 5 (**ስድስት**) መ/ቤቶች፤
- ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች (**Disclaimer opinion**) 5 (**አምስት**) መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. ጥሬ ገንዘብ

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘባቸው መ/ቤቶች፤

በሁለት መ/ቤቶች ማለትም፡-

- ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ብር 367,025.00 እና
- የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ብር 16,213.48

በድምሩ ብር 383,238.48 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት በታየባቸው ባለበጀት መ/ቤቶች ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በጉድለት የታየው ገንዘብ እንዲተካ አሳስበናል።

1.2 በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ እጅ መያዝ ከሚገባው በላይ በጥሬ ገንዘብ የተገኘ

- በቤተመንግሥት አስተዳደር በድምሩ ብር 190,579.77 በካዘና ከተፈቀደው በላይ ተቀምጦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የሚመለከተው አካል ለወደፊት ይህ እንዳይፈጠር ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

1.3 የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ የማያስገቡ

- የቤተ-መንግስት አስተዳደር በድምር ብር 642,587.41 የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይሆን መሆኑ በኦዲት ተረጋግቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መ/ቤቱ የሚሰበሰብ ገቢ በየዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ ከሆነ ብልሹ አሠራር ሊያስከትል ስለሚችል በበላይ ኃላፊዎች ገንዘቡ በወቅቱ እንዲገባ ተገቢው የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘጋጅለትና ገንዘቡም በወቅቱ ገቢ ስለመደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.4 መደበኛ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተጣራ ሃብት ሂሳብ (Net Asset Equity Account)

በፌዴራል የመንግስት መስሪያቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ቁጥር 2 ፊደል ለ መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመመሪያው መሰረት እያንዳንዱ ሂሳብ አርዕስት በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በመንግስት ኮምኒኬሽን አገልግሎት በድምሩ ብር 1,111,709.62 ከመደበኛ የሂሳብ ሚዛን ውጪ ወይም መደበኛ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተጣራ ሃብት ሂሳብ በዴቢት የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የተጣራ ሀብት ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ሊያሳይ የቻለበት ምክንያት በማጣራት፣ ተገቢውን የሂሳብ ማስተካከያ በመስራት የሂሳብ ሪፖርቶች እንዲስተካከሉ እና ለወደፊቱም ማንኛውም ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛ የሂሳብ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ዴቢትና ክሬዲት ሚዛኑ የሚገጥም መሆኑ እንዲረጋገጥ ስራ አመራሩ የእርምት እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.5 የፕሮጀክት ስራቸው ተጠናቆ የባንክ ሂሳባቸው ያልተዘጋ የፕሮጀክት ሂሳብ

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በድምር 226,243.88 የፕሮጀክት ስራቸው ተጠናቆ የባንክ ሂሳባቸው ያልተዘጋ የፕሮጀክት ባንክ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

እንቅስቃሴ የሌላቸው የፕሮጀክት ሂሳቦች በአጠቃላይ የሌጀር ሚዛን ላይ የሚታዩ ቋሚ ሂሳቦች ማለትም የሳጥንና የባንክ የጥሬ ገንዘብ፣ የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳቦች ሚዛናቸውንና ትክክለኛነታቸውን በተገቢው መንገድ በማጣራት በተደረሰው ውጤት መሰረት እና በፕሮጀክቶቹ የውል ስምምነት መሰረት ሂሳቡ በትክክል ተዘግቶ ሪፖርት መደረግ እንዳለበትና ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2 **ተሰብባሰቢ ሂሳብ**

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 648/2001፣ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተሰብሳቢ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከፊደል ሀ-ሰ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት በወቅቱ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 **በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂማብ**

ሀ. **የመደበኛ ሂሳብ**

በ26 መ/ቤቶች ውስጥ ፡-

- በ16 መ/ቤቶች ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት የቆየ በድምር ብር 89,336,309.80
- በ 22 መ/ቤቶች ከ 1 ዓመት እስከ 5 ዓመት በድምር ብር 741,496,755.79
- በ 16 መ/ቤቶች ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት በድምር ብር 264,373,758.97
- በ7 መ/ቤቶች ከ 10 ዓመት በላይ በድምር ብር 5,496,655.79
- በ2 መ/ቤቶች በቆይታ ዕድሜው ያልተተነተነ በድምር ብር 22,118.04

ጠቅላላ ድምሩ ብር 1,100,725,598.39

በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ተገኝቷል፡፡

ለ.**የፕሮጀክት ሂሳብ**

በ4 መ/ቤቶች፡-

- በ3 መ/ቤቶች ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት የቆየ በድምር ብር 63,705,886.67
- በ2 መ/ቤቶች ከ 1 ዓመት እስከ 5 ዓመት በድምር ብር 68,157,314.02
- በ2 መ/ቤት ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት በድምር ብር 382,662,079.74

በድምሩ ብር 514,525,280.43

በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ የፕሮጀክት ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በተሰብሳቢ ሂሣቦች ላይ ተገቢ ክትትል እየተደረገ በወቅቱ እንዲሰበሰብ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በውዝፍ የተገኘው ተሰብሳቢ ማስረጃ ቀርቦለት እንዲወራረድ ካልሆነም ገንዘቡ እንዲመለስ አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች

2.2.1 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ

- በ7 መ/ቤቶች ውስጥ በድምሩ ብር 55,982,583.93 ገንዘቡ ከማን እንደሚሰበሰብ፣ መቼ ወጪ እንደሆነና መቼ እንደሚወራረድ የማይታወቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መቼ በተሰብሳቢ እንደተያዘና ከማን እንደሚሰበሰብ መነሻ ሰነድ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ በመኖሩ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ሆነ አስተያየት ለመስጠት ስለማይቻል የመነሻ ሰነድ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ሰነዱን ፈልጎ ማቅረብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.2.2 ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው መ/ቤቶች (አባሪ 3.3 ሀ)

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ጂማ ቅርንጫፍ በድምር ብር 392,490.30 ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ **(Abnormal balance)** የሚታይባቸው መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ሊያሳይ የቻለበት ምክንያት በማጣራት ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ በመስራት የሂሳብ ሪፖርቶቹ እንዲስተካከሉ በማድረግ ሪፖርት ሊቀርብ

ይገባል፡፡ ለወደፊቱም እንደዚህ ነዓይነት ስህተት እንዳይከሰት ክትትልና ቁጥጥር እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.2.3 የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ

- የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ብር 3,931,426.57
- የመንግስት ግዥ አገልግሎት ብር 288,648,153.16

በድምሩ ብር **292,579,579.73** የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የተሰብሳቢ ሂሳቦች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የተሰብሳቢ ሂሳብ አርዕስታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፤ በመሆኑም አለአግባብ በግዥ ሰራተኞች ተመዝግቦ የሚገኘው የተሰብሳቢ ሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3 የገቢ ሂሣብ

የገቢ ሂሳብ በአግባቡ መሰብሰቡንና በሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መመዝቡን እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ፣ ደንብና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ግብር እና ታክስ መቀነሱንና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

3.1 በሌሎች መ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ገቢ

- የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ብር 845,370.69 የስራ ግብር
- የቤተ-መንግስት አስተዳደር ብር 1,853,306.44 የስራ ግብር
- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 22,894.20 የስራ ግብር

በድምር ብር **2,721,571.33**

ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተሰበሰበው ገንዘብ ተሰብስቦ ለሚመለከው አካል ገቢ እንዲሆን አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተቀነሰ የሕክምና መዋጮ

- የቤተ-መንግስት አስተዳደር 5,856.24 ከአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር የህክምና መዋጮ በመመሪያው መሰረት ከደመወዛቸው ተቀናሽ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ከደመወዝ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ የቦርዱ ኃላፊዎች እንዲከፍሉ በማድረግ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.3 <u>ተገቢው ማስረጃ ባለመቅረቡ የገቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች</u>

ከ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **910,656.04 እና በ1 መ/ቤት $ 1,374,914.00** ተገቢው ማስረጃ ባለመቅረቡ የገቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የገቢ ሂሳቡ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ያልተመዘገበበትን እና ሪፖርት ያልቀረበበትን በማጣራት መ/ቤቶቹ ለወደፊቱ የገቢ ሂሳብን ምዝገባ በማከናወን በሚያቀርበው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት እንዲካተት አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የገቢን ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች፣</u>

- ትራንስፖትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር 146,160.00
- የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ 86,734,879.48

በድምሩ ብር 86,881,039.48 በገቢን ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተተ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ያልተመዘገበውን ገቢ በመመዝገብ ወይም ማስተካከያ በመስራት ትክክለኛ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 <u>በእለቱ ተሰብስበው ወደ ባንክ ያልገባ የገቢ ሂሳብ፣</u>

የትራንስርትና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር ብር 5,472,233.10 በእለቱ ተሰብስበው ወደ ባንክ ያልገባ የገቢ ሂሳብ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መ/ቤቱ የሚሰበሰበው ገቢ በየዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ ከሆነ ብልሹ አሰራር ሊያስከትል ስለሚችልና መንግስት በወቅቱ ከተሰበሰበው ገንዘብ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣው ስለሚችል፣ በእለቱ የተሰበሰበው ገቢ በእለቱ ወደ ባንክ መግባቱን በበላይ ኃላፊዎች ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.6 በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ፣

- የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ብር 28,028,835.85
- የቤተ-መንግስት አስተዳደር ብር 25,314,641.24
- የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ብር 60,680,275.70

በድምሩ ብር 114,023,752.79

በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር ገቢ የሚሰበስቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ባልጸደቀ መመሪያ መሰብሰብ ስለማይቻል አዲስ የቀረበው ረቂቅ የአገልግሎት ክፍያ ተመን አፀድቆ ስራ ላይ እንዲያውል በ2011 ጀምሮ የኦዲት ሪፖርት የአስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በ2015 በጀት ዓመትም ባልጸደቀ መመሪያ ገቢ እየሰበሰበ በመሆኑ በአስቸኳይ ማስተካከል ያለበት ሲሆን በተሰጠው አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ባልወሰዱ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለብት አሳስበናል፡፡

3.7 የገቢ ዕቅድ በዝርዝር ያልተዘጋጀ

- የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እና በቤተመንግሥት አስተዳደር የወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል በመመሪያው መሠረት የገቢ እቅድ በዝርዝር በየሂሳብ መደቡ የማያዘጋጅና ያልፀደቀ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧ፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከላይ በተገለፀው መሰረት አስተዳደሩ የተከታዩን በጀት ዓመት በተላለፈው የፌደራል መንግሰት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 መሠረት ለገቢው እቅድ ማዘጋጀት እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.9 በገቢ መታየት የነበረበት በተከፋይ ሂሳብ የያዘ መ/ቤት

- በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በድምሩ ብር 457,643,809.64 ከመደበኛው ሂሳብ ጋር ፕሮጀክት ሂሣብ በተከፋይ 5054 በመደበኛ የተመዘገበ የፕሮጀክት ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

አስተዳደሩ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ በተፈቀደለት መሰረት ለፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ የሂሳብ አወቃቀር በማዘጋጀት ወይም ከመደበኛው ሂሳብ ጋር በትክክለኛ የሂሳብ ምዝገባ ስርዓት መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር ተግባራዊ እንዳይደረግ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ለቋሚ ሂሳቦች የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.10 ቦሎ እና ቀረጥ ሳይከፈል ባልተሟላ ማስረጃ የተፈጸመ የተሽከርካሪ ሽያጭ ገቢ፣

አባሪ New finding ቸ

በመንግስት ግዥ አገልግሎት በድምር ብር 14,487,711.44 የቦሎ ግብር እና ቀረጥ የተከፈለበት የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ጨረታ ወጥቶ የተሽከርካሪ ሽያጭ በመፈጸም ገቢ የተሰበሰበ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

አገልግሎቱ ከየመስሪያ ቤቱ የተሰብሰቡ ተሽከርካሪዎችን ሽያጭ ለመፈጸም ጨረታ ከማውጣቱ በፊት በመመሪያው መሰረት የቦሎ እዳቸውንም ሆነ ከቀረጥ እዳ ነጻ መሆናቸው አረጋግጦ መሸጥ ይኖርበታል፡፡ ይህን በደረጉ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ በመውድ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም እንዲህ አይነቱ ስህተት እንዳይደገም ተገቢውን ጥንቃቄና ትኩረት ሊደረግለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4 የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን፣ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙንና የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎችች ተገኝተዋል፡፡

4.1 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ የተገኘባቸው

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 የመደበኛና የካፒታል ሥራ ማስኬጃ ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ሊረጋገጥ እንደሚገባ የተገለጸ ቢሆንም በ10 መ/ቤቶች ብር 7,722,647.08 የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የተሟላ ማስረጃ ሳይኖር የተወራረደበትን ምክንያት በማጣራትና ይህን ባደረጉ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ለኦዲት ያልቀረበውን ማስረጃ ለኦዲት በማቅረብ ለወደፊቱም የተሟላ ማስረጃ መቅረቡ ሳይረጋገጥ ወጪዎች እንዳይመዘገብ አሳስበናል፡፡

4.2 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

ማንኛውም ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት የተሟላ ደጋፊ ሰነዶች መቅረብ እንዳለባቸው የተደነገገ ቢሆንም፡-

- በ2 መ/ቤቶች በድምር ብር 17,544,125.03 የተሟላ ደጋፊ ሰነዶች ሳይቀርቡ በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተወራረደበትን ምክንያት በማጣራትና ይህን ባደረጉ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ለኦዲት ያልቀረበው ማስረጃ ለኦዲት ማቅረብ ለወደፊቱም የወጪ ማስረጃ መቅረቡ ሳይረጋገጥ በወጪ እንዳይመዘገብ አሳስበናል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በመንግስት ታምኖባቸው በወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት የተፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ5 መ/ቤቶች በድምር ብር 3,852,206.43 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ማንኛውም ወጪ የመንግስት መመሪያዎችን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበትና ከደንብና መመሪያ ውጪ እንዲከፈል በፈቀዱና በፈጸሙት አካላት ላይ የእርምት እርምጃ

በመውሰድ ደንብና መመሪያን ሳይከተል አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችን ተመላሽ በማድረግ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገበ አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ</u>

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ብር 3,790.24
- የመንግስት ግዥ አገልግሎት ብር 1,161.92
- የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር ብር 24,439.69

በድምሩ ብር **29,391.85**

በስራ ገበታቸው ለሌሉ ሰራተኞች ክፍያ ተፈጽ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከመመሪያ ውጪ አላግባብ የተከፈለው ደመወዝ እንዲመለስ አሳስበናል፡፡

4.5 <u>በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያ</u>

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ በድምር **39,531,164.69** በመንግስትም ይሁን በሚመለከተው አካል የተፈቀደ የክፍያ ተመን ሳይኖር ለምርጫ ተሳታፊዎች የተከፈለ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለወደፊቱ ማንኛውም ክፍያ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን መሰረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

4.6 <u>በወቅቱ ክፍያ ባለመፈጸሙ አላግባብ የተከፈለ ቅጣት፣</u>

- የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ብር 5,960.40
- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ብር 6,812.34

በድምር ብር 12,772.74

አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

መ/ቤቶች በመመሪያው መሰረት ክፍያዎችን በወቅቱ በመክፍል መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረግ ባደረጉት አካላት ላይ እንዲጠየቁ በማድረግ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.7 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ ሁለት ጊዜ የተመዘገበ ወጪ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ብር 734,284.94 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ ሁለት ጊዜ የተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ ወጪ መሆኑ ታውቋል፣

የማሻሻያ ሀሳብ

በሂሣብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ላይ በድጋሚ ተመዝግቦ ሪፖርት ለተደረገው ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ በመስራት የተስተካከለ የሂሳብ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በሂሳብ አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

4.8 ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

በ5 መ/ቤቶች በድምር ብር 1,965,391,650.20 ለኦዲት ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለኦዲት የሚፈለጉት ሰነዶች አለመቅረባቸው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን የሚጥስና ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለሆነ በበጀት ዓመቱ ሂሳብ ሪፖርት መሰረት የመ/ቤቱ የወጪ ሂሳብ ሰነዶቹ በሙሉ ለኦዲት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.9 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ምደባ የፈጸሙ መ/ቤቶች

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 55 ሰራተኞችን ወደ ቋሚ የስራ መደብ ከተዛወሩት ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ምደባ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ቦርዱ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ሲቀጠር የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዎ መርሆዎች ተከትሎ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በፋይል ውስጥ ሊገኙ በሚገባቸው መረጃዎች ላይ የታየው ክፍተት እንዲስተካከል መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም በአሰራሩ ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.10 ከሚያዝያ በኋላ በቀሩት ሁለት ወራት ውስጥ ግዥ መፈጸም የማይቻል ስለመሆኑ

▪ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት	ብር	17,961,185.75
▪ የፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	ብር	1,687,237.43
▪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	ብር	743,700.05
▪ የመንግስት ግዥ አገልግሎት	ብር	914,126.33
በድምሩ	ብር	21,306,249.56

ከሚያዝያ በኋላ በቀሩት ሁለት ወራት ውስጥ ግዥ መፈጸም መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የሚፈጽማቸው ግዥዎች በዕቅዱ መሰረት ወቅቱን ጠብቆ እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበትና ከመመሪያ ውጭ የተፈፀሙ ግዥዎች ለምን እንደተከናወነ በማጣራት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ በመንግስት ታምኖባቸው የሚወጡ መመሪያው ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.11 በብልጫ የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎች

- በ4 መ/ቤቶች **ብር 129,180.42** በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጠር አሳስበናል፡፡

4.12 ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ

(ውላቸው ከተቋረጠ የሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ)

የቤተ-መንግስት አስተዳደር፡-

- የቅድሚያ ክፍያ የገንዘቡ ልክ/ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ ብር 28,852,886.80 እና
- ውል ካቋረጡ ያልተመለሰ የውል ማስከበሪያ ብር 15,411,224.99 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተመለሰው ቅድሚያ ክፍያ እና ያልተወረሰው የውል ማስከበሪያ ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

4.13 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት በወጣው የግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት መፈጸም እንዳለበት የተደነገገ ቢሆንም፡-

- በ11 መ/ቤቶች ያለጨረታ በቀጥታ የተገዛ በድምር ብር 188,488,167.44 የእቃና አገልግሎት ግዥ የፈጸሙ መሆኑ፤
- በ16 መ/ቤቶች ግልፅ ጨረታ ሳይወጣ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ በማከናወን በድምር ብር 32,263,378.55 የሚያወጡ የእቃና አገልግሎት ግዥ የፈጸሙ መሆኑ፤
- በ1 መ/ቤት በድምር ብር 8,175,411.53 የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ፣
- በ13 መ/ቤቶች የግዥ ስርዓትን ሳይከተሉ በድምር ብር 91,519,724.28 ግዥ የፈጸሙ መሆኑ፤

በጠቅላላ ድምር ብር 320,446,681.80 መመሪያን ያልተከተለ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የመንግስትን ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዳይሆን ለመከላከል እና ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃት እና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ግዥዎች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያው መሠረት በመፈጸም ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.14 በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ የግዥ ክፍያዎች

- የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ብር 4,128,039.56
- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 10,597,804.73

በድምር ብር 14,725,844.29

ንብረቱ ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ማንኛውም የቴክኒክ ፍተሻ የሚያስፈልጋቸው ዕቃ በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ተፈትሸው ጥራታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ ሲቀርብ ክፍያውን መፈጸም ይገባል፡፡ በመሆኑም የገባው

እቃ ለምን በወቅቱ እንዳልተፈተሸ ተጣርቶ እና ተፈትሾ ማስረጃ ሊቀርብ እንደሚገባና ለወደፊቱም እንዲህ አይነት አሰራር እንዳይፈጸም ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.15 ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ ከሚገባቸው ጥንቃቄዎች ውስጥ አንዱ ዕቃው ወደ መስሪያ ቤቱ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡን ማረጋገጥ መሆኑን ይገልጻል፡፡ መ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት …………… ብር 140,875.00
- የቤተ-መንግስት አስተዳደር ……………. ብር 208,688.00
- የመንግስት ኮምኒኬሽን አገልግሎት …… ብር 394,350.00

በ3 መ/ቤቶች በድምር ብር 743,913.00

ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

መ/ቤቶቹ ለመድረሱና ጥቅም ላይ ለመዋሉ ተረጋግጦ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ደረሰኝ እንዲቀርበ አሳስበናል፡፡

4.16 ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተመዘገበ ወጪ የተገኘባቸው

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 4 /2003 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የመደበኛና የካፒታል የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች፣ ወጪ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመሥሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ዕቅድ ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈጸም እንደማይገባ ያዛል፡፡ በመመሪያው መሰረት ክፍያዎች በተያዘለት በጀት ዓመት እየተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ የአገልግሎት ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶች ብር 8,445,860.71 ከበጀት ዓመቱ ውጭ ክፍያ በመፈጸም ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መ/ቤቶች የሚመደብላቸውን በጀት በበጀት ዓመቱ ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ብቻ ማዋል እንዳለበትና ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስስበናል፡፡

4.17 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: መ/ቤቶችን በትክክለኛው የሂሳብ አርዕስት ተጠቅሞ እየመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ19 መ/ቤቶች ከተፈቀደው የሂሳብ አርዕስት ብር 47,185,246.29 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በመ/ቤቶቹ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የምዝገባ ክፍተት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳሰስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ፣

- የፌዴራሉ ሪፐብሊካን ጥበቃ ኃይል ብር 2,217,300.00
- የቤተ-መንግስት አስተዳደር ብር 705,985.25

በድምር ብር 2,923,285.25

በወጪ መመዝገብ ሲገባው በተሰብሳቢ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር አሳስበናል፡፡

4.18 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተፈጸመ ክፍያ

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ 563,999.00 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተፈጸመ ክፍያ ተፍጽሞ ተግኝቷል።

የማሻሻያ ሀሳብ

መ/ቤቱ የሚፈጽማቸው የዱቤ ግዥዎች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ስርዓቱን ተከትሎ ምዝገባውን ማከናወን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.19 ከፕሮጀክት ሂሣብ ከተመን በላይ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ

- የመንግስት ግዢ ባለስልጣን 162,600.00 የፕሮጀክት ሂሳብ ከፕሮጀክት ሂሣብ ከተመን በላይ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ፤

  <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

  ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ ክፍያውን የፈቀዱና የፈጸሙትን አካል ተጠያቂ በማድረግ በብልጫ የተከፈለው የውሎ አበል ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡

4.20 **<u>ያለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ደረሰኝ የተፈጸመ ክፍያ</u>** (**አባሪ** New finding **ሠ**)

በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 26,831,851.34 ያለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ደረሰኝ የተፈጸመ ክፍያ ተፈጽሞ ተግኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለተለያዩ ግዥዎች ለተፈጸሙ ክፍያዎች ህጋዊ የሆነ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ /ካሽ ሬጅስተር ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው በጥገና ወይም በሌላ ምክንያት መስራት አለመስራቱን ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሳይቀርብ በሌላ በማንኛውም ደረሰኝ ለድርጅቱ ክፍያ የተፈፀመበት ምክንያት ተጣርቶ በሚመለከተው የስራ ክፍል ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱም ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ላለበት ድርጅት ክፍያ በሚፈፀምበት ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በጥብቅ ማስገንዘብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.21 **<u>ከመመሪያው በላይ ለስራ ተቋራጭ የተሰጠ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ</u>**

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን 16,618,007.30 ከመመሪያው በላይ ለስራ ተቋራጭ የተሰጠ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ መኖሩ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመመሪያው ከተቀመጠው በላይ የስራ ውል መስጠት ተገቢነት የሌለው አሰራር በመሆኑ መምሪያው ጉዳዩን አጣርቶ ከመመሪያ ውጪ የለውጥ ትዕዛዝ ስራ በፈቀዱና በፈጸሙ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ አሳሰበናል፡፡

4.22 **<u>የቀን ሰራኞች እንደ ኮንትራት ሰራኛ በመቅጠርና በማሰራት የተፈጸመ ክፍያ</u>**

የቤተመንግስት አስተዳደር በድምሩ ብር 13,520,250.17 የቀን ሰራኞችን እንደ ኮንትራት ሰራተኛ በመቅጠርና በማሰራት የተፈጸመ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

አስተዳደሩ በአዋጁ መሰረት ክፍት የስራ መደቦችን በቋሚ ቅጥር ወይም የማይቻል ከሆነ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን ጠይቆ በማስፈቀድ የኮንትራት ቅጥር መፈጸም ሲገባው የቀን ሰራተኞች በሚል እንደ ኮንትራት ወሩን ወይም ዓመቱን ሙሉ ማሰራት ከመመሪያ ውጪ ከመሆኑ በተጨማሪ ባለፉት ዓመታት ተመሳሳይ ግኝት ተገኝቶ እንዲስተካከል አስተያየት ቢሰጥም ያልተስተካከለ በመሆኑ ይህን በፈቀዱና በፈጸሙ አካላት ላይ የእርምት ተወስዶ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

5.1 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001፣ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተከፋይ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከፊደል ሀ-ሠ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እየተከፈሉና እየተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ17 መ/ቤቶች፡-

- በ12 መ/በቶች ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት የቆየ ብር 27,668,994.42
- በ11 መ/ቤቶች ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት የቆየ ብር 247,089,405.67
- በ4 መ/ቤቶች ከ 5 ዓመት በላይ እስከ 10 ዓመት ብር 16,281,372.64
- በ2 መ/ቤት ከ10 ዓመት በላይ የቆየ ብር 268,088,707.17

በአጠቃላይ በድምሩ ብር **559,128,479.90**

በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ የተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑን በኦዲት ታውቋል፡፡

5.1.2 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ የፕሮጀክት ተከፋይ ሂሳብ አባሪ 6/1</u>

- በ2 መ/ቤቶች ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት በድምሩ ብር 12,443,978.09
- በ3 መ/ቤቶች ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት ብር 10,460,115.82
- በ1 መ/ቤት ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ብር 1,090,309.21

በድምሩ ብር

23,994,403.12

በወቅቱ ያልተከፈለ የፕሮጀክት የተከፋይ ሂሳብ_የሚገኝ መሆኑን ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የዕዳ ክምችት እንዳይኖር ተከፋይ ሂሳቦች ለተቋሙ ጥቅም የዋሉ ትክክለኛ ዕዳዎች መሆናቸውን በማረጋገጥ በወቅቱ ለሚከፈለው አካል እንዲከፈል፣ መከፈል የማይቻለውን በማጣራት ከእዳ መሰረዝ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች</u>

5.2.1 <u>በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 37,365,726.19 የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለመ/ቤቶቹ በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ላልቀረበለት ማቅረብ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.3 <u>ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ያልተደረገ ሂሳብ /አባሪ ቸ</u>

5.3.1 <u>ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ</u>

- **በ3 መ/ቤቶች ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ብር 408,087.04**

5.3.2 <u>ያለአግባብ የተመዘገበ ተከፋይ ሂሳብ (አባረ 6/ ቸ)</u>

- በ2 መ/ቤቶች በድምር ብር 23,027,175.36 መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለታዩት የአሰራር ክፍተቶች ተገቢውን ማስተካከያ በመስራት የተስተካከለ ሂሳብ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በሂሳብ አሰራሩ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖረበታል፡፡

5.4 በወጪ መታት የነበረበት በተከፋይ ሂሳብ የሚታይ ፕሮጀክት ሂሳብ መ/ቤቶች

(አባሪ New finding ለ)

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር 64,846,538.71 በወጪ መታየት ሲገባው ከመደበኛው ሂሳብ ጋር 5054 በዴቢት ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

አስተዳደሩ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ በተፈቀደለት መሰረት ለፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ የሂሳብ አወቃቀር በማዘጋጀት ወይም ከመደበኛው ሂሳብ ጋር በትክክለኛ የሂሳብ ምዝገባ ስርዓት መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር ተግባራዊ እንዳይደረግ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ለቋሚ ሂሳቦች የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

5.3 የፕሮጀክት ወጪን ከመደበኛ ሂሳብ ጋር 5054 በተከፋይ ሂሳብ የያዘ መ/ቤት

(አባሪ New finding ለ)

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር 144,455,549.86 የፕሮጀክት ወጪን ከመደበኛ ሂሳብ ጋር 5054 በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ።

የማሻሻያ ሀሳብ

አስተዳደሩ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ በተፈቀደለት መሰረት ለፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ የሂሳብ አወቃቀር በማዘጋጀት ወይም ከመደበኛው ሂሳብ ጋር በትክክለኛ የሂሳብ ምዝገባ ስርዓት መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር ተግባራዊ እንዳይደረግ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ለቋሚ ሂሳቦች የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

6. በጀት ሂሳብ

6.1 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት /ከ10% በላይ ልዩነት ያለው

- በ26 መ/ቤቶች ከመደበኛ በጀት በድምር ብር 2,427,257,911.25
- በ10 መ/ቤቶች ካፒታል በጀት በድምር ብር 7,842,381,149.22

በጠቅላላው በድምሩ ብር 10,276,505,456.04

ሥራ ላይ አለመዋሉ በጀት ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለወደፊቱ በጥናትና በመረጃ የተደገፈ የበጀት ዕቅድ እንዲዘጋጅ ቢደረግ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ሊረዳ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የተደለደለውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል እንዲቻል በበጀት አጠቃቀምና አፈፃፀም ላይ ተገቢው ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6.2 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ የመ/ቤቶች ዝርዝር

• በ6 መ/ቤቶች ከመደበኛ በጀት	ብር	99,100,460.57
• በ1 መ/ቤቶች ካፒታል በጀት	ብር	13,646,398.70
በድምር	ብር	**112,746,859.27**

በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ከተመደበው በጀት በላይ ወጪ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለመ/ቤቶች ከጸደቀላቸው በጀት በላይ ወጪዎችን እንዳይፈጽሙ ከፍተኛ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት መጠቀም ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

7. የዕቃና ንብረት አስተዳደር

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት በታዘዘው መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

7.1.1 ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ

4 መ/ቤቶች ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ መሆኑን፣

7.1.2 በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች

በ2 መቤቶች የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መሆኑ፣

7.1.3 ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ መ/ቤቶች

በ1 መ/ቤቶች ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ መሆኑ፤

7.1.4 <u>የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ያላደረጉ መ/ቤቶች</u>

በ3 መቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ያላደረጉ መሆኑ፣

7.1.5 <u>የቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ መቀመጣቸው፣ /አበረ 8/1 ዘ</u>

በ6 መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ መቀመጣቸው በኦዲት ታውቋል፡፡

7.1.6 <u>ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ /አባሪ 8/1 ረ</u>

በ4 መ/ቤቶች ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ፣

7.1.7 <u>ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች</u>

በ7 መ/ቤቶች ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች መገኘታቸው፡፡

7.1.8 <u>አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው</u>

በ21 መ/ቤቶች አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፤

7.1.9 <u>ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰው ተደርበው የሚከናወኑባቸው</u>

በ2 መ/ቤቶች ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰው ተደርበው የሚከናወኑ መሆኑ፤

7.1.10 <u>የለቀቁ ሰራተኞች (ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸው</u>

በ5 መ/ቤቶች 48 የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎችና ኮምፒተሮች፣

7.1.11 <u>ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች</u>

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የተለያዩ በርካታ ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና በአግባቡ ያላስወገዱ ተገኝቷል፡፡

7.1.12 በጉድለት የተገኙ ንብረቶች

በ2 መ መ/ቤቶች በ 7 የተለያዩ ኮምፒውተር እና እቃዎች በጉድለት የተገኙ መሆኑ፣

7.1.13 ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞችን በተመለከተ

በገንዘብ ሚኒስቴር 2 ሰራተኞች የተሟላ ዋስትና ያላቀረቡ መሆኑ።

7.14 የንብረት ምዝገባ በኢፍሚስ ሲስተም እንዲመዘገብ ያላደረጉ መሥሪያ ቤቶች

በ2 መ/ቤቶች የንብረት ምዝገባ በኢፍሚስ ሲስተም እንዲመዘገብ ያላደረጉ መሥሪያ ቤቶች፤

የማሻሻያ ሀሳብ

መ/ቤቱ መንግስት ያወጣውን የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ከላይ ለተመለከቱት የአሰራር ግድፈቶች ተገቢ የሆነ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ሊወገዱ የሚገባቸውን ንብረቶች በመለየት ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር እንዲወገዱ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

7. 2 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

የንብረት አያያዝ አጠቃቀም እና አስተዳደር በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መሆኑን የተሽከርካሪዎች የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ተገኝቷል፡፡

- **ሊብሬ ያልቀረበላቸው**
- በ5 መ/ቤቶች በድምር 16 ተሽከርካሪዎች ሊብሬ የላቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

7.2.1 በብልሽት ምክንያቶች የቆሙና በወቅቱ ያልተጠገኑ ተሽከርካሪዎች

በ21 መ/ቤቶች 111 ተሽከርካሪዎችና እና 25 ሞተር ሳይክል በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ፤

7.2.2 ሻንሲ ቁጥር የሌላቸው

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 1 ተሽከርካሪ ተገኝቷል፡፡

7.2.3 <u>የሞተር ቁጥር የሌላቸው ተሽከርከሪዎች የተገኙበት መ/ቤት (አባሪ 35.መ)</u>

በ2 መ/ቤቱች ብዛት 2 ተሽከርካሪዎች ተገኝተዋል፡፡

7.2.4 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ</u>

በ7 መ/ቤቶች 190 ተሽከርካሪዎች ተገኝተዋል፡፡

7.2.5 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው ሞተር መካከል ልዩነት ያለ መሆኑ፣</u> (<u>አባሪ 8/2.ረ)</u>

የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው ሞተር መካከል ልዩነት ያለ መሆኑ።

7.2.6 <u>የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ</u>

በ3/መቤቶች ብዛት 8 የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

7.2.7 <u>አገልግሎት የማይሰጡ/መወገድ/ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች</u>

በ6 መ/ቤቶች 71 አገልግሎት የማይሰጡ/መወገድ/ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች የተገኙ መሆኑ፣

7.2.8 <u>የተሽከርካሪ ነዳጅ አጠቃቀም የተስተዋሉ ችግሮች (አባሪ 8/2 ቸ)</u>

በ3 መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ነዳጅ አጠቃቀም የተስተዋሉ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

7.2.9 <u>የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ያልቀረበ በመሆኑ ምክንያት የነዳጅ ወጪ አጠቃቀም አግባብነት ማጣራት ያልተቻለ</u>

በ 2 መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ያልቀረበ በመሆኑ ምክንያት የነዳጅ ወጪ አጠቃቀም አግባብነት ማጣራት ያልተቻለ፣

7.2.10 <u>በመድኃኒት ገቢ ደረሰኝ ገቢ መሆን ሲገባው በንብረት ገቢ ደረሰኝ(ሞዴል-19) ገቢ የተደረገ የመድኃኒት ግዥዎች</u>

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጤና ዋና መምሪያ ብር 34,221,907.38 በድምሩ ብር የሚወጣ መድሀኒት በመድሃኒት ገቢ ደረሰኝ ገቢ መሆን ሲገባው በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል-19) ገቢ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በተጠቀሱት መ/ቤቶች የሚታዩ የተሽከርካሪ አያያዝ፤ የመጽሐፍት አጠቃቀምና አያያዝ፤ አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት እንዲያስተካክሉ እንዲሁም የመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም በዓለም ጤና ድርጅት ስርዓት መሰረት እንዲሆን አሳስበናል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች

የውስጥ ቁጥጥር ክፍተት የታየባቸው መ/ቤቶች

- የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለስልጠን
- የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት ጂማና ሚዛን ቅርንጫፍ

የማሻሻያ ሀሳብ

የተስተዋሉ የውስጥ ቁጥር ስርዓቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል፡፡

በህንጻ አስተዳደር፤ ርክክብና እድሳት ላይ የታዩ ችግሮች (አባሪ 8.4)

- የአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ

የማሻሻያ ሀሳብ

በህንጻዎች አስተዳደር፤ ርክክብና እድሳት ላይ የሚታዩ ክፍተቶች በአስቸኳይ እንዲስተካከሉ አሳሰበናል፡፡

8 ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ

በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች፣ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት እርምጃ መወሰዱን ማጣራት ሲደረግ፡-

8.1 ከመመሪያ ውጪ ያለአግባብ ተከፍሎ ተመላሽ ያልተደረገባቸው ገንዘብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በ18 መ/ቤቶች ብር 36,156,668.33 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡፡ እና በ2 መ/ቤት ዶላር $175.43 ለተለያዩ የውጭ ሃገር ጉዞ ከወሰዱት ገንዘብ ላይ በብልጫ የተከፈለና ተመላሽ አለመደረጉ፡

8.2 የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያት ቢሰጥም ያላቀረቡ መ/ቤቶች

በ6 መ/ቤቶች በድምር ብር 10,531,853.14 የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያት የተሰጠ ቢሆንም ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት በወቅቱ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ በስራ አመራሩ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

3.2 ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች

የተጠቃለለ ሪፖርት

(አባሪ -1)

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

1.1 የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር /በዕቅዱ መሰረት ያልተከናወነ ስራ ካለ ምክንያቱ ይገለፅ/

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			መግለጫ
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር	
1	የገቢዎች ሚኒስቴር		3,729,807,015.76		3,729,807,015.76	
2	የጉምሩክ ኮሚሽን		1,379,856,634.05		1,379,856,634.05	

1.2 <u>የተሰጠው የኦዲት አስተያየት</u>

ተ.ቁ	የኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የተሰጠው የኦዲት አስተያየት			
		ነቀፌታ የሌለበት Clean Opinion	በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion)	የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse opinion/	ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቸለባቸው መ/ቤቶች (Disclaimer opinion)
1	የገቢዎች ሚኒስቴር		✓		
2	የጉምሩክ ኮሚሽን		✓		

1.3 <u>ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች</u>

ሀ/ <u>ፋይናንሻል ኦዲት</u>

1. የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ

1.1. የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የፌደራል መንግስት የሂሰብ አያያዝ መመሪያ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ማለትም በሰኔ 30/2015 በጀት ዓመት እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- መደበኛ ሚዛኑ ያልጠበቀ የተጣራ ሀብት ክሬዲት መያዝ ሲገባው በሂሳብ ሪፖርት ላይ በዴቢት ተመዝግቦ የሚታይበት በገቢዎች ሚኒስቴር ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 79,590,839.45 ስለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

  (ዝርዝሩን በአባሪ ከአባሪ-2/1 እና 2/4ይመልከቱ/

  የሂሳብ መደብ ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ እና ወደ ማጠቃለያው በትክክል ያልዞረበት ምክንያት ሊጣራና የሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. ተሰብባሰቢ ሂሳብ

2.1. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ በቆይታ ጊዜው /በእድሜው/ የተተነተነ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ እንደሚሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- *በ 13 ቅ/ጽ/ቤቶች* እና በ2ቱ ዋና መ/ቤቶች ሳይሰበሰብ የቆየ ብር **34,989,279.48** ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታይቷል፡፡ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው፣

ተ.ቁ	የቆየበት ጊዜ	የገንዘቡ መጠን
1	ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት	13,986,475.27
2	ከ 1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	11,368,594.35
3	ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት	3,141,484.45
4	ከ10 ዓመት በላይ	6,358,077.01
5	በቆይታ ጊዜ ያልተተነተነ	77,746.53
	ድምር	34,932,377.61

(ዝርዝሩን በአባሪ 3/1 ይመልከቱ)

2.2. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳቦች የዴቢት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም በጅማ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የተመለከተው የመዝጊያ ሚዛን (Ending Balance) የተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ቋት ላይ ብር **36,994.12** ሚዛኑን ያልጠበቀ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፡፡

መሰብሰብ የሚገባውም የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ መሰብሰብ የሚኖርበት ሲሆን ማስረጃ የሌለውና ሊሰበሰብ የማይችል ሂሳብ ከሆነ በፋይናንስ ህግና ደንቡ መሰረት ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሥራ አመራር ሪፖርት ገልጸናል፡፡

3. የገቢ ሂሣብ

3.1. ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ፣በቆይታ ጊዜው /በእድሜው/ለስንት ዓመት ወይም ለምን ያህል ጊዜ ሳይሰበሰብ እንደቆየ የተገለጸ፣

በተለያዩ አካላት ማጣራት መሰረት የተገኘ ያልተሰበሰበ የመንግስት ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ለመሰብሰብ ቅ/ጽ/ቤቶቹ እየሰሩ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በየቅ/ጽ/ቤቱ በ 2015 በጀት ዓመት የታየው የእዳ መጠን እና በባለፉት አመታት እንዲሰበሰብ ተብሎ በዋና ኦዲተር መ/ቤት አስተያየት የተሰጠበት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ሳይሰበሰብ የቆየ እና በተለያየ ሂደት የሚገኝ፣

የ2015 በጀት ዓመት፡-

- የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ***በ 8 ቅ/ጽ/ቤቶች*** በድምሩ ብር **3,108,197,669.27** መኖሩ፣
- ***በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች*** በተለያየ ሂደት የሚገኝ የግብር ዕዳ ብር **1,382,842,703.34** በድምሩ 4,491,040,372.61 መኖሩ፣

2014 እና ከዚያ በፊት ያሉ

- የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ***በ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች*** በድምሩ ብር **11,531,792,165.35** መኖሩ፣
- ***በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች እና አዲስ ወደተቋቋመው ቅ/ፅ/ቤት*** *የተዛወረውን ዕዳ ጨምሮ* በተለያየ ሂደት የሚገኝ የግብር ዕዳ ብር 6,866,146,945.24 በድምሩ 18,397,938,660.59 መኖሩ፣

በጠቅላለው በድምሩ ብር 22,888,979,033.20 ከአንድ ኣመት እስከ 6 ዓመት እድሜ ያለው ውዝፍ እዳ መኖሩን ለማየት ተችሏል::

የየቅ/ጽ/ቤቶቹ ዕዳ ክትትል ቡድንና የመ/ቤቶቹ እዳ ክትትል ዳይሬክቶሬት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ግብር ከፋዮች ላይ ያለባቸውን ዕዳ ለመሰብሰብ ቀጣይ እርምጃቸውን በመውሰድ ውዝፍ ዕዳውን ሊሰበስቡ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.2. በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ

በገቢ ግብር አዋጅ ፣በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣በኤክሳይዝ አዋጅ፣ በጉምሩክ አዋጅ ፣ በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም በወጡት ደንብና መመሪያዎች መሰረት የመንግስት ገቢ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መሰብሰብ ቢኖርበትም **በ20 ቅ/ጽ/ቤቶች** ግን በአዋጆቹና ና በመመሪያዎቹ መሰረት በትክክል ባለመሰራቱ ብር 1,614,625,781.60 ያልተሰበሰበ ገቢ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳቡ ያልተሰበሰበበት ምክንያትም፡-

- የመጫኛ/ማራገፊያ፣ የባህር ትራንስፖርት፣ የየብስ ትራንስፖርት እና የኢንሹራንስ ወጪ በትክክል በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ እንዲሁም ማስረጃ ባለመቅረቡ ፣
- በማህበራዊ ልማት ደንብ መሰረት ባለመሰብሰቡ፣
- በግብይት ዋጋ(FOB) ላይ የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ(marine insurane) ወጪ ባለመደመሩ፣
- የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ከጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS) አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ ከ10 በመቶ በላይ በመሆኑ ፣
- በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለበት የትራንስፖርት ወጪ በአግባቡ ባለመካተቱ፣
- በትክክለኛ የቀረጥና ታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ፣
- ዕቃው በዲክላራሲዮን ላይ በተመዘገበበት ቀን በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት ባለመሰላቱ ፣
- የእርጅና ቅናሽ በትክክለኛው ምጣኔና ስሌት አለመሰራቱ፣
- የዕቃው ዋጋ በዕቃዎች አካላዊ ፍተሻ ሪፖርት መሰረት ባለመሰራቱ፣

- በ2014 ዓ.ም በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ካሳወቁት ልዩነት ያለው በመሆኑና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ፣

- ከ2013 የግብር ዘመን መዞር ያለበት ያልተሸጠ ወይም በምርት ሂደት ላይ ያለ ዕቃ/ending inventory ወደ 2014 የግብር ዘመን በሚዞርበት ጊዜ ከፍ እንዲል በመደረጉ፣

- ተቀናሽ መደረግ የማይገባቸው አግባብነት የሌላቸው ወጪዎች ከገቢ ላይ ተቀናሽ በመደረጋቸው ፣

- ያልተከፈለ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር በመኖሩ፣
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ግብር ከፋዮች ተቀናሽ የተደረገው ቅድመ ግብር በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት የተፈጸመ ባለመሆኑ፣

- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በሚቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረት የሽያጭ ገቢያቸውን ባለማስታወቃቸው፣

- በአግባቡ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በመኖሩ፣
- በኢት ዮጵያ ነዋሪነት ከሌላቸው ባለሙያዎች ክፍያ ላይ ግብሩ ተቀንሶ ቀሪ ባለመደረጉ፡
- በተዕታ ማስታወቂያ ላይ ባሳውቁት መሰረት የተጨማሪ ዕሴት ታክሳቸውን እንዲከፍሉ ባለመደረጉ፣፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የሀገር ውስጥ ግብር እና ቀረጥ ታክስ ወለድና መቀጫን በመጨመር ከአስመጪዎችና ግብር ከፋዮች መሰብሰብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡ ለወደፊቱም ቅ/ጽ/ቤቶቹ በአዋጆቹን ደንቦቹ መሰረት ለመስራት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን አስገንዝበናል፡፡

3.3. በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች

የመንግስት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- በግብር ከፋዮች ወይም በአስመጪዎች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ወይም የቀረጥና ታክስ ዕዳ ውሳኔ አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ዕዳ በ3 ቅ/ፅ/ቤቶች ብር 31,511,026.23 እንዲሁም በዋና መ/ቤት ፍርድ ቤት እና በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ላይ ያለ ብር 378,929,904.84
- በ6 ቅ/ጽ/ቤ/ቶች ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያላሳወቁ 122 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ኤክሳይስ ታክስና ተርኦቨር ታክስ በወቅቱ ያላሳወቁ 284 ድርጅቶች መገኘታቸው፣
- በሞጆ እና አዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶት በኩል ወደ ሀገር የገባው ዕቃ ቀረጥና ታክሱ የተሰላ ቢሆንም ክፍያ ሳይፈጸምበት ወይም ሳይሰረዝ የቆየ(assessed but not paid) ብር **16,135,323.73** <u>መገኘቱ</u>
- በአዳማ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ወደ ሀገር የገባው ዕቃ የተመዘገበ ቢሆንም ቀረጥና ታክሱ የተሰላ የቆየ(Regiter but not assessed) ብር 514,882.65 መገኘቱ
- በቫውቸር ሥርዓት ከቀረጥ ነጻ ገብተው በጊዜ ገደቡ ምርት ላይ ስለመዋሉና ምርቱም ለውጭ ገበያ የቀረበ ስለመሆኑ ክትትል ያልተደረገበት አስቀድሞ በቫውቸር የተመዘገበው የቀረጥና ታክስ መኖሩ፣
- በአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽቤት እቃው የተወረሰበት፣ እንዲሁም የተወገደበት ማስረጃ ሳይኖር በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የዕቃው ግምታዊ ዋጋ 2,445,750.00 ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ የተደረገ መሆኑ፡

ታውቋል፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም ከላይ የተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1. ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለ አግባብ በብልጫየተፈፀሙ ክፍያዎች

የአገልግሎትም ክፍያዎች በጀት ተይዞለት እና ለመ/ቤቱ አላማ የሚውል መሆኑን ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገበት በከፍተኛ ደረጃ ውጤት ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን፣ የውሎ አበል በሚከፈልበት ወቅት ተገቢው ፎርም እየተሞላና በተመኑ መሰረት መከፈሉን የወሮታ አበል በመመሪያውና ገቢ በሆነው የዕቃ ዋጋ መሰረት መሆኑን፣ ለዕቃ ግዥ የሚፈጸመው በውድድር አነስተኛ ዋጋ ባቀረበው መጠን መከፈሉን፣ መመሪያው በሚያዘው መሰረት የውሎ አበል ክፍያ የሚፈጽም መሆኑን፣ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጉምሩክ ኮሞሽን ዋና መስሪያ ቤት እና ጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶት በተለያየ ምክንያት በብልጫ የተከፈለ ብር 49,175,506.74 መገኘቱ፣

4.2. ሌሎች የወጪ አፈፃፀም የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሲታይ

- በ4ቅ/ፅ/ቤቶችና በ1ዋና መ/ቤት የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር 981,500 መኖሩ፣
- በጉምሩክ ኮሚሽን አዋሽ ቅርንጫፍ ማስረጃ ሳይኖር የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ የክፍያ ሂሳብ ብር 2,445,750.00፣
- በ7 ቅ/ፅ/ቤቶችና በ2ቱም ዋና መ/ቤቶች በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸመ ክፍያ ብር 8,690,239.54፣
- በ1 ቅ/ፅ/ቤት በፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቀድ የተፈፀመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 40,602.75 መኖሩ፣
- በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት አላግባብ የተወረሰ ተሽከርካሪን ለባለቤቱ እንዲመልስ በፍርድ ቤት የተሰጠው ጊዜ ገደብ በማለፉ

ፍርድ ቤቱ የተሸከርካሪውን ግምታዊ ዋጋ እንዲያቀርብለት ለጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መ/ቤት በጠየቀው መሰረት በአዲስ ተሸከርካሪ ከፍተኛ ዋጋ ቀረጥና ታክስን ጨምሮ ዋጋ በመስጠቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብር 10,070,064.95 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣ ስለዚህ ተሸከርካሪ ባገኘነው መረጃ መሰረት ባለንብረቱ በጨረታ ከመንግስት ተቋም በ150,000 ብር የተገዛ መሆኑ፣

- በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በመደበኛ የስራ ሰዓት መሰራት ሲኖርበት በትርፍ ሰዓት በማሰራት የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 346,545.81 መኖሩ፣
- በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተፈፀመ ግዢ ብር 2,342,485.08 መኖሩ፣
- በ5 ቅ/ፅ/ቤቶችና በ1 ዋና መ/ቤት የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ ብር 7,570,847.33 መኖሩ፣
- በ2 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ክፍያ የተፈፀመና የተወራረደ ሂሳብ ብር 1,450,920.41 መኖሩ

4.3. የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ግዢዎች የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስተር ባወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ያለጨረታ በቀጥታ፣ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 1,915,087,938.49 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 14,507,024.77 በድምሩ ብር 1,929,594,963.26 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ መፈጸሙ ታውቋል፡፡

- በ2 ቅ/ፅቤቶች በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ የግዥ ክፍያ ብር 39,052,659.24 መኖሩ፣

በመሆኑም ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያከናውኑትን ግዥ በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ማከናወን ያለባቸው መሆኑንና ወጪዎችን ፀንተው ባሉ

ህጎችና መመሪያዎችን ተከትለው እንዲፈፅሙ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ

5.1. ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ / በቆይታ ጊዜው የተተነተነ/

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀፅ 5 ከሀ እስከ ሠ የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ በተከፋይ መያዙን፣ በጊዜ ቀነ ገደቡ መሰረት ያልተወራረዱት በቂ ማስረጃ ሲቀርብ በመዝገብ እና በሌጀር በተከፋይ መያዝ የሚገባ መሆኑን እና የተከፋይ ሂሳብ ክምችት እንዳይኖር መወራረድ እንዳለበት በሚገልጸው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶችና በ1 ዋና መ/ቤት ሰኔ 30/2014 ሳይወራረድ፡-

• ከ1ወር እስከ 1ዓመት እድሜ ያለው በድምር	ብር	**294,539.40**
• ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት እድሜ ያለው በድምር	ብር	4,862,888.68
• ከ5 እስከ 10ዓመት እድሜ ያለው በድምሩ	ብር	2,049,792.45
• ከ10 ዓመት በላይ እድሜ ያለው በድምሩ	ብር	183,384.63
በጠቅላላው በድምሩ	ብር	7,390,605.16

ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርትም በተከፋይነት የተያዙ ሂሳቦች ላይ ወቅታዊ ክትትል በማድረግ የማወራረድ ስራ ሊሰራ የሚገባ መሆኑንና ተከፋይ ያልሆኑ ሂሳቦች ካሉ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግእንደሚገባ አሳስበናል፡፡

6. የዕቃና ንብረት አስተዳደር

6.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት

የንብረት አስተዳደርን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት ተገዝተው ወደ መ/ቤቶች የገቡ ንብረቶችን በትክክል መግባታቸውን፣ ወጪ

መደረጋቸውን እና ምዝገባ መኖሩን የሚያሳይ መዝገብ መቋቋሙን እንዲሁም ንብረቶቹ በአግባቡ መጠበቃቸውን እና ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ንብረት ቆጠራ ተደርጎ የመንግስት ንብረት ለመጠበቅ የተሟላ የቁጥጥር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በየቅ/ጽ/ቤቶ የንብረት አያያዝ ክፍተቶች የታዩ መሆናቸው በሚከተለው ሁኔታ ተዘርዝረዋል፡፡

- አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች(ተሽከርካሪን ጨምሮ) በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው 12 ቅ/ጽ/ቤቶች፣
- የተተዉ፣ የተወረሱ እና ያልተወረሱ በህግ ሂደት ላይ ያሉ የተለያዩ ዕቃዎችና አስተዳደር እና ቁጥጥር ደካማ የሆነባቸው 8 ቅ/ጽ/ቤቶች፣

መሆናቸው ታውቋል፡፡

የሚወገዱ ንብረቶችን በአግባቡ እንዲወገዱ ጥረት ማድረግና የንብረት አያያዙም መመሪያን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ አስተማማኝ የሆነ የንብረት አያያዝ ስርዓት እንዲኖር መስራት ያለባቸው መሆኑን በላክነው ሪፖርት ገልጸናል፡፡

6.2 በ9 ቅ/ፅቤቶች የተተዉና የተወረሱ 636 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣

7. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ

በባለፉት በጀት ዓመታት በተገኙ ግኝቶች ላይ ለተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ***በአባሪ 36*** ባሉት ግኝቶች ላይ እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል፡፡

በኦዲት ሪፖርት የተሰጡትን የኦዲት ግኝቶች ላይ በድርጊት መርሃ ግብር መሰረት መስተካከል ያለበት እንዲስተካከል መሰብሰብ ያለበትንም መሰብሰብ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3 በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ

መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም እንዲሁም በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1146/2011 ዓ.ም ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን እና መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት ለገንዘብ ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ ሃያ ሰባት ዩኒቨርሲቲዎች እና አንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር የሚገኙ ሶስት ኮሌጆች፣ ሁለት ኢንስቲትዩት እና አንድ ሆስፒታል ሂሣብን ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሰረት የአሥራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች እና የአንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የኦዲት ሥራቸው ተጠናቆ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን ዩኒቨርሲቲዎቹ ምላሽ ከሰጡ እና የመወጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ ለሆኑት የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር ለሚገኙ ስድስት ተቋማት ደግሞ የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት ብቻ እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰባት በአማራ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ሥራቸው የተቋረጠ በመሆኑ (ዝርዝራቸው በአባሪ ተያይዟል) በዚህ የተጠቃለለ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተቱ አልተደረገም፡፡

I. **የተሰጠው የኦዲት አስተያየት**

የኦዲት ሥራቸው ለተጠናቀቁ ሂሳብ አቅራቢ ተቋማት የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ3 ዩኒቨርሲቲ፤ ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሒሳባቸው አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠው ለ1 ዩኒቨርሲቲ፤ ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት

አስተያየት ደግሞ ለ16 ዩኒቨርሲቲዎች እና ለ1 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተሰጥቷቸዋል። ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል።

II. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2015 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል።

1 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ

1.1. በሂሳብ መግለጫው ላይ ለረጅም ዓመታት የሚታይ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ

1.1.1. ግኝት

የፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 34 ቁጥር 1/ሀ በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጭ ቀሪ ሆኖ በካዝና ውስጥ በጥሬ ገንዘብ ከተቆጠረው ሂሳብ ውስጥ የዲፖዚት ገንዘብ፤ የእርዳታና የብድር ገንዘብ ካለ ተቀንሶ በተራፊነት የሚገኝ ሂሳብ እንዲሁም በተራ ቁጥር 2 በመንግስት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም አይነት ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በህግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት አመቱ ውስጥ በየግዜው ለማዕከላቱ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ በፈሰስ ገቢ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል። ሆኖም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በሂሳብ መግለጫው ላይ ምክንያቱ የማይታወቅ ብር **110,444.01** የሚታይ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል።

1.1.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ሂሳቡ ከመነሻው በጥልቀት እና በጥንቃቄ ተጣርቶ ገንዘቡ ከሚመለከተው ሰራተኛ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ወይም በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተደግፎ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራለት መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

1.2. በክፍያ መመሪያው መሰረት በቼክ/በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ መከፈል ሲገባው በጥሬ ገንዘብ የተፈጸመ ክፍያ

1.2.1. ግኝት

የቀድሞው የገንዘብ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታኅሳስ 2003 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003፤ ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር እሂመ 39/7/22፤ ጥቅምት 28 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር እሂመ 39/7/23 እንዲሁም ህዳር 15 ቀን 2012 በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/46 ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ከብር 5,000.00 ብር በላይ የሆኑ ወጪዎች መከፈል ያለባቸው በቼክ/ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመጠቀም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል። ሆኖም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በበጀት ዓመቱ በናሙና ከታዩት ወጪዎች ውስጥ ከብር 5,000.00 በላይ እስከ ብር 50,000.00 ድረስ ለተለያዩ ግዥዎችና አገልግሎቶች የተፈጸሙ ክፍያዎች ብር 149,846,00 በቼክ/ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመጠቀም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ መፈጸም ሲገባቸው በግዥ ሰራተኞች ሥም ቼክ እየተዘጋጀ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል። አሰራሩ ኮሌጁ ህጉን ተከትሎ የመፈጸም ክፍተት ያለበት መሆኑን ከማሳየቱም በተጨማሪ ሁኔታው የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ መንገድ የሚከፍት መሆኑን ያሳያል።

1.2.2. የማሻሻያ ሃሳብ

በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ ላልተገባ ዓላማ እንዲውል ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ተቋማቱ መንግሥት የዘረጋውን የክፍያ ሥርዓት እንዲተገብሩ እንዲሁም የገንዘብ ዝውውሩን ለመቆጣጠር መንግሥት ያወጣው መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል።

2 የገቢ ሂሳብ

2.1. ከክፍያ ሰርተፊኬቱ ላይ የተቀነሰው የቅጣት ሂሳብ ባንክ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት ስለመሆኑ

2.1.1. ግኝት

የፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 21/2 ገንዘብ ለመሰብሰብ ውክልና የተሰጠው ሰው የመንግስት ገንዘብ ሕጋዊ የገቢ ደረሰኝ ለከፋዩ መስጠት እንዳለበት ተመልክቷል። ሆኖም የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ ኮንትራክተሮች በውሉ መሰረት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ከክፍያ ሰርተፍኬቱ ላይ ለቀነሰው ቅጣት ብር **750,000.00** ባንክ ያልገባና ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል።

2.1.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮንትራክተሮቹ በውሉ መሰረት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ከክፍያ ሰርተፍኬቱ ላይ የተቀነሰው ቅጣት ድርጅቶቹ በዩኒቨርሲቲው የባንክ ሂሳብ ገቢ ለማድረጋቸው የባንክ ገቢ ደረሰኝ ማቅረብ እንዳለባቸው፤ የባንክ ገቢ ደረሰኝ ማቅረብ ካልቻሉ ከድርጅቶቹ ላይ ተሰብስቦ ወደ መንግስት ባንክ ሂሳብ ገቢ ተደርጎ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት እናሳስበናል።

2.2. የትምህርት ጊዜያቸውን አጠናቀው ወደ ሥራ ገበታቸው ባልተመለሱ መምህራን ላይ እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

2.2.1. ግኝት

ህዳር 2007 ዓ.ም የፐብሊክ ስርቪስና የሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር ያወጣው የትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 6 አንቀጽ 6.2(12) ላይ የአገልግሎት ግዴታውን ሳያጠናቅቁ በራሱ ፍቃድ መሥሪያ ቤቱን ቢለቅ በትምህርት እና ሥልጠና ወቅት መሥሪያ ቤቱ ያወጣውን ወጪ በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ከነወለዱ መክፈል እንዳለበት መመሪያው ይደነግጋል።

በዚህ መሰረት የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ለሥልጠና የላካቸው ባለሙያዎች በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በዩኒቨርሲቲው እስፖንሰርነት ለትምህርት በሀገር ውስጥ እና በወጪ ሐገር ዩኒቨርሲቲዎች የፒኤችድ እና የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ዕድል ካገኙት ሰራተኞች ውስጥ አስራ አንድ ሰራተኞች በገቡት የውል የጊዜ ገደብ ውስጥ ትምርታቸውን አጠናቅቀው ወደ ሥራቸው ያልተመለሱ በመሆኑ ውል የገቡበት ክፍያ ይኸውም፡-

1. በዋናው ግቢ ብር 1,951,346.00፤
2. በጅግጅጋ ሼክ ሀሰን ኮምፕሬሂንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 2,082,868.00፤

በጠቅላላ ብር 4,034,214.00 እንዲከፍሉ ወይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። ሁኔታው በውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓቱ ላይ ያለውን ክፍተት ከማመልከቱም በተጨማሪ የኒቨርሲቲው በሥልጠናው ሊያሳካ ያሰበውን ግብ እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን ችሏል።

2.2.2. የማሻሻያ ሃሳብ

መምህራኖቹ ትምህርታቸውን አጠናቀው ያልተመለሱበት ምክንያት በተጨባጭ ማስረጃ ተጣርቶ በገቡት የውል ግዴታ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ዕድል የሰጣቸው ሰራተኞች ተገቢው ውል ለመፈረማቸውና ትምህርታቸውን አጠናቀው ለመመለሳቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

3. የወጪ ሂሳብ

3.1. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

3.1.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለወጪ ሂሳቦች ተገቢ የሆነ የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መቅረቡን

ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአራት ተቋማት የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 7,751,496.82 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው (የኮሌጁ) ስም	የገንዘቡ ልክ
1.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	772,329.00
2.	የቀብሪደሐር ዩኒቨርሲቲ	642,682.00
3.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	620,000.00
4.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	5,716,485.82
	ጠቅላላ ድምር	7,751,496.82

3.1.2. የማሻሻያ ሃሳብ

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ ለተመዘገቡ ሒሳቦች የተሟላ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ ለወደፊቱም በክፍያ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.2. የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

3.2.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት መሥሪያ ቤቶች የፈጸሙት ክፍያዎች በወጪ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከሶስት ተቋማት በጠቅላላው ለብር 5,703,029.60 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ የመዘገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝራቸው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ሥም	የገንዘቡ ልክ
1.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ	734,620.00
2.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	561,645.00
3.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	4,406,764.60
	ጠቅላላ ድምር	5,703,029.60

3.2.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ለክፍያዎች የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በተጨማሪ የወጪ የሂሳቡን ተዓማኒነት ሊያሳጣ የሚችል በመሆኑ የወጪ ማስረጃ ላልቀረበላቸው ክፍያዎች የወጪ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.3. ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸሙ ክፍያዎች

3.3.1. ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የፈጸሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መሰረት አድርገው የፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ሶስት ተቋማት የወጡትን ህጎች ሳይከተሉ ለተለያዩ ክፍያዎች ብር 1,800,779.32 ክፍያ የፈጸሙ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው (የኮሌጁ) ስም	የገንዘቡ ልክ
1.	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	1,156,500.00
2.	የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	224,279.32
3.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	500,000.00
	ጠቅላላ ድምር	1,800,779.32

3.3.2. የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች የፈጸሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ካልተከተሉ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና በውስጥ ቁ"ጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር

ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቶች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው እና አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችም ተመላሽ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3.4. <u>ከሥራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ</u>

3.4.1. <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ተራ ቁጥር 10 የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ አከፋፈል ደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ/ወጪ ከመደረጉ በፊት መከናወን ካለባቸው ጥንቃቄዎች አንዱ ንዑስ ቁጥር 5 በጡረታ፣ በሞትና በሌሎች ምክንያት ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር መውጣት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በመመሪያው መሰረት ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞች ደመወዝ ከለቀቁበት ቀን ጀምሮ እንዳልተከፈላቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአራት ተቋማት ከሥራ ለለቀቁ ሰራተኞች ያልሰሩበት ደመወዝ ብር **118,663.40** ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው (የኮሌጁ) ስም	የገንዘቡ ልክ
1.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	56,296.87
2.	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	22,790.13
3.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	16,979.40
4.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	22,597.00
	ጠቅላላ ድምር	118,663.40

3.4.2. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ከሥራ ለቀው ከሄዱ በኋላ የተፈጸመው የተጣራ ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለሥራ ግብርና ለጡረታ ተቀናናሽ ሂሳቦች ደግሞ ተገቢ ማስተካከያ እንዲሰራላቸው እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም በፌዴራል

መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 12 (1ሐ) መሰረት የዩኒቨርሲቲዎቹና የኮሌጁ የሥራ ክፍሎች በሥራቸው የሚገኙ ሰራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ መረጃውን ወር በገባ እስከ 20ኛው ቀን ድረስ የፋይናንስ ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል እንዲሁም በግልባጭ የአስተዳደር ክፍሉ እንዲያውቀው በማድረግ ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ለሰራተኞች የሚከፈለውን ደመወዝ መቀነስ ስለሚቻል በደመወዝ አከፋፈል ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.5. <u>በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቀድ ቀጣይነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ ለተፈጸመ የኮንትራትና የቀን ሠራተኞች ቅጥር የተፈጸመ ክፍያ</u>

3.5.1. <u>ግኝት</u>

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተጻፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣

በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባልተመደበ እና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው እና እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ ተላልፏል፡፡

ይሁን እንጂ ስምንት ተቋማት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን ሳይስፈቅዱ በኮንትራት እንዲሁም በቋሚ የሥራ መደቦች ላይ ሰራተኞችን በቀን ሥራ በመቅጠር በጠቅላላው ብር **31,215,064.81** ክፍያ የፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

3.5.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ዘላቂነት ባለው የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀንና በኮንትራት/ ጊዚያዊነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ ክፍያው ሊቆም እንደሚገባ፤ ለወደፊቱም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር ለመፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማቅረብ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

3.6. በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ

3.6.1. ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመደንገግ በወጣው መመሪያ ቁጥር 921/2014 ክፍል ሁለት አንቀጽ አምስት ንዑስ አንቀጽ ሁለት መሰረት በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የትርፍ ሰዓት ሥራ ተግባራዊ የሚሆነው በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አስቀድሞ ከተፈቀደ ብቻ ለመሆኑ ተመልክቷል።

ይሁን እንጂ የቀብሪደሐር ዩኒቨርሲቲ በጠቅላላው ብር 489,500.00 የትርፍ ሰዓት ክፍያ ለ39 የአስተዳደር ሰራተኞች ሲፈጽም የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲፈቀድ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። ሁኔታው ዩኒቨርሲቲው ህጉን ተከትሎ የመፈጸም ክፍተት ያለበት መሆኑን ያመለክታል።

3.6.2. የማሻሻያ ሃሳብ

የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የትርፍ ሰዓት ሥራው ለመስራት ያስፈለገበትን ሁኔታ በመግለጽ እና ሥራው ሳይሰራ ቢቀር በመሥሪያ ቤቱ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት በመጥቀስ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ከተፈቀደ በኋላ ክፍያ መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል።

3.7. አለአግባብ (በብልጫ) የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎች ስለመኖራቸው

3.7.1. ግኝት

ዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ ክፍያዎች የሚፈጽሙት የወጡ አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰባት ተቋማት ብር 5,487,974.93 አለአግባብ (በብልጫ) የተፈጸሙ የተለያዩ ክፍያዎች መኖራቸው ታውቋል። ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል።

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም	ለውሎ አበል፣ ለደመወዝ እና ሌሎች ወጪዎች
1.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	50,316.00
2.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	738,433.15
3.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	6,800.00
4.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	291,379.61
5.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የንግድ ሥራ ት/ቤት	38,739.60
6.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	3,475,179.47
7.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	887,127.10
	ጠቅላላ ድምር	5,487,974.93

3.7.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ አለአግባብ የተፈጸሙት ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ፤ ለወደፊቱም የተለያዩ ክፍያዎች ሲፈጸሙ ደንብና መመሪያን መሰረት አድርገው እንዲፈጸሙ አሳስበናል።

3.8. በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ያልተፈጸሙ ግዥዎች

3.8.1. ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል መስከረም 25 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር

ገ/ሂ/1/53/86 ባስተላለፈው ስርኩላር መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በዘጠኝ ተቋማት በብር 35,610,058.92 ለተፈጸመው ግዥ ጨረታ ሳይወጣ ግዥው ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- በስምንት ተቋማት በብር 19,689,998.87 ለተፈጸመው ግዥ ጨረታ ሳይወጣ ግዥው በዋጋ ማወዳደሪያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- በአራት ተቋማት በብር 3,350,236.64 ለተፈጸመው ግዥ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ ግዥው በቀጥታ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

በድምሩ ብር በብር 58,650,294.43 ከመመሪያው ውጪ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል።

3.8.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ግዥዎች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው የማይፈጸሙ ከሆነ፡-

- ♦ በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤

- ♦ የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤
- ♦ ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን የሚችል በመሆኑ፤
- ♦ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ፤

ዩኒቨርሲቲዎቹ የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3.9. በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ የወጪ ሂሳቦች

3.9.1. ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገንዘብ ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአስራ ሶስት ተቋማት ብር 56,442,824.95 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡

በተገቢው የሒሳብ መደብ ካልመዘገቡት ውስጥ ከፍተኛውን መጠን የያዙት፡-

1.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	ብር 27,190,058.66፣
2.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	ብር 7,000,000.00፣
3.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	ብር 5,871,433.53፣
4.	የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	ብር 5,596,224.47፣
5.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	ብር 3,390,615.81
6.	የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	ብር 1,944,143.77፣
7.	የትምህርት ሚኒስቴር	ብር 1,585,496.00፣
8.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	ብር 1,496,900.97፣

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

3.9.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ዩኒቨርሲቲዎቹ የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የሒሳብ መደቡን (ኮዱን) ጠብቀው እንዲመዘገቡ ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3.10. በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

3.10.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2(5) መሰረት ለወጪ ሒሳቦች ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን እና ማስረጃ እስኪቀርብላቸው ድረስ በተሰብሳቢ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር **3,202,966.00** በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

3.10.2. የማሻሻያ ሃሳብ

የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ሥርዓት መመሪያ መሰረት በወጪ ለተመዘገበው ማስረጃ ቀርቦ ሂሳቡ እስኪወራረድ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲያዝ መደረግ እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

3.11. የቦታ ግምት ካሳ ክፍያ ተፈጽሞ የቦታ ርክክብ ያልተደረገ ስለመሆኑ

3.11.1. ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8(2/ለ) መሰረት ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ለመሬት ካሳ ለተፈጸሙ ክፍያዎች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን እና የቦታ ርክክብ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የዲላ ዩኒቨርሲቲ ለካሳ ክፍያ ብር **3,161,951.46** የፈጸመ ቢሆንም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰነድ ያልቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ የቦታ ርክክብ ያልተደረገ መሆኑ ታወቋል፡፡

3.11.2. የማሻሻያ ሃሳብ

የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰነድ ሳይቀርብ ለተፈጸመው ክፍያ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ፤ ክፍያ ተፈጽሞ የመሬቱ ርክክብ ሳይደረግ

መቆየቱም አግባብነት የሌለው ስለሆነ ዩኒቨርሲቲዎቹ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠትና ከሚመለከታቸው የአስተዳደሮቹ አካላት ጋር በመነጋገር ጉዳዩ መፍትሔ እንዲያገኝ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል።

3.12. በገቡት የውል ግዴታ መሰረት ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ገበታቸው ባልተመለሱ መምህራን ላይ እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

3.12.1. ግኝት

ዩኒቨርሲቲዎች ለሚሰጡት የትምህርት ዕድል የግዴታ ውል የሚያስገቡ፣ ዋስ የሚያስጠሩ መሆኑን እና የትምህርት ዕድል ያገኙት መምህራን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግዴታቸውን የሚወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሶስት ተቋማት የትምህርት ዕድል ከተሰጣቸው ውስጥ ውል የገቡበት የገንዘብ መጠን የማይታወቅ ሲሆን፣ አሥራ ሰባት መምህራኖች በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ብር 6,127,344.00 እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል።

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም	ብዛታቸው በቁጥር	የገንዘብ ልክ
1.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	3	1,957,080.00
2.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	11	2,945,762.00
		1	አይታወቅም
3.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	3	1,224,502.00
	ጠቅላላ ድምር	18	6,127,344.00

3.14.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ሰራተኞቹ በገቡት የውል ግዴታ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም ዩኒቨርሲቲዎቹ የትምህርት ዕድል የሰጧቸው ሰራተኞች በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን የተወጡ

ለመሆናቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4. ተሰብሳቢ ሂሳብ

4.1. በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ

4.1.1. ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በአሥራ ስድስት ተቋማት በጠቅላላው ብር **2,410,782,443.36** ለረጅም ዓመታት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ የታወቀ ሲሆን የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ	የገንዘቡ ልክ
1	ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት	309,386,378.96
2	ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት	1,724,133,446.82
3	ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት	323,291,987.72
4	ከአሥር ዓመት በላይ	50,751,111.42
5	የቆይታ ጊዜው እና ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ	3,219,518.44
	ድምር	2,410,782,443.36

ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰብ (ሳይወራረድ) ከቆየው ሂሳብ ከፍተኛውን መጠን ከያዙት ውስጥ፡-

1.	የትምህርት ሚኒስቴር	ብር	1,012,583,714.10፣
2.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	ብር	433,597,818.45፣
3.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	ብር	191,754,375.39፣
4.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	ብር	189,174,831.59፣
5.	የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	ብር	170,720,828.82፣
6.	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	ብር	102,279,202.56፣

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ።

4.1.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ ሪፖርቶቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡት ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው አሳስበናል።

4.2. መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ተሰብሳቢ ሂሳቦች

4.2.1. ግኝት

በተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery Ledger) ላይ የተመለከቱት ተሰብሳቢ ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በትምህርት ሚኒስቴር ብር 898,637.50 እና በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,152,246.41 በጠቅላላው ብር 3,050,883.91 የተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን ሳይጠብቁ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ ታውቋል።

4.2.2. የማሻሻያ ሃሳብ

በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ አጠቃላይ ሌጀሮቹ ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን እና የሂሳብ ምዝገባውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው

ስለሚችል ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና፤ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ እሳስበናል።

4.3. ከግንባታ ክፍያዎች ያልተቀነሰ (ተመላሽ ያልተደረገ) የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ

4.3.1. ግኝት

ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በውሉና በህጉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና የአመዘጋገብ ሥርዓቱም የገንዘብ ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ብር 17,482,830.27 የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። ዝርዝራቸው ቀጥሎ ቀርቧል።

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም	ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያ
1.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	7,447,056.05
2.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	10,035,774.22
	ጠቅላላ ድምር	17,482,830.27

4.3.2. የማሻሻያ ሃሳብ

መሰብሰብ የሚገባው ገንዘብ ካልተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ ባክኖ እንዲቀር ምክንያት ሊሆን ስለሚችል የቅድሚያ ክፍያው ሂሳብ በህጉና በውሉ መሰረት እንዲሰበሰብ መደረግ እንዳለበት እሳስበናል።

4.4. ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ በተቀጽላ ሌጀር ላይ የተመለከተ ሂሳብ

4.4.1. ግኝት

የገንዘብ ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በተቀጽላ ሌጀር ላይ የተመለከቱት ሂሳቦች ከማን እንደሚሰበሰቡ ሲጣራ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶለት የተመዘገበው ሂሳብ ብር 1,136,040.83 ከማን እንደሚሰበሰብ የማይጣወቅ መሆኑ ታውቋል።

4.4.2. የማሻሻያ ሃሳብ

በተቀጽላ ሌጀር ላይ የተመዘገበው ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቀው ሂሳብ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

4.5. ለአንድ ግለሰብ በተለያየ ጊዜ በተዘጋጁ መታወቂያዎች ውል ተፈጽሞ በድጋሚ በተሰብሳቢ የተያዘ የካሳ ክፍያ

4.5.1. ግኝት

በተሰብሳቢ የተያዙ ሂሳቦች ተገቢነት ሲጣራ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በአንድ ግለሰብ ሥም በተለያየ ጊዜ በተዘጋጁ መታወቂያዎች በተዘጋጁ ውሎች በሁለት የባንክ ሂሳብ ቁጥር ብር 653,535.00 እና ብር 362,876.40 በድምሩ ብር **1,016,411.40** በአንድ ግለሰብ ሥም ተከፍሎ በድጋሚ በተሰብሳቢ የተያዘ የካሳ ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡

4.5.2. የማሻሻያ ሃሳብ

በአንድ ግለሰብ ሥም በተለያየ ጊዜ በተዘጋጁ መታወቂያዎች ውል ተፈጽሞ የተከፈለው ሂሳብ ሁኔታ ተጣርቶ ያለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ እንዲደረግ፤ በተጨማሪም በዚህ ድርጊት ላይ ተሳትፎ ያላቸው አካላት ተጣርተው አስፈላጊው የህግ እርምጃ እንዲወሰድባቸው መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5. ተከፋይ ሂሳብ

5.1. ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ ሂሳብ

5.1.1. ግኝት

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል በተገባው ውልና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአሥራ አንድ ተቋማት በጠቅላላው ብር **85,536,339.55** በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝ ሲሆን የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ	የገንዘቡ ልክ
1.	ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት	20,806,008.36
2.	ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት	47,396,977.84
3.	ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት	7,860,666.73
4.	ከአሥር ዓመት በላይ	8,634,428.74
5.	የቆይታ ጊዜው የማይታወቅ	838,257.88
	ድምር	85,536,339.55

ለረጅም ዓመታት ከፍተኛውን የተከፋይ ሂሳብ መጠን ከያዙት ውስጥ፡-

1. የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,952,097.85፣
2. የአምቦ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,701,215.42፣
3. የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,476,600.10፣
4. የትምህርት ሚኒስቴር ብር 5,339,275.11፣
5. የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,399,546.93፣
6. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 3,548,890.51፣

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

5.1.2. የማሻሻያ ሃሳብ

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ስለሚችሉ ዩኒቨርሲቲዎቹ የተከፋይ ሂሳቦቹን ሁኔታ በማጣራት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

5.2. መደበኛ የሒሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ተከፋይ ሂሳቦች ስለመኖራቸው

5.2.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የተከፋይ ሒሳቦች የክሬዲት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በሚዛን

ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በቴፒ ግቢ በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ ብር 2,586,601.32 ክሬዲት ሚዛን መታየት ሲኖርበት ዴቢት ሚዛን የሚታይ መሆኑ ታውቋል።

5.2.2. የማሻሻያ ሃሳብ

በዴቢት ሚዛን የሚታየው የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም ሂሳቦች መደበኛ የዴቢትና የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

5.3. ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው የተከፋይ ሂሳቦች ስለመኖራቸው

5.3.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለተሰብሳቢ እና ለተከፋይ ሒሳቦች ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀላቸው መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ሥር በሚገኙ ካምፓሶች በጠቅላላው ለብር **84,820,262.99** ተከፋይ ሂሳቦች ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው እና የተከፋይ ሂሳብ ባለመብቶች ተለይተው የማይታወቁ መሆኑ ታውቋል።

5.3.2. የማሻሻያ ሃሳብ

የሂሳቦቹ ባለመብቶቹ እነማን እንደሆኑ በማስረጃ ተደግፎ በተገቢው ሁኔታ ተጣርቶ ተቀጽላ ሌጀር ሊዘጋጅላቸው እንደሚገባ እና ለወደፊቱም ተከፋይ ሂሳቦች በሚመዘገቡበት ጊዜ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

5.4. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ ሂሳብ

5.4.1. ግኝት

1. የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው በገቢው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 60/2012 አንቀጽ አንቀጽ 7(5) ማንኛውም ወኪል በወሩ ውስጥ ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ቀንሶ የያዘውን ታክስ በሙሉ ወሩ በተጠናቀቀ ባለው

ቀጣይ ወር የ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ገቢ የተደረገ መሆኑን፤

2. የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የቅድመ ግብር ክፍያ ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/2011 ባወጣው መመሪያ ተራ ቁጥር 1(ሀ እና ለ) እና ተራ ቀጥር 4 መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የቅድመ ግብር ተቀናሽ የሚደረግ መሆኑን እንዲሁም በወሩ ቀንሶ ቀሪ ያደረገውን አጠቃላይ ግብር ከወሩ መጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ገቢ የተደረገ መሆኑን፤
3. ከግንባታ ክፍያ ላይ ተቀናሽ መደረግ ያለባቸው ሂሳቦች የግዥና የታክስ ህጉን ተከትለው የተቀነሱ መሆኑን፤
4. በገቢ አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል 2 አንቀፅ 12 እና ክፍል 6 አንቀፅ 25 እንዲሁም በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ክፍል ሰባት አንቀፅ 54 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ላይ የሥራ ግብር ተቀናሽ የሚደረግ መሆኑን፤

ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

- በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 263,593.22 የተገኘ መሆኑ፤
- በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ያልተቀነሰ የቅድሚያ ግብር ብር 544,271.57 የተገኘ መሆኑ፤
- በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ብር 4,967.64 የተገኘ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያልተቀነሰ የሥራ ግብር ብር 84,600.00 የተገኘ መሆኑ፤

በጠቅላላው ብር **897,432.43** በህጉ መሰረት ያልተቀነሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.4.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ያልተቀነሱት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፤ ለወደፊቱም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት መቀነስ ያለባቸው ሂሳቦች በህጉ መሰረት ለመቀነሳቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

6. በጀት

6.1. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

6.1.1. ግኝት

ኦዲት የተደረጉት ዩኒቨርሲቲዎችና መሥሪያ ቤቶች በ2014 በጀት ዓመት በየፕሮግራሞቹ ለመደበኛና ለካፒታል እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው የበጀት አጠቃቀም ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲመዛዘን ከ10% በላይ፡-

- በአስራ ሁለት ተቋማት ከመደበኛ ሂሳብ የወጪ በጀት ብር **405,257,969.29**፤
- በአሥራ አንድ ተቋማት ከካፒታል ሂሳብ የወጪ በጀት ብር **2,242,247,015.58**፤
- በሰባት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ሂሳብ የወጪ በጀት ብር **207,644,481.79**፤

በጠቅላላው ብር **2,855,149,466.66** ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

6.1.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ እና በተጨማሪም በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ክትትል በማድረግና ሥራ ላይ ሊውል የማይችለውን በጀት

ለይተው በማውጣት ለገንዘብ ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

6.2. ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ

6.2.1. ግኝት

ኦዲት በተደረጉት ዩኒቨርሲቲዎች እና መሥሪያ ቤቶች በ2014 በጀት ዓመት በየፕሮግራሞቹ ለመደበኛና ለካፒታል እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተደለደለው የወጪ ሂሳብ በጀት አጠቃቀም ሁኔታ ሲመዛዘን፡-

- በሰባት ተቋማት ከመደበኛ ሂሳብ የወጪ በጀት ብር **285,599,086.14**፤
- በአራት ተቋማት ከካፒታል ሂሳብ የወጪ በጀት ብር **475,783,496.92**፤
- በሶስት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ሂሳብ የወጪ በጀት ብር **288,998,079.52**፤

በጠቅላላው ብር **1,050,380,662.58** ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

6.2.2. የማሻሻያ ሃሳብ

በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል ተቋማቱ የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትለው የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

7. ንብረት

7.1. የዩኒቨርሲቲዎቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ ይኸውም፡-

7.1.1. ግኝት

1. ሁለት ተቋማት ለቋሚ እቃዎች በተሟላ መልኩ መለያ ቁጥር ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል። ዝርዝራቸውም ቀጥሎ ቀርቧል።

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም
1.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ
2.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በከፊል

2. አምስት ተቋማት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ መሆኑ ታውቋል። ዝርዝራቸውም፡-

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም	ምርመራ
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	
2.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	
3.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	
4.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	በቤተ-መጽሐፍት
5.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	

3. አራት ተቋማት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል። ዝርዝራቸውም፡-

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም	ምርመራ
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	በላይብረሪው
2.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	ከንብረት ግምጃ ቤት ውጭ ያሉ ንብረቶች
3.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ	

4.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	ከንብረት ግምጃ ቤት ውጭ ያሉ ንብረቶች

4. በሁለት ተቋማት ለአላቂ እቃዎች መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ያላቋቋሙ እና ቢያቋቁሙም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ መሆኑ ታውቋል። ዝርዝራቸውም፡-

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም	ምርመራ
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	ለመድሃኒቶችና ለሆስፒታሉ አላቂ እቃዎች እንዲሁም ለንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች፡፡
2.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	ሪፈራል ሆስፒታል ለመድኃኒት እና በሃጫሉ ሁንዴሳ ካምፓስ ለተማሪዎች የምግብ ግብአቶች ሚኒ ስቶር

5. በስምንት ተቋማት ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች መኖራቸው ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)

6. በአሥራ አምስት ተቋማት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)

7. በአምስት ተቋማት ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞችና ኃላፊዎች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያላደረጉ

መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 10 ተያይዟል)

8. በስድስት ተቋማት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶችና የተለያዩ ኬሚካሎች ያልተወገዱ መሆኑ ታውቋል። ዝርዝራቸውም፡-

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ
2.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ
3.	የቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ
4.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ
5.	የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
6.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

7.1.2. ***የማሻሻያ ሃሳብ***

የአሰራር ክፍተቶቹ የመንግሥት ንብረቶችን ለብክነት የሚያጋልጡ እና ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት መስተካከል እና መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል።

7.2. *የመሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-*

7.2.1. ***ግኝት***

1. ***ያለአገልግሎት ወይም በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች***

   1.1. በአሥራ ሶስት ተቋማት 115 መኪኖች፤

   1.2. በሶስት ተቋማት 4 ሞተር ሳይክሎች፤

   1.3. በሁለት ተቋማት 4 ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎች፤

   በጠቅላላው 123 ተሽከርካሪዎች ያለአገልግሎት በብልሽት ቆመው የሚገኙ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝራቸው አባሪ 11 ተያይዟል)

2. በአራት ተቋማት ለአስራ አንድ መኪናዎች እና ለአራት ሞተር ሳይክሎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊቢሬ) ያልቀረበላቸው መሆኑ ታውቋል። ዝርዝራቸውም፡-

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ሥም	መኪና	ሞተር ሳይክል
1	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	6	
2	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	2	4
3	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	1	
4	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	2	
	ድምር	11	4

3. በአምስት ተቋማት የሚገኙ አስራ ሰባት ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም መሆናቸው ታውቋል።

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ሥም	መኪና
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	2
2.	የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	1
3.	ትምህርት ሚኒስቴር	1
4.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	6
5.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	7
	ድምር	17

4. <u>በተሽከርካሪዎች ላይ የታዩ ልዩ ልዩ ክፍተቶች</u>

4.1. በሶስት ተቋማት የሚገኙ 14 መኪኖች እና 2 ሞተር ሳይክሎች የነዳጅ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤

4.2. በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ አንድ መኪና፣ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ አንድ ሞተር፣ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ አንድ ትራክተር የሰሌዳ (የታርጋ) ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤

4.3. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር በሚገኙ ሁለት ተቋማት በሁለት መኪኖች አካል እና በሊቢሪያቸው መካከል ያለው የሻንሲ ቁጥር የተለያየ መሆኑ፤

4.4. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር በሚገኙ ሁለት ተቋማት በሁለት መኪኖች አካል እና በሊቢሬው መካከል ያለው የሞተር ቁጥር የተለያየ መሆኑ፤

4.5. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ንብረት በሆነው በሰሌዳ (የኮድ) ቁጥር 4-16171 አካል ላይ የሞተር ቁጥሩ ያልተገኘ መሆኑ፤

4.6. የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ንብረት ለሆኑ ሶስት መኪኖች የመድኅን ዋስትና ያልተገባላቸው መሆኑ፤

ታውቋል።

7.2.2. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ካልተደረገ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ካልተደረገ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ ስለሚችል፣
- ሊቢሬ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች የመሥሪያ ቤቶቹ ናቸው ብሎ ለመቀበል ስለሚያስቸግር፣

- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሆኑ እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች የዩኒቨርሲቲው ንብረቶች ናቸው ብሎ ለመቀበል ሊያስቸግር ስለሚችል፣
- የነዳጅ ጌጃቸው የማይሰሩ ተሽከርካሪዎች ካልተስተካከሉ በነዳጅ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ስለሚችል፤
- የታርጋ ቁጥር ለሌለው ተሽከርካሪ ታርጋ እንዲወጣለት ካልተደረገ መንቀሳቀስ ስለማይችል፤

- በሊብሪያቸው መካከል ያለው የሻንሲ ቁጥራቸው እና የሞተር ቁጥራቸው እንዴት ሊለያይ እንደቻለ ተጣርቶ ካልተስተካከለ በቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ስለሚችል፤
- የመድኀን ዋስትና ያልተገባላቸው መኪኖች ላይ አደጋ ቢደርስ የመድን ዋስትና ሽፋን ስለማያገኙ እና የመጠገን እድላቸው የጠበበ ሊሆን ስለሚችል፤

በአጠቃላይ በመሥሪያ ቤቶቹ ተሽከርካሪዎቹ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ላይ የታዩትን ክፍተቶች በመመሪያው መሰረት መስተካከል እንዳለባቸው አሳስበናል።

8. ልዩ ልዩ

8.1. በውሉ መሰረት በጊዜ ገደባቸው ያልተጠናቀቁ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

8.1.1. ግኝት

በግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሥር በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን እና ሥራ ተቋራጮቹም በገቡት ውል መሠረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ከግንባታ ክፍል በተገኘው መረጃ መሰረት በጠቅላላው በብር 1,880,279,986.62 እየተገነቡ የሚገኙ 18 የግንባታ ፕሮጀክቶች ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት ድረስ በገቡት ውል መሰረት ግንባታውን ያልተጠናቀቁ መሆኑን ለመገንዘብ ተችላል።

8.1.2. የማሻሻያ ሃሳብ

መጠናቀቅ ባለባቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ እና የዘገዩ ግንባታዎች አፈጻጸም ተጨማሪ ወጪ የሚያስከትሉ በመሆኑ ዩኒቨርሰቲው ከሥራ ተቋራጮቹ፣ ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመነጋገርና በመወያየት ለመዘግየታቸው ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት እና ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በመሥራት ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዲበቁ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው አካላት ከፍተኛ ጥረት

ሊያደርጉ እንደሚገባ እና በተጨማሪም በገቡት ውለታ መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡ የሥራ ተቋራጮች ላይ በግዥ መመሪያው መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

8.2. በውሉ መሰረት በጊዜ ገደባቸው ያልተጠናቀቁና የተቋረጡ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

8.2.1. ግኝት

በአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲው እየተከናወኑ የሚገኙ ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን እና ሥራ ተቋራጮቹም በገቡት ውል መሠረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ኮንትራክተሮች ጋር ሶስት ፕሮጀክቶችን ለማሰራት ተጨማሪ ሥራዎችን ጨምሮ በብር 607,089,134.77 ውል የገባ ቢሆንም፡-

1. ሁለት የግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራቸው 22% እና 87% የሚገኝ ሲሆን ከ2 እና ከ10 ዓመት በላይ ሥራቸው የተቋረጠ መሆኑ፤
2. አንድ የግንባታ ፕሮጀክት ሥራው 99% ላይ የሚገኝ ሲሆን የግንባታ ሥራው ሳይጠናቀቅ ከሁለት ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

ታውቋል።

8.2.2. የማሻሻያ ሃሳብ

መጠናቀቅ ባለባቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ እና የዘገዩ ግንባታዎች አፈጻጸም ተጨማሪ ወጪ የሚያስከትሉ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ከሥራ ተቋራጮቹ እና ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር በጋራ በመወያየት ለመዘግየታቸው ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት እና ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በመሥራት ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዲበቁ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው አካላት ከፍተኛ ጥረት ሊያደርጉ እንደሚገባ፤ እንዲሁም በገቡት ውለታ መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡ የሥራ ተቋራጮች ላይ በግዥ መመሪያው መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

8.3. የተቋረጡ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

8.3.1. ግኝት

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ለሚያካሂደው የተለያዩ ግንባታዎች ከተለያዩ ኮንትራክተሮች ጋር ባደረገው የውል ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎች የግዥ ውሉን ተከትሎ የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ዩኒቨርሲቲው ከሚያካሂደው የተለያዩ ግንባታዎች ውስጥ፡-

1. ሲና ህንጻ ሥራ ተቋራጭ፣ (G+0) የተማሪዎች መመገቢያ (Lot:C-21)፣
2. ሼድ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ (Construction of G+4 Student Dormitory Building (Lot:C-15) ፣
3. ሼድ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ፣ (አነስተኛ ስታዲየም በዋናው ግቢ (Lot: C-5A) ፣
4. 3M ኢንጂነሪንግ (G+4) ሜዲካል ላባራቶሪ ህንጻ ግንባታ (Lot: C)፣
5. ኢቅራ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ (አነስተኛ ስታዲየም በዋናው ግቢ (Lot C-5A) ፣
6. ኦሪክስ ኮንስትራክሽን ፒኤልሲ (G+4) ክላስ ሩም ህንጻ ግንባታ (Lot C-5B) ፣
7. ሰለሞን ግደይ የሕንፃ ሥራ ተቋራጭ (G+1) የቤተመጽሐፍት ህንጻ ግንባታ (Lot- C-20) ፣

የተባሉ የሥራ ተቋራጮች ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ የግንባታ ሥራቸውን ያቋረጡ ሲሆን ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ድረስ ከተመለከቱት የሥራ ተቋራጮች ብር 104,702,573.10 ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 12 ተያይዟል)

8.3.2. የማሻሻያ ሃሳብ

ድርጅቶቹ ግንባታውን በገቡት ውል መሰረት ካለማጠናቀቃቸውም በተጨማሪ ከፍተኛ የቅድሚያ ክፍያ ቀሪ ገንዘብ እያለባቸው ሥራቸውን ያቋረጡ ሲሆን በዩኒቨርሲቲው በኩል የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ

ታውቋል። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው በውሉ መሰረት ተገቢ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት አሳስበናል።

8.4. <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና በሂደት ላይ የሚገኙ ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች</u>

8.4.1. <u>ግኝት</u>

ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ከተደረጉ ተቋማት ብር 250,494,083.16 እና በዶላር 23,055.00 ተመላሽ መደረግ ካለባቸው (ማስረጃ ሊቀርብላቸው ከሚገባቸው) የኦዲት ግኝቶች ውስጥ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ብር 31,531,504.30 እርምጃ የተወሰደበት (የተሰበሰበ) ሲሆን ብር 218,962,578.86 እና በዶላር 23,055.00 እርምጃ ያልተወሰደበት (ያልተሰበሰበ) መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 13 ተያይዟል)

8.4.2. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ዩኒቨርሲቲዎቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት እንዲሁም ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ዩኒቨርሲቲዎቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል።

<u>በጸጥታ ችግር ምክንያት የኦዲት ሥራቸው የተቋረጠ ተቋማት ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም
1.	የደባርቅ ዩኒቨርሲቲ
2.	የጎንደር ዩኒቨርሲቲ
3.	የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
4.	የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

5.	የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
6.	የወሎ ዩኒቨርሲቲ
7.	የመቅደላ ዩኒቨርሲቲ

<u>በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቀድ ቀጣይነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ ለተፈጸመ ለኮንትራትና የቀን ሠራተኞች ቅጥር የተፈጸመ ክፍያ ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የገንዘቡ ልክ
1.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	2,394,120.00
2.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	10,767,898.33
3.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	312,591.00
4.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	8,128,315.56
5.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ	1,123,188.72
6.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ	1,531,800.20
7.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	6,297,692.00
8.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	659,459.00
	ጠቅላላ ድምር	**31,215,046.81**

የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ የፈጸሙ መሥሪያ ቤቶች

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው (የኮሌጁ) ስም	ለግዥው ጨረታ ሳይወጣ			የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ	ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ጉዳዮች	ድምር
		በቀጥታ ከአንድ አቅራቢ የተፈጸመ ግዥ	መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተፈጸመ ግዥ	በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ			
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	5,510,614.58			280,500.00		5,791,114.58
2.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ			876,120.51	704,716.41		1,580,836.92
3.	የቀብሪደሐር ዩኒቨርሲቲ	4,240,000.00					4,240,000.00
4.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	1,184,900.00		3,822,862.15			5,007,762.15
5.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	320,461.23		2,371,055.00	1,065,632.49		3,757,148.72
6.	የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	970,000.00					970,000.00
7.	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	8,574,216.00					8,574,216.00
8.	የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	4,404,960.07		434,571.20			4,839,531.27
9.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ			720,750.01			720,750.01
10.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	2,210,440.38		1,367,000.00			3,577,440.38

11.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	8,194,466.66		4,925,140.00	1,299,387.74		14,418,994.40
12.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ			5,172,500.00			5,172,500.00
	ጠቅላላ ድምር	35,610,058.92	-	19,689,998.87	3,350,236.64	-	58,650,294.43

<u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ የወጪ ሂሳቦች ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ሥም	የገንዘቡ ልክ
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	**845,195.80**
2.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	**3,390,615.81**
3.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	**372,302.84**
4.	የቀብሪደሐር ዩኒቨርሲቲ	**811,220.00**
5.	የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	**1,944,143.77**
6.	የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	**5,596,224.47**
7.	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	**322,155.60**
8.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	**17,077.50**
9.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	7,000,000.00
10.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	**27,190,058.66**
11.	የትምህርት ሚኒስቴር	**1,585,496.00**

12.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	5,871,433.53
13.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	1,496,900.97
	ጠቅላላ ድምር	**56,442,824.95**

<u>በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው (የመሥሪያ ቤቱ) ሥም	የተሰብሳቢው የቆይታው ጊዜና የገንዘቡ መጠን				የቆይታ ጊዜው እና ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ	ድምር
		ከ1 ወር በላይ እስከ 1 ዓመት	ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት በላይ እስከ 10 ዓመት	ከ 10 ዓመት በላይ		
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	9,766,370.23	179,408,461.36				189,174,831.59
2.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	180,400.00	1,694,277.55	60,123.40	96,433.13		2,031,234.08
3.	የትምህርት ሚኒስቴር	11,949,908.77	980,250,606.83	9,456,248.24	10,926,950.26		1,012,583,714.10
4.	የቀብሪደሐር ዩኒቨርሲቲ	4,870,788.65	78,784,821.30				83,655,609.95
5.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	28,967,980.61	79,805,627.72	81,652,164.53	1,328,602.53		191,754,375.39
6.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	33,058,531.68	6,009,238.90	3,170,394.66	94,315.88		42,332,481.12
7.	የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	329,271.12	159,901,449.18	7,961,924.00	2,528,184.52		170,720,828.82
8.	የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	12,483,320.37	2,188,334.51	1,795,354.36	64,767.12		16,531,776.36

9.	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	450.86	35,662,533.70	66,603,598.00	12,620.00		102,279,202.56
10.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ	1,407,705.60	2,746,443.06	20,406,588.02		421,006.32	24,981,743.00
11.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	3,495.83	1,225,839.19	2,056,577.53			3,285,912.55
12.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ አርክቴክቸር ሕንጻ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት		2,815,927.27		32,103,443.98	3,512,486.20	38,431,857.45
13.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ	249,252.71	4,304,409.68	4,063,498.97	2,881,819.92		11,498,981.28

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው (የመሥሪያ ቤቱ) ሥም	የተሰብሳቢው የቆይታው ጊዜና የገንዘቡ መጠን				የቆይታ ጊዜው እና ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ	ድምር
		ከ1 ወር በላይ እስከ 1 ዓመት	ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት በላይ እስከ 10 ዓመት	ከ 10 ዓመት በላይ		
14.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	11,074.64	36,054,466.88				36,065,541.52
15.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	204,045,678.69	111,648,040.19	117,904,099.57			433,597,818.45
16.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	2,062,149.20	41,632,969.50	8,161,416.44			51,856,535.14

	ጠቅላላ ድምር	309,386,378.96	1,724,133,446.82	323,291,987.72	50,037,137.34	3,933,492.52	2,410,782,443.36

<u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳቦች ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው (የመሥሪያ ቤቱ) ስም	የቆይታው ጊዜና የገንዘቡ ልክ					ድምር
		ከ1 ወር በላይ እስከ 1 ዓመት	ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት በላይ እስከ 10 ዓመት	ከ 10 ዓመት በላይ	የቆይታው ጊዜ የማይታወቅ	
1	የትምህርት ሚኒስቴር	695,621.54		4,643,653.57			5,339,275.11
2	የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	11,952,964.19	25,413,373.44	1,804,763.77	780,996.45		39,952,097.85
3	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	3,728,082.21	7,051,946.46	1,101,423.86	7,819,762.89		19,701,215.42
4	የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	45,580.65	2,924.80				48,505.45
5	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ	1,063,068.07	469,925.91				1,532,993.98
6	በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	2,505,716.93	919,716.76	123,456.82			3,548,890.51
7	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ	166,811.59		8,146.71	33,669.40		208,627.70
8	የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ	123,585.01				838,257.88	961,842.89

9	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	357,521.61		9,222.00			366,743.61
10	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	167,056.56	4,232,490.37				4,399,546.93
11	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ		9,306,600.10	170,000.00			9,476,600.10
	ጠቅላላ ድምር	20,806,008.36	47,396,977.84	7,860,666.73	8,634,428.74	838,257.88	85,536,339.55

ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው የወጪ ሂሳብ በጀት ከ10% በላይ ያልተሰራበት በጀት እና ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ዝርዝር

ተ/ቁ	የዩኒቨርሲቲው ስም	ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ			ድምር	ሥራ ላይ ያልዋለ			ድምር
		መደበኛ	ካፒታል	ከውስጥ ገቢ		መደበኛ	ካፒታል	ከውስጥ ገቢ	
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ					146,810.00	110,215.82		257,025.82
2.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	128,153,771.30			128,153,771.30	68,509,420.98	642,394,191.36	16,936,096.46	727,839,708.80
3.	የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	3,565,114.05	49,780,492.81	21,762,308.79	75,107,915.65	137,446.06	600,000.00	6,950.00	744,396.06
4.	የትምህርት ሚኒስቴር					16,176,643.91	708,106,473.75		724,283,117.66
5.	የቀብሪ ደሐር ዩኒቨርስቲ	42,075.00			42,075.00	3,000,175.40	186,018,752.68		189,018,928.08
6.	የአምቦ ዩኒቨርስቲ	49,102,193.82	33,715,147.13	569,523.34	83,386,864.29	2,128,955.38	52,754,652.14	680,356.11	55,563,963.63

7.	የዲላ ዩኒቨርስቲ					56,552,952.56	4,053,914.77		60,606,867.33
8.	የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ					551,830.06		28,044,777.53	28,596,607.59
9.	የመደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ					29,269,397.39	57,699,498.17	2,330,662.54	89,299,558.10
10.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ተጠሪ ተቋማቱ	1,264,027.23		266,666,247.39	267,930,274.62	53,363,573.37	185,365,045.25	159,399,739.15	398,128,357.77
11.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	93,539,671.80	79,672,569.64		173,212,241.44	69,818,065.66	379,443,935.34	245,900.00	449,507,901.00
12.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	9,932,232.94	312,615,287.34		322,547,520.28	105,602,698.52	25,700,336.30		131,303,034.82
	ጠቅላላ ድምር	285,599,086.14	475,783,496.92	288,998,079.52	1,050,380,662.58	405,257,969.29	2,242,247,015.58	207,644,481.79	2,855,149,466.66

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሰቲው ስም	ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ			ድምር	ሥራ ላይ ያልዋለ			ድምር
		መደበኛ	ካፒታል	ከውስጥ ገቢ		መደበኛ	ካፒታል	ከውስጥ ገቢ	
13.	የጂንካ ዩኒቨርሲቲ	25,399,297.60			25,399,297.60	31,171,940.39	137,589,697.74		168,761,638.13
14.	የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ					2,866,834.90	171,800.00		3,038,634.90
15.	የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	58,781,272.64	1,516,014.54		60,297,287.18	28,565,058.06	233,337,010.00		261,902,068.06
16.	የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ					2,808,167.37	11,885,524.24		14,693,691.61
17.	የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	127,725,047.47	173,178,550.80	57,781,689.74	358,685,288.01	53,656,505.23	64,633,293.08	134,172.62	118,423,970.93
18.	የአርሲ ዩኒቨርሲቲ					1,465,653.07	14,122,759.75		15,588,412.82
19.	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ					51,734,961.38	7,136,078.30	11,925,675.19	70,796,714.87
20.	የጂማ ዩኒቨርሲቲ					4,849,901.08	9,248,615.82		14,098,516.90
21.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ተጠሪ ተቋማቱ	1,441,762.45		27,607,474.59	29,049,237.04	21,574,204.28		903,857.16	22,478,061.44
	ጠቅላላ ድምር	913,078,341.12	197,801,791.28	90,369,468.63	1,201,249,601.03	972,836,050.77	2,347,512,858.31	285,604,069.45	3,605,952,978.53

ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ዝርዝር

ተራ ቁጥር	ዩኒቨርሲቲው ሥም	የዕቃው ዓይነት	መስፈሪያ	ብዛት	ጠቅላላ ዋጋ	ዋጋቸው
1	የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	አክሰሰሪዎች	በቁጥር	46		አልተገለጸም፡፡
		ካሲዮ ካልኩሌተር	በቁጥር	10		
		ዲስክ ፍሎፒ	በቁጥር	60		
		የወንድና የሴት ጫማዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		
		ፍላት 43 ኢንች ቴሌቪ	በቁጥር	10		
		ቶነሮች/ቀለሞች	በቁጥር	338		
		የኮምፒዩተር መስታዎቶች (የኮምፒዩተር ብርሃን መቀነሻ ግላሶች)	በቁጥር	209		አልተገለጸም
		ካርትሪጅ (Nanodas Cartridge)	በቁጥር	249		አልተገለጸም
		ሸሚዞች	በቁጥር	549		አልተገለጸም
		ፑም ሁድ ማሽኖች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		የፕሪንተር ቀለሞች	በቁጥር	52		አልተገለጸም
		የተለያዩ ወንበሮች፣ ሰሀኖች፣ ብረት ድስቶች እና ቆርቆሮዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		ወንበሮች እና ብረታ ብረቶች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		ስቴንስሎች	በቁጥር	214		አልተገለጸም
		ወንበሮች	በቁጥር	29		አልተገለጸም

ተራ ቁጥር	ዩኒቨርሲቲው ሥም	የዕቃው ዓይነት	መስፈሪያ	ብዛት	ጠቅላላ ዋጋ	ዋጋቸው
		Silent /kinder Mann	በቁጥር	1500		አልተገለጸም
		ፕሮጀክተር	በቁጥር	625		አልተገለጸም
		የተማሪዎች ፍራሽ	በቁጥር	10		አልተገለጸም፡፡
		የካፍቴሪያ እና የተለያዩ የትህምርት መሳሪያዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም፡፡
		የማባዣ ቀለም/4253	በቁጥር	129		አልተገለጸም፡፡
		የአጥር ፍራሽ ቆርቆሮ እና ብረታ ብረት	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም፡፡
		የካፌ ቤት ፕላስቲክ ጠረጴዛ	በቁጥር	50		አልተገለጸም፡፡
		የመሰብሰቢያ አዳራሽ ወንበር	በቁጥር	7300		አልተገለጸም፡፡
		"LASER POINTR"	በቁጥር	132		አልተገለጸም፡፡
		ባለ አራት በር ትልቁ ፍሪጅ	በቁጥር	2		አልተገለጸም፡፡
		መካከለኛ ፍሪጅ	በቁጥር	2		አልተገለጸም፡፡
		የካፍቴሪያ ወንበር	በቁጥር	61		አልተገለጸም፡፡
		ነጪ ካፕ ቦርድ (ቁም ሳጥን)	በቁጥር	3		አልተገለጸም፡፡
		የጁስ መፍጫ ማሽን	በቁጥር	5		አልተገለጸም፡፡
		ትልቅ ኦቨን	በቁጥር	1		አልተገለጸም፡፡
		ጎላ ድስት	በቁጥር	12		አልተገለጸም፡፡
		የቧንቧ እቃዎች	በቁጥር	2,830		አልተገለጸም፡፡
		ኦቨር ሄድ ፕሮጀክተር (Over Hade Projector)	በቁጥር	2		አልተገለጸም፡፡
		S-4253 RISO INK ቀለም	በቁጥር	160		አልተገለጸም፡፡

ተራ ቁጥር	ዩኒቨርሲቲው ሥም	የዕቃው ዓይነት	መስፈሪያ	ብዛት	ጠቅላላ ዋጋ	ዋጋቸው
2	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	በእርዳታ የመጡ ዘመናዊ የህክምና መገልገያ እቃዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም፡፡
		ከክልሉ ጤና ቢሮ ለተቋሙ የተሰጡ አልጋዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም፡፡
		አዳዲስ የህክምና መሳሪያዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም፡፡
3	የቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ	የላብራቶሪ እቃዎች	በቁጥር	18		አልተገለጸም
		ካዝናዎች	በቁጥር	2		አልተገለጸም
		ጎዋን	በቁጥር	50		አልተገለጸም
		ሮቶ ባለ 500 ሊትር	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		ሮቶ ባለ 200 ሊትር	በቁጥር	2		አልተገለጸም
		የካፌ ጠረጴዛዎች	በቁጥር	16		አልተገለጸም
		ሎከር	በቁጥር	4		አልተገለጸም
		ፍሪጅ	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		የወረቀት ማባዣ ማሽኖች	በቁጥር	7		አልተገለጸም
		የፌሮ ብረታ ብረቶች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		የውሃ ማሞቂያ	በቁጥር	3		አልተገለጸም
		ኤሲዎች	በቁጥር	7		አልተገለጸም
4	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	የሴቶች ጥንድ ጫማዎች	በጥንድ	8		አልተገለጸም
		የተማሪዎች መመገቢያዎች፣ ዲቫይደር፣ ሳህኖችና መደርደሪያዎች	በቁጥር	አይታወቅም		አልተገለጸም

ተራ ቁጥር	ዩኒቨርሲቲው ሥም	የዕቃው ዓይነት	መስፈሪያ	ብዛት	ጠቅላላ ዋጋ	ዋጋቸው
		የዕቃ ማጠቢያ ሽቦዎች እና ብዛት ያላቸው የውሃ መቅጃ ጆንች	በቁጥር	አይታወቅም		አልተገለጸም
		ባለ 200 ሊትር ብረት ድስት	በቁጥር	46		አልተገለጸም
		ባለ 150 ሊትር ብረት ድስት	በቁጥር	54		አልተገለጸም
		አንድ ባለ 10,000 ሊትር ሮቶ	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		የተለያዩ የኦሮሞ የባህል ልብሶች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		መክተፊያዎች	በቁጥር	2		አልተገለጸም
		የሻይ ማንቆርቆሪያ	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		ፍራሽ	በቁጥር	3		አልተገለጸም
		አጭር የወንድ ጫማዎች	በቁጥር	199		አልተገለጸም
		ያለው ቾክ	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		ዲቫይደር	በቁጥር	400		አልተገለጸም
		ሄልሜት	በቁጥር	50		አልተገለጸም
		አንፀባራቂ ቱታ	በቁጥር	42		አልተገለጸም
		የጋዎን ጨርቅ	በሜትር	663		አልተገለጸም
		የተለያዩ ዓይነት የመለዋወጫ እቃዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		የተለያዩ ዓይነት የግንባታ እቃዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		የተለያዩ ዓይነት እቃዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		የውሀ ማጠራቀሚያ ሮቶ	በቁጥር	1		አልተገለጸም

ተራ ቁጥር	ዩኒቨርሲቲው ሥም	የዕቃው ዓይነት	መስፈሪያ	ብዛት	ጠቅላላ ዋጋ	ዋጋቸው
		ጄኔሬተር	በቁጥር	1		አልተገለጸም
5	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	ብትን ጨርቅ	በሜትር	532		አልተገለጸም
		ውስጥ ልብስ	በሜትር	488		አልተገለጸም
		ለጽኑ ህሙማን አገልግሎት የሚውል የህክምና ማሽን እንዲሁም በርካታ የህክምና መሳሪያዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		አልጋዎች	በቁጥር	20		አልተገለጸም
		ሰርጂካል ላይት (Surgical light)	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		ለደም ግፊት መለኪያ የሚያገለግል መሣሪያ "Negative Pressure Career"	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		የዕቃ ማጠቢያ ማሽን	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		የዳቦ ማቡኪያ ማሽኖች	በቁጥር	6		አልተገለጸም
		የማብሰያ ማሽኖች	በቁጥር	6		አልተገለጸም
		የወተት ማቀነባበሪያ ማሽን	በቁጥር	1		አልተገለጸም
6	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ አርክቴክቸር ሕንጻ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት	የሰሃንና የኩባያ ማጠቢያ ማሽን	በቁጥር	2		አልተገለጸም
		የወጥና የሻይ መሥሪያ ማሽኖች	በቁጥር	3		አልተገለጸም

ተራ ቁጥር	ዩኒቨርሲቲው ሥም	የዕቃው ዓይነት	መስፈሪያ	ብዛት	ጠቅላላ ዋጋ	ዋጋቸው
		የድንችና የሽንኩርት መላጫ ማሽን	በቁጥር	2		አልተገለጸም
		የምግብ ማስቀመጫ ፍሪጆች	በቁጥር	2		አልተገለጸም
7	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	ትልልቅ የወርክ ሾፕ ማሽኖች (የብረት ጥርስ ማውጫ እና የብረት ቅርፅ ማውጫ)	በቁጥር	3		አልተገለጸም
		የወጥ መስሪያ ስቲም	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		የሽንኩርት መፍጫ ማሽን	በቁጥር	1		አልተገለጸም
8	የሚዛን ቴፒ የኒቨርሲቲ	ትራሶች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		የወንድና የሴት ጫማዎች	በቁጥር	ብዛት ያላቸው		አልተገለጸም
		የወንዶች የደንብ ልብስ	በሜትር	2944		አልተገለጸም
		ዲቶል	በቁጥር	10,257		አልተገለጸም
		የሴቶች ጉርድ ጫማ	በጥንድ	412		አልተገለጸም
		የወንድ ጫማ	በጥንድ	506		አልተገለጸም
		አንሶላ	በጥንድ	69		አልተገለጸም
		ደስታ ወረቀት	በቁጥር	122		አልተገለጸም
		አዲስ የመኪና ቀለሞች	በቁጥር	5		አልተገለጸም
		እስቶቭ ትልቅ	በቁጥር	3		አልተገለጸም
		እስቶቭ ትንሹ	በቁጥር	6		አልተገለጸም
		ትንንሽ እስቶቮች	በቁጥር	13		አልተገለጸም

ተራ ቁጥር	ዩኒቨርሲቲው ሥም	የዕቃው ዓይነት	መስፈሪያ	ብዛት	ጠቅላላ ዋጋ	ዋጋቸው
		ትልልቅ ፍሪጆች	በቁጥር	3		አልተገለጸም
		ትንንሽ ፍሪጆች	በቁጥር	2		አልተገለጸም
		ቬንትሌተሮች	በቁጥር	10		አልተገለጸም
		የወጥ መሥሪያ ድስቶች	በቁጥር	6		አልተገለጸም
		ትንንሽ ምድጃዎች	በቁጥር	5		አልተገለጸም
		የዳቦ ማቡኪያ	በቁጥር	1		አልተገለጸም
		መካከለኛ ባክ እስዊብል ወንበር (ሚሽቴብል)	በቁጥር	42		አልተገለጸም

አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም
1	የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
2	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ
3	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ
4	የቀብሪደሐር ዩኒቨርሲቲ
5	የዲላ ዩኒቨርሲቲ
6	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ

7	የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ
8	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
9	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ
10	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ አርክቴክቸር ሕንጻ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት
11	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
12	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
13	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት
14	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ
15	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

<u>ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞችና ኃላፊዎች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያልተደረጉ ዕቃዎች ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም	የእቃው ዓይነት	የዕቃው ብዛት በቁጥር	የእቃው ጠቅላላ ዋጋ	ምርመራ
1	የትምህርት ሚኒስቴር	አንድ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር	9	235,733.00	ከሰባት ሰራተኞች የሚፈለግ
2	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	አንድ ኤች ፒ ላፕቶፕ ኮምፒውተር	1	17,318.50	ከአንድ ሰራተኛ የሚፈለግ
3	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	ሶስት ዲስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ አንድ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር እንዲሁም አንድ ፕሪንተር	38	አይታወቅም	ከአራት ሰራተኞች የሚፈለግ

		ሰላሳ ስምንት የተለያዩ ዓይነት ንብረቶች	አይታወቅም	አይታወቅም	
4	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	11 ሌኖቮ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር	አይታወቅም	አይታወቅም	
5	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	ለሁለት ሰራተኞች የተለያዩ ንብረቶች	2	19,478.06	

ያለአገልግሎት ወይም በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርሲቲው ስም	ብዛት		
		መኪና	ሞተር ሳይክል	** ሌሎች
1.	የሠመራ ዩኒቨርሲቲ	7		
2.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	18	2	3
3.	የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	2	1	
4.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	19		
5.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ	37		
6.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	6		
7.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢሾፍቱ እንስሳት ሕክምናና ግብርና ኮሌጅ	2		
8.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ አርክቴክቸር ሕንጻ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት	3		
9.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል	8		
10.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	4		
11.	የትምህርት ሚኒስቴር	1		

12.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	2		
13.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	6	1	1
	ድምር	115	4	4

** ሌሎች፡- ሎቤድ፣ ትራክተር፣ ባጃጅ እና የመሳሰሉትን ይይዛል፡

አባሪ. 12

የግንባታ ሥራቸውን ያቋረጡ የግንባታ ሥራ ተቋራጮች ዝርዝር

ቀን	የፕሮጀክቱ ስም	የተቋራጩ ስም	ውል የተገባበት ጊዜ	ውሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜ	ውል የተቋረጠበት ጊዜ	የግንባታ ውል ክፍያ ተ.እ..ታን ጨምሮ	በውሉ መሰረት የተሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ተእ.ታን ጨምሮ	የተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ተ.እ.ታን ጨምሮ	ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳ
1.	G+0 የተማሪዎች መመገቢያ (Lot:C-21)	ሲና ህንጻ ሥራ ተቋራጭ	ነሐሴ 13 ቀን 2009 ዓ.ም	ነሀሴ 18 ቀን 2010 ዓ.ም	መጋቢት 23 ቀን 2011 ዓ.ም	34,401,643 .95	6,880,328.79		6,880,
2.	G+4 የተማሪዎች መኝታ ቤት (ዶርሚተሪ) (Lot:C-15)	ሼድ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ	የካቲት 27 ቀን 2009 ዓ.ም	የካቲት 27 ቀን 2011 ዓ.ም	ህዳር 1 ቀን 2012 ዓ.ም	81,693,234.08	24,507,970.23	9,677,297.95	14,830,
3.	አነስተኛ ስታዲየም በዋናው ግቢ (Lot: C-5A)	ሼድ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ	የካቲት 10 ቀን 2009 ዓ.ም	የካቲት 28 ቀን 2011 ዓ.ም	ሀምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም	95,668,193.90	28,700,458.17	11,645,185.05	17,055,
4.	G+4 ሜዲካል ላባራቶሪ ህንጻ ግንባታ (Lot C)	3M ኢንጂነሪንግ	ነሐሴ 13 ቀን 2009 ዓ.ም	የካቲት12 ቀን 2011 ዓ.ም	የካቲት 24 ቀን 2011 ዓ.ም	94,865,725.71	28,459,717.71		28,459,
5.	አነስተኛ ስታዲየም በዋናው ግቢ (Lot: C-5A)	ኢቅራ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ	ሐምሌ 2/2020	ጥቅምት 19/2022	መጋቢት 28 ቀን 2014 ዓ.ም		23,106,673.43		23,106,
6.	G+4 ክላስ ሩም ህንጻ ግንባታ (Lot C-5B)	ኦሪክስ ኮንስትራክሽን	ጥቅምት 24/2009		ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም		14,369,907.77		14,369,

		ፒኤልሲ							
7.	G+1 የቤተመጽሐፍት ህንጻ ግንባታ (Lot- C-20)	ሰለሞን ግደይ ሕንፃ ሥራ ተቋራጭ	ነሐሴ 9 ቀን 2009 ዓ.ም	ጥቅምት 22 ቀን 2013 ዓ.ም	ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም	33,143,488.85	9,943,046.66	9,943,046.66	0.00
	ድምር					305,370,642.54	135,968,102.76	31,265,529.66	104,702,573.10

=

አባሪ. 1

እርምጃ የተወሰደባቸው እና ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የዩኒቨርስቲው ሥም	ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠበት	ተመላሽ የተደረገ	ተመላሽ ስለመደረጉ ያልተረጋገጠ	እርምጃ ያልተወሰደበት ቀሪ ሂሳብ
1.	የትምህርት ሚኒስቴር	436,667.12			436,667.12
2.	የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	4,157,768.79	3,503,190.47		654,578.32
3.	የወለጋ ዩኒቨርሲቲ	51,876.00	22,176.00		29,700.00
4.	የዲላ ዩኒቨርሲቲ	154,854.59	12,991.78		141,862.81
5.	የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	3,039,997.84	44,091.34		2,995,906.50
6.	የአምቦ ዩኒቨርሲቲ	374,860.00	18,775.52		356,084.48
7.	የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	121,812,262.09	21,818,271.77		99,993,990.32
8.	የቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ	225,562.00			225,562.00
9.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በብር	27,902,863.51			27,902,863.51
	በዶላር	23,055.00			23,055.00
10.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	15,536,817.39	3,077,002.03		12,459,815.36

11.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢሾፍቱ እንስሳት ሕክምናና ግብርና ኮሌጅ	228,991.64	224,647.64		4,344.00
12.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ አርክቴክቸር ሕንጻ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት	175,011.88	24,500.00		150,511.88
13.	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ	7,150,592.49	2,367,216.47		4,783,376.02
14.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት	100,000.00			100,000.00
15.	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	5,009,830.64			5,009,830.64
16.	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	64,136,127.18	418,641.28		63,717,485.90
	ጠቅላላ ድምር በብር	250,494,083.16	31,531,504.30		218,962,578.86
	በዶላር	23,055.00			23,055.00

<u>3.4 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት</u>

<u>የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የተጠቃለለ ሪፖርት</u>

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ **የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት** የ2015 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 31 መሥሪያ ቤቶች እና ሂሳብ አቅራቢ ያልሆኑ 3 ኮሌጆች በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡

በዕቅድ ከተያዙት መ/ቤቶች የ28 መ/ቤቶች እና የ3 ኮሌጆች ኦዲት ሥራ ተጠናቆ የኦዲት ሪፖርት ተልኳል፡፡ በፀጥታ ችግር ምክንያት የ1 መ/ቤት የኦዲት ሥራ የተቋረጠ ሲሆን የ2 መ/ቤቶች የኦዲት ሥራን ለማከናወን አልተቻለም፡፡

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች ረቂቅ የስራ አመራር ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው የሰጡትን ምላሾች መሰረት በማድረግ የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡

1. <u>የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን</u>

1.1. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ ከያዛቸው መ/ቤቶች የ28 መሥሪያ ቤቶች እና 3 ኮሌጆች ኦዲት በማድረግ የዕቅዱን 91% አከናውኗል፡፡

1.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2015 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	22/04/2016	624,613,400.00	1,304,000,000.00	1,928,613,400.00
2	አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	19/12/2015	692,783,500.00	1,032,172,936.69	1,724,956,436.69
3	የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር	27/04/2016	432,569,355.61	300,000,000.00	732,569,355.61
3.1	አርዳይታ የግብርና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	17/03/2016	145,198,754.00	15,000,000.00	160,198,754.00
3.2	ገዋኔ የግብርና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	22/02/2016	85,221,010.00	58,000,000.00	143,221,010.00
3.3	ሚዛን የግብርና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	30/12/2015	84,654,727.00	62,600,000.00	147,254,727.00
4	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	05/12/2015	582,429,000.00	450,930,460.00	1,033,359,460.00
5	የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	15/12/2015	92,513,895.00	145,651,950.00	238,165,845.00
6	ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ	30/12/2016	542,035,600.00	705,069,900.00	1,247,105,500.00
7	ቦረና ዩኒቨርሲቲ	30/12/2016	204,950,075.00	638,250,225.00	843,200,300.00
8	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ	07/02/2016	483,091,200.00	620,000,000.00	1,103,091,200.00
9	የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን	09/02/2016	23,623,088,719.00	840,000,000.00	24,463,088,719.00
10	የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች	14/01/2016	2,664,868,565.88	0.00	2,664,868,565.88

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	መደበኛ	ካፒታል	ድምር
	አገልግሎት				
11	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	19/04/2016	326054920.00	196,788,712.00	522,843,632.00
12	የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን	25/01/2016	76,330,325.00	0.00	76,330,325.00
13	የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን	02/12/2016	34,120,655.39	0.00	34,120,655.39
14	የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን	24/01/2016	154,236,926.34	0.00	154,236,926.34
15	የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን	28/12/2015	72,782,810.00	0.00	72,782,810.00
16	የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት	02/03/2016	278,073,680.59	684,357,989.00	962,431,669.59
17	ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ	26/04/2016	334,037,471	156,545,873.43	490,583,344.43
18	መቱ ዩኒቨርሲቲ	25/12/2015	459,117,921.00	670,000,000.00	1,129,117,921.00
19	የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር	21/04/2016	594,561,885.26	11,327,550,000.00	11,922,111,885.26
20	የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	21/01/2016	763,712,504.00	347,521,426.00	1,111,233,930.00
21	የሰላም ሚኒስቴር	10/12/2015	117,225,073.00	750,050,000.00	867,275,073.00
22	የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	22/02/2016	274,386,189.90	0.00	274,386,189.90

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	መደበኛ	ካፒታል	ድምር
23	ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ	30/12/2015	587,535,540.00	420,876,600.00	1,008,412,140.00
24	የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት	17/12/2015	249,370,576	454,365,000	703,735,576.00
25	የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	30/11/2015	117,193,507.64	0.00	117,193,507.64
26	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	04/04/2016	686,427,402.00	600,000,000.00	1,286,427,402.00
27	ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	26/02/2016	712,008,636.48	1,026,072,210.63	1,738,080,847.11
28	ወራቤ ዩኒቨርሲቲ	08/02/2016	532,613,790.00	614,754,683.77	1,147,368,473.77
		ድምር	**36,627,807,615.09**	**23,420,557,966.52**	**60,048,365,581.61**

1.3. የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ የሆነ አስተያየት ለ13 መ/ቤቶች (C)፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ13 መ/ቤቶች (E) እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ2 መ/ቤቶች (X) ተሰጥቷል፡፡ ለመ/ቤቶቹ በ2013 እና በ2014 የተሰጠው አስተያየት ለንጽጽር ቀርቧል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

2. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ የ2015 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

3. ተሰብሳቢ ሂሳብ

3.1. በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ

ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በ23 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር **1,992,899,328.99** በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ከመቻላቸውም በላይ

የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3.2. ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ

ግኝት

በ2 መ/ቤቶች (በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ) በድምሩ ብር 254,067,171.89 በተሰብሳቢ የተመዘገበ ቢሆንም መቼ በተሰብሳቢነት እንደተመዘገበና እያንዳንዱ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅና የቆይታ ጊዜዉን የሚገልፅ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቡ የተመዘገበበት ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢ ማስረጃ እንዲቀርብለትና ይህ ካልተቻለ ደግሞ በመመሪያው መሠረት ተገቢ የሂሳብ ማስተካከያ እንዲዘጋጅለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3. ከዕቃ አቅራቢዎች ተመላሽ ያልተደረገ ቅድሚያ ክፍያ

ግኝት

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ በአንቀጽ 30/1 የመንግስት መ/ቤቶች ከአቅራቢዎች ጋር የተፈራረሙበት ውሎች እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን እልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉን ማጠናቀቅ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 መ/ቤት (የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት) ለላብራቶሪ ዕቃዎች ግዢ ለአቅራቢ የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ሲወራረድ ማስረጃ ያልቀረበለት (ዕቃው ያልቀረበ) ብር 715,773.59 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከአቅራቢው የሚፈለገው የመንግሥት ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. የገቢ ሂሳብ

4.1. ያልተሰበሰበ ገቢ

4.1.1. የሥራ ግብር፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ግብር ክፍያ

ግኝት

ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓም ጀምሮ ተግባራዊ በተደረገው የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም ስለፌደራል የገቢ ግብር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 410/2009 መሠረት መሰብሰብ ያለበት ገቢ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶች የሥራ ግብር ብር 5,643,957.00፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 95,157.34 እና የቅድመ ግብር ክፍያ (withholding tax) ብር 200,411.82 በድምሩ ብር 5,939,526.16 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

ያልተሰበሰበው ገቢ ተሰብስቦ ለሚመለከተው የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ እንዲደረግና ለወደፊቱ የገቢ ሂሳብ መንግስት ባወጣው የገቢ ግብር አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.1.2. ከአቅራቢዎች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ

ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ላዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንደሌለበት ተገልጿል፡፡

በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ2 መቤቶች ከዕቃ አቅራቢዎች ጋር በተገባው ውል መሠረት ዕቃዎቹን ማስረከብ ባለባቸው ቀን ያላስረከቡ አቅራቢዎች

ላዘገዩበት ቀናት የጉዳት ካሳ ብር 170,180.21 እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ የዕቃ አቅራቢዎች ላይ የሚፈለገው የጉዳት ካሳ በውሉ መሠረት ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የተገዙ ዕቃዎች በወቅቱ ቀርበው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.2. <u>የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ከስፖንሰር ድርጅቶች የተሰበሰበ ገንዘብ ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 በክፍል 3 አንቀጽ 10 **የመንግስት ገንዘብ አሰባሰብ** ንዑስ አንቀጽ 1 በሕግ ካልተፈቀ በስተቀር ማናቸውንም የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብ አይቻልም፡፡ በንዑሱ አንቀጽ 2 ማናቸውንም የመንግስት ገንዘብ የሚሰበሰበው የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ብቻ ይሆናል፡፡ በንዑስ አንቀጽ 3 የመንግስት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ስልጣን የተሰጠው አካል የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ወደተጠቃለለው ፈንድ ገቢ ያደርጋል፡፡ ገንዘብ የተቀበለበትን እና ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ መዝግቦ ይይዛል፡፡ ዘዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ 1 መ/ቤት (የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር) ገንዘብ መሰብሰብ እንዲችል የሚመለከተውን የመንግስት አካል ሳይጠይቅና ሳያስፈቅድ **17ኛው አለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ** ለማካሄድ ከተለያዩ ድርጅቶች በስፖንሰር **ብር** 8,693,749.27.00 ሰብስቦ በመ/ቤቱ B የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገና ከተሰበሰበው ገንዘብ የተለያዩ ክፍያዎች የተፈጸሙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የሚመለከተው የመንግስት አካል ሳይፈቅድ ገንዘብ እንዳይሰበብ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እና ከድርጅቶቹ ተሰብስቦ ከወጪ ቀሪ

(Balance) ሆኖ የሚገኘው ሂሳብ በውስጥ ኦዲት ክፍል ተጣርቶ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት በአስቸኳይ ፈሰሥ ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. የወጪ ሂሳብ

5.1. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

ግኝት

የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም በንዑስ አንቀጽ 7 ማንኛውም ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ ሊቀርብና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,053,197.80 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ማስረጃ ላልቀረበላቸው የወጪ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ እንዲቀርብና ለወደፊቱም የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ የወጪ ሂሳብ እንዳይመዘገብ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.2. ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ከፋይናንስ ደንብና መመሪያ ውጭ (ቤት ለተሰጣቸው መምህራን የተከፈለ የቤት አበል፣ የቤት ኪራይ ቅጣት፣ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ቅጣት፣ የውሎ አበል ቅጽ ሳይሞላ የተከፈለ አበል፣ የመስክ ሥራ ሳይሄዱ የተከፈለ አበል፣ ለሰራተኞች ማበረታቻ የተከፈለ፣ ከመመሪያ ውጭ የጉባኤ ሥራ ለማስተባበር የተከፈለ፣ ከመመሪያ ውጭ ለብሔራዊ አብይ ኮሚቴ የተከፈለ፣ በሌላ መ/ቤት መሸፈን ለሚገባው ወጪ አላግባብ የተከፈለ …ወዘተ) በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 5,564,901.29 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ከመመሪያ ውጭ አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ የመ/ቤቶቹ ሥራ አመራር ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.3. በብልጫ የተከፈለ

ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች ለግንባታና ለተለያዩ ግዢዎች በድምሩ ብር 611,734.31 እና ለውሎ አበል፣ ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች በድምሩ ብር 191,295.00 በአጠቃላይ ድምር ብር 803,029.31 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ማሻሻያ ሀሳብ

በብልጫ የተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱም ክፍያዎች በጥንቃቄ እንዲፈጸሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.4. የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው እና ከታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የግዥ መመሪያ መሠረት እና እንዲሁም የገንዘብ ሚኒስቴር መስከረም 25 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር ገ/ኢ/1/53/86 በመንግስት ግዢ አፈጻጸምና ንብረት አወጋገድ ዙሪያ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮችን በተመለከተ ባስተላለፈው ሰርኩላር መሠረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በሁለት መ/ቤቶች የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ በብር 36,224,798.66 የቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤
2. በስድስት መ/ቤቶች ተከፋፍሎ በዋጋ ማወዳደሪያ የብር 12,418,320.38 ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤
3. በአንድ መ/ቤት ሌሎች የግዢ ሂደቶችን ያልተከተሉ ግዢዎች (ለጥቃቅን ግዢ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ የተፈጸመ) በብር 431,625.68 ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤

በድምሩ በብር 49,074,744.72 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሃሳብ**</u>

- መ/ቤቶች ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲፈጽሙ አሳስበናል፡፡
- በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት በማድረግ እንዲሁም በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ከተሳተፉት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ያቀረበው ዋጋ ጋር ተመሳክሮ ዋጋው የተጋነነ መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ግዥውን መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡
- የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት በመሆኑ አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እድል እንዲኖራቸው በዙር ሁሉም ሊሳተፉ የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባና ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበትና የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም እንደሚገባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.5. በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ገቢ ለተደረጉ ዕቃዎች የተፈጸመ የግዢ ክፍያ

ግኝት

የተገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (specification) መሰረት መቅረባቸውን ወይም አገልግሎት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2 መ/ቤቶች የተገዙት ዕቃዎች በናሙናውና በጥራት መቅረባቸው በቴክኒክ (ጥራት አረጋገጭ) ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ገቢ ተደርገው ብር 7,929,394.56 የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ዕቃዎች በትክክል ለመቅረባቸው ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች (የጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ) የፅሁፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ የግዢ ክፍያ እንዳይፈጸም አሳስበናል፡፡

5.6. ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ

ግኝት

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የተገዛ ዕቃ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ3 መ/ቤቶች የተገዙት ዕቃዎች ገቢ ለመደረጋቸው የዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ሳይቀርብ **ብር 931,089.25** የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ክፍያ የተፈጸመባቸው ዕቃዎች ገቢ ያልተደረገቡት ሁኔታ ተጣርቶ ዕቃዎቹ ለመ/ቤቶቹ ገቢ እንዲደረጉ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ እና ይህ ካልተቻለ ደግሞ ገንዘቡ ተመላሽ ሆኖ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

5.7. በአማካሪ መሃንዲስ ሳይረጋገጥ የተፈጸመ የግንባታ ሥራ ክፍያ

ግኝት

በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ 5ሀ ለግንባታ ዘርፍ መሰረተ ልማት ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ

ከአማካሪ መሃንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 መ/ቤት (የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር) በድምሩ ብር 169,777,652.22 የግንባታ ሥራ ክፍያ በአማካሪ መሃንዲስ ሳይረጋገጥ የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ከፍተኛ በጀት የሚጠይቁ የግንባታ ሥራዎች የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ በሌላቸው ባለሙያዎች እንዳይሠሩ እንዲደረግ፤ ያለ አማካሪ መሃንዲስ በመ/ቤቱ እየተከናወኑ ለሚገኙ የግንባታ ሥራዎች ህጋዊ አማካሪ ድርጅቶች እንዲመደብላቸው እንዲደረግ እና በአማካሪ መሃንዲስ ሳይረጋገጥ የተፈፀመውም ክፍያ ትክክለኛነት በባለሙያ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

5.8. <u>በአግባቡ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሳብ በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት በአግባቡ መፈጸሙንና በትክክል መመዘገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ1 መ/ቤት ብር 56,178,158.97 የወጪ ሂሳብ በድጋሚ የተመዘገበ መሆኑ፤ በ1 መ/ቤት ብር 655,715.20 የወጪ ሂሳብ በብልጫ የተመዘገበ መሆኑ እና በ1 መ/ቤት ብር 1,203,002.60 የወጪ ሂሳብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለሂሳቦቹ ተገቢ የሂሳብ ማስተካከያ መስራት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግስት መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙና በትክክል እንዲመዘገቡ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.9. <u>ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተመዘገበ ወጪ</u>

<u>ግኝት</u>

በ10 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 30,072,138.92 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ መኖሩ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በ2015 በጀት ዓመት በዕቅድ ለተያዙ ስራዎች ማከናወኛ ከተፈቀደው በጀት የቀድሞው በጀት ዓመት ክፍያ መፈጸሙ መ/ቤቶቹ የበጀት ህጉን ተከትለው አለማከናወናቸውን እንደሚያመለክት ጠቁመን ክፍያዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ እና ተገቢው የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.10. በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ

ግኝት

የገንዘብ ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሠረት የወጪ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ11 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 38,349,758.27 የወጪ ሂሳብ በትክክለኛው የወጪ ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ማንኛውም ሂሳብ በትክክለኛ የሂሳብ መደብ (ኮድ) መመዝገቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.11. በሚመለከተው ኃላፊ ሳይጸድቅ የተፈጸመ ክፍያ

ግኝት

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 በአንቀጽ 7/1 የማጭበርበር ወይም የስህተት ስጋቶችን ለመቀነስ በአንድ ሰዉ በመከናወናቸው ምክንያት ለጥፋትና ለስነ ምግባር ችግር ሊጋለጡ የሚችሉ ስራዎችና ኃላፊነቶች በተለያዩ ሰዎች መሰራት እንዳለባቸዉ ይገልጻል፡፡
በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 ዩኒቨርሲቲ (ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ) ለመምህራን የሙያ አገልግሎት የተከፈለው ብር 909,150.00 በክፍያ ማዘዣዎች ላይ የሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈርም (ወጪው ሳይፀድቅ) በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የተጠቀሰው ክፍያ ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት የዋለ መሆኑ ተረጋግጦ ወጪው በሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ እንዲፀድቅ ማድረግ እንደሚገባ እና ለወደፊቱም የወጪ ሂሳብ በሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ ሳይጸድቅ ምንም አይነት ክፍያ እንዳይፈጸምና ሂሳቡ እንዳይመዘገብ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.12. በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደና በወጪ የተመዘገበ

ግኝት

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በክፍል ሁለት አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 7 ለተገዛ እቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ህጋዊና ኦርጂናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 ዩኒቨርሲቲ (ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ) ለዕቃ ግዢ ለተከፈለ ብር 1,804,936.67 የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው ሂሳቡ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳብ ማወራረድና መመዝገብ ሂሳቡ በድጋሚ ክፍያ ሊጠየቅበት የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚችል ጠቁመን፣ ለተጠቀሰው ሂሳብ ከድርጅቱ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.13. ከመደበኛ በጀት መከፈል ሲገባው ከውስጥ ገቢ የተፈጸመ ክፍያ

ግኝት

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 የመንግስት ሂሳብ አያያዝ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ስርዓት መሰረት የተፈቀደላቸውን በጀትና የወጣውን ወጪ ማሳየት እንዲችሉ ተለይቶ በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 መ/ቤት (የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት) ለመደበኛ ሥራ ማከናወኛ የተከፈለ ብር 1,293,772.95

ከመደበኛ በጀት መከፈል ሲገባው ከውስጥ ገቢ ሂሳብ የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መ/ቤቱ የመንግሥት ደንብና መመሪያዎችን ጠብቆ ሥራውን ማከናወን እንደሚገባው ጠቁመን ለመደበኛ ስራ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.14. ለተጨማሪ ሥራ የውል ስምምነት ሳይገባ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ ግኝት

የፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 በፊደል ተራ "መ" በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ አሸነፊው ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል የመጀመሪያው ግዥ የተከናወነባቸው ዓይነት ተመሳሳይ ሥራዎች ወይም አቅርቦቶች በድጋሚ እንዲሰሩ ወይም እንዲቀርቡ ማድረግ ሲያስፈልግ ተጨማሪ ውል መፈፀም እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ 25.11 የመንግስት መ/ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፅመው ግዥ የውል ስምምነት መፈረም እንዳለበት ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 መ/ቤት (የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር) ለቢሮ እድሳት ሥራ የተጨማሪ ስራ (Supplementary work) ትዕዛዝ የተሰጠ ሲሆን ለተጨማሪ ሥራው የውል ስምምነት መፈረም ሲገባው ውል ሳይገባ ለተጨማሪ የግንባታ ሥራው **ብር 3,917,074.99** የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ተገቢ የውል ስምምነት ተገብቶ እንዲፈረም ማድረግ እንደሚገባና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

5.15. የግንባታ ሥራ የጥራት ዋስትና መያዣ (Retention) ሳይቀነስ የተፈጸመ ክፍያ፤

ግኝት

የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ በክፍል 7 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 28.5 በፊደል ለ/ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 16.26.9 ከተመለከተው በተጨማሪ ለማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሰረት ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ስራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% (አምስት በመቶ) በመያዣ መልክ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም በፊደል ሐ/ የግንባታ ስራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ አንቀፅ በፊደል ተራ (ለ) መሰረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% ለስራ ተቋራጩ ይለቀቃል፤ ቀሪው 50% ለአንድ ዓመት የጥገና ጊዜ ተይዞ እንደሚቆይ ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 ዩኒቨርሲቲ (ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ) ለተለያዩ የሕንጻ ሥራ ተቋራጮች ጋር የግንባታ ሥራ ክፍያ ሲፈጸም ከክፍያው ላይ በድምሩ **ብር 966,197.34** የግንባታ ሥራ የጥራት ዋስትና መያዣ (Retention) ያልተቀነሰ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከሥራ ተቋራጮች ክፍያ ላይ የጥራት ዋስትና መያዣ ገንዘብ በመመሪያው መሠረት በአግባቡ መቀነስ እንደሚኖርበት፤ ሂሳቡም በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ ሌጀር እና ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶለት መመዝገብ እንደሚገባው እና ያልተቀነሰው የመያዣ ሂሳብ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ቀጣይ ክፍያ ላይ እንዲቀነስ እሳስበናል፡፡

5.16. አላግባብ በወጪ የተመዘገበ የግንባታ መያዣ ተመላሽ ክፍያ

ግኝት

የፌዴራል መንግስት ግዥ አፋጻጸም መመሪያ ክፍል 6 አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀጽ 5 ፊደል ለ የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የሚስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈፀመው ከእያንደንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራ ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% በመያዣ መልክ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በፊደል ሐ የግንባታው ሥራው ሲጠናቀቅ እና ጊዚያዊ ርክክብ ሲደረግ ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% ለሥራ ተቋራጩ ይለቀቃል፡፡ ቀሪው 50% ለአንድ ዓመት የጥገና ጊዜ ተይዞ ይቆያል፡፡

ሆኖም የሥራ ተቋራጩ ለ12 ወራት የሚቆይ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረት ዋስትና ካቀረበ የተያዘው ገንዘብ ሊለቀቅለት ይችላል፡፡ በዚሁ መሠረት ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በ1 መ/ቤት (የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር) ለአንድ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ የግንባታ መያዣ ክፍያ (Retention) **ብር 44,755,532.47** ተመላሽ ሲደረግ የመያዣ ተከፋይ በሂሳብ መደብ 6175101 (5061) በዴቢት (Debit) መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 2311208 (6324) የግንባታ ሥራ ክፍያ አላግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለሂሳቡ ተገቢ የሂሳብ ማስተካከያ እንዲዘጋጅ እና ለወደፊቱም የሂሳብ እንቅስቃሴዎች በመመሪያው መሠረት በጥንቃቄ እንዲመዘገቡ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. ተከፋይ ሂሳብ

6.1. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ

ግኝት

የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በ15 መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተከፈለ) ብር 79,473,085.21 ውዝፍ ተከፋይ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ ለባለመብቶች አለመክፈል ተጠያቂነትን ሊያስከትል እንደሚችል ጠቁመን ውዝፍ ተከፋይ ሂሳቦች እንዲወራረዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.2. በተከፋይ የተመዘገበና ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ

ግኝት

በ2 መ/ቤቶች (በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና በመስኖና ቆላማ አካባቢ አካባቢ ሚኒስቴር) በድምሩ ብር 1,679,720,098.80 ተከፋይ ሂሳብ በተከፋይ የተያዘበት ጊዜና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅና ማስረጃ የሌለው መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ተከፋይ ሂሳቡ የተመዘገበበት ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢ ማስረጃ እንዲቀርብለትና ይህ ካልተቻለ ደግሞ በመመሪያው መሠረት ተገቢ የሂሳብ ማስተካከያ እንዲዘጋጅለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3. <u>ያልተመዘገበ የግንባታ መያዣ (Retention) ተከፋይ ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት ግዥ አፋጻጸም መመሪያ ክፍል 6 አንቀፅ 28.5 የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የሚስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈፀመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራ ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% በመያዣ መልክ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 8 የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ንዑስ አንቀፅ 5(ሀ) ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈፀምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለባቸው፣ እንዲሁም በዚሁ ንዑስ አንቀፅ (ለ) የተከፋይ ሂሳብ እንቅስቃሴዎች በእለቱ የሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 መ/ቤት (የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር) ለቢሮ እድሳት ሥራ ለተለያዩ ሥራ ተቀራጮች ከተፈጸመው ክፍያ የተቀነሰው የመያዣ ሂሳብ (Retention) **ብር 9,025,910.01** በተከፋይ ሂሳብ መደብ 6175101 (5061) መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለግንባታ ሥራ ጥራት ዋስትና የተያዘው የመያዣ ሂሳብ በወቅቱ እንዲመዘገብና በተቋራጮቹ ስም ተቀፅላ ሌጀር እንዲዘጋጅ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7. በጀት

7.1. የበጀት አጠቃቀም

ግኝት

ኦዲት በተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2015 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን በተለያዩ የሂሳብ ኮዶች ከመደበኛ እና ከካፒታል በጀት በድምሩ ብር 609,738,799.69 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን እንዲሁም በተለያዩ የሂሳብ ኮዶች ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 92,137,714.58 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መ/ቤቶቹ የተፈቀደላቸውን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሠረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የመ/ቤቶቹ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7.2. በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው የበጀት ሰራተኛ ሳያረጋግጥ የተፈጸመ ክፍያ

ግኝት

የገንዘብ ሚኒስቴር ነሃሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ እና እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 ማናቸውም የሳጥንና የባንክ ሂሳብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ መረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በ1 ዩኒቨርሲቲ (ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ) ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ የወጪ ማስመስከሪያ ቫውቸሮች ላይ የሚመለከተው የበጀት ሰራተኛ በፊርማ ሳያረጋግጥ በድምሩ ብር 9,689,756.38 የተከፈለ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለወጪው በጀት የተያዘ ስለመሆኑ በወጪ ማስመስከሪያ ቫውቸር ላይ የሚመለከተው የበጀት ሰራተኛ በፊርማ እንዲያረጋገጥ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

8. <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር</u>

8.1. <u>ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ግኝት</u>

የንብረት አያያዝና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተመለከቱት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	**መ/ቤቶች**			**ቅ/ጽ/ቤቶች**
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ ***አባሪ 8/1 ሀ***	• ባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት • ቦረና ዩኒቨርሲቲ • የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን • ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ			
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ ***አባሪ 8/1 ረ***	• ቦረና ዩኒቨርሲቲ • ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ			
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች ***አባሪ 8/1 ሰ***	**የመ/ቤቱ ስም**	**የእቃው ዓይነት**	**መለኪያ**	**ብዛት**
	1. አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	የተለያዩ ጠረጴዛዎች	በቀጥር	169
		የፕላስቲክ ወንበር	››	268
		የተማሪ ሎከር	››	434
		የእንጨት ወንበር	››	617
		የብረት ጠረጴዛ	››	64
		ዊል ሸልፍ	››	62
		የዳቦ ፓትራ	››	172
		ዩፒኤስ	››	179
		የስልክ ቀፎ	››	86
		ላፕቶፕ ኮምፒተር	››	177
		ዴስክ ቶፕ ኮምፒተር	››	54
	2. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር	ባለ32 inch ቲቪ	በቁጥር	8
		DELL ኮምፒዩተር	››	6
		Lenovo ኮምፒዩተር	››	2
		የፕሪንተር ቀለም	››	150
		ላፕቶፕ ኮምፒዩተር	››	5
		ጥቅል የዲሽ ኬብል	››	18
		የህጻናት ፍራሽ	››	10

<table>
<tr><th>የግኝቶች መግለጫ</th><th colspan="3">መ/ቤቶች</th><th>ቅ/ጽ/ቤቶች</th></tr>
<tr><td>ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ

አባሪ 8/1 ሀ</td><td colspan="3">• ባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
• ቦረና ዩኒቨርሲቲ
• የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን
• ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ</td><td></td></tr>
<tr><td>ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ
አባሪ 8/1 ረ</td><td colspan="3">• ቦረና ዩኒቨርሲቲ
• ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ</td><td></td></tr>
<tr><td rowspan="18">ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች

አባሪ 8/1 ሰ</td><td>የመ/ቤቱ ስም</td><td>የእቃው ዓይነት</td><td>መለኪያ</td><td>ብዛት</td></tr>
<tr><td rowspan="11">3. አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ</td><td>የተለያዩ ጠረጴዛዎች</td><td>በቀጥር</td><td>169</td></tr>
<tr><td>የፕላስቲክ ወንበር</td><td>››</td><td>268</td></tr>
<tr><td>የተማሪ ሎከር</td><td>››</td><td>434</td></tr>
<tr><td>የእንጨት ወንበር</td><td>››</td><td>617</td></tr>
<tr><td>የብረት ጠረጴዛ</td><td>››</td><td>64</td></tr>
<tr><td>ዌል ሸልፍ</td><td>››</td><td>62</td></tr>
<tr><td>የዳቦ ፓትራ</td><td>››</td><td>172</td></tr>
<tr><td>ዩፒኤስ</td><td>››</td><td>179</td></tr>
<tr><td>የስልክ ቀፎ</td><td>››</td><td>86</td></tr>
<tr><td>ላፕቶፕ ኮምፒተር</td><td>››</td><td>177</td></tr>
<tr><td>ዴስክ ቶፕ ኮምፒተር</td><td>››</td><td>54</td></tr>
<tr><td>4. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር</td><td>ባለ32 inch ቲቪ</td><td>በቁጥር</td><td>8</td></tr>
<tr><td rowspan="5"></td><td>DELL ኮምፒዩተር</td><td>››</td><td>6</td></tr>
<tr><td>Lenovo ኮምፒዩተር</td><td>››</td><td>2</td></tr>
<tr><td>የፕሪንተር ቀለም</td><td>››</td><td>150</td></tr>
<tr><td>ላፕቶፕ ኮምፒዩተር</td><td>››</td><td>5</td></tr>
<tr><td>ጥቅል የዲሽ ኬብል</td><td>››</td><td>18</td></tr>
</table>

		የህጻናት ፍራሽ	››	10
		የተለያዩ ቶነሮች	››	በርካታ
		የፎቶ ኮፒ ማሽኖች	››	››
		ስካነሮች	››	››
		የካፌ ፕላስቲክ ወንበሮች	››	››
		በርሜሎች	››	››
		የምግብ ሰርቪሶች	››	››
		ሲኒዎች	››	››
		ሰሃኖች	››	››
		ብረት ድስቶች	››	››
		የብረት ምድጃ	››	››
		የሻይ ማሽን	››	››
		ኦቨኖች	››	››
		ፍሪጆች	››	››
		የእንጅራ ምጣዶች	››	››
		ተሽከርካሪ ወንበሮች	››	››
		ጠረጴዛዎች	››	››
		የፋይል ካቢኔቶች	››	››
	5. ሚዛን የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	አልጋ	በቁጥር	6
		ፍራሽ		6
		የማር መጫጃ ማሽን		1
		የማር ማጣሪያ		1
		የላብራቶሪ ዕቃ መቀቀያ		1
		ብረት ድስት		7
		የኢንሴክት መያዣ		12
		SAMSUNG 43		1

		Inch TV		
		PANASONIC 32 Inch TV		2
	6. አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	ሞንታርቦ	በቁጥር	10
		የእህል ወፍጮ	››	2
	7. ቦረና ዩኒቨርሲቲ	የዳቦ መጋገሪያ ማሽን	በቁጥር	2
		የሽንኩርት መላጫ ማሽን	››	1
		የድንች መላጫ ማሽን	››	1
		የቲማቲም መፍጫ ማሽን	››	1
	8. የፌዴራል ተክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት	ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች	በቁጥር	8
		የዶሮ መመገቢያ ዕቃ	››	23
		የወተት ሙቀት መለኪያ ቴርሞሜትር	››	10
		የወረቀት መቁረጫ	››	4
		የወረቀት ትሪ	››	10
	9. ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ	የሴት ቆዳ ጫማ	በቁጥር	58 ጥንድ
		የሴት ቡትስ ጫማ	››	5 ጥንድ
		የወንድ ሸሚዝ	››	56
		የወንድ ሱሪ	››	56
		ኮፍያ	››	74
		የደንብ ልብስ ጨርቅ	ሜትር	48
	8. መቱ ዩኒቨርሲቲ	የዳቦ ሊጥ ማቡኪያ	በቁጥር	1
		የዳቦ መጋገሪያ ማሽን	››	1
		ፍሪጅ	››	5

		የውሃ ማሞቂያ ማሽን	››	2
		የተሽከርካሪ ጎማ	››	54
		ፍራሽ	››	በርካታ
		ትራስ	››	››
	9. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	የዳታ ሴንተር እና የኔትዎርክ ዕቃዎች	በቁጥር	በርካታ
		የመኪና ጎማ	››	››
		ካሜራዎች	››	››
		ላፕቶፕ ኮምፒዩተር	››	››
		ፕሪንተሮች	››	››
		ዴስክቶፕ ኮምፒዩተር	››	››
		ራኮች	››	››
		የእሳት ማጥፊያ	››	››
		የስልክ ቀፎ	››	››
		አዳፕተር	››	››
		ጠረጴዛዎች	››	››
		የሰርቨር ራኮች	››	››
		የእንግዳ ወንበር	››	››
		ጠረጴዛዎች	››	››
		ዩፒኤስ	››	››
		ሶኬቶች	››	››
		የኮምፒዩተር አክሰሰሪዎች	››	››
		ተሽከርካሪ ወንበሮች	››	››
	10. የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	የተለያዩ ልብሶች	በቁጥር	በርካታ
		ብርድ ልብስ	››	>>
		የተለያዩ የቤት	››	>>

		ዕቃዎች		
		ዊልቼር	››	31
		ክራንች	››	49
		ኖርማል ዎከር	››	17
	11. የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት	የፕሪንተር ቀለሞች	በቁጥር	18
		ሽሚዝ	››	30
		የሴት ጫማ	››	27 ጥንድ
		የወንድ ጫማ	››	17 ጥንድ
		የበር ቁልፍ	››	149
		አምፖሎች	››	በርካታ
		የኤሌክሪክ ገመዶች	››	>>
	12. ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	የፕሪንተር ቀለሞች	በቁጥር	343
		የፎቶ ፍሬም	››	300
		የዳቦ መጋገሪያ ማሽን	››	1
		የስጋ መፍጫ	››	4
		የሸንኩርት መፍጫ	››	3
	13. ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	የላብራቶሪ ማሽን	በቁጥር	1
		የዕቃ ማጠቢያ ማሽን	››	1
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው *አባሪ 8/1 ሸ*	• አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ • አዳማ ሳይንሰና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ • የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር • አርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ • ገዋኔ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ • ሚዛን የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ • አሶሳ ዩኒቨርሲቲ • የባዮ እና ኢመርጂነገ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት • ቦነንጋ ዩኒቨርሲቲ • ቦረና ዩኒቨርሲረቲ • ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቴ • የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን • የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን • የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን • የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት • ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ • መቱ ዩኒቨርሲቲ			

<table>
<tr><td></td><td colspan="2">• የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
• የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
• ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ
• የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት
• ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
• ወልቂጤ ዩኒቨርሲቴ
• ወራቤ ዩኒቨርሲቲ</td><td></td></tr>
<tr><td>ተያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰው ተደርበው የሚከናወኑባቸው

አባሪ 8/1 ቀ</td><td colspan="2">• የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
• ገዋኔ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
• ሚዛን የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
• ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ</td><td></td></tr>
<tr><td rowspan="2">ከመ/ቤቱ የለቀቁ ሰራተኞች (ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ
አባሪ 8/1 በ</td><td>**የመ/ቤቱ ስም**</td><td>**የንብረቱ ዋጋ**</td><td>**የሰራተኞች ብዛት**</td></tr>
<tr><td>ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ</td><td>940,173.01</td><td>67</td></tr>
<tr><td>ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች

አባሪ 8/1 ቸ</td><td colspan="2">• ሚዛን የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
• አሶሳ ዩኒቨርሲቲ
• ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ
• የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት</td><td></td></tr>
<tr><td>ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ መቀመጣቸው

አባሪ 8/1 ዘ</td><td colspan="2">• የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
• የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
• የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን</td><td></td></tr>
<tr><td>በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎች ዋጋ ያልተመኑ መሥሪያ ቤቶች፤

አባሪ 8/1 ዠ</td><td colspan="2">• ቦረና ዩኒቨርሲቲ</td><td></td></tr>
<tr><td>የአገልግሎት ግዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች በስቶር የሚገኙባቸው መ/ቤቶች

አባሪ 8/2 ከ</td><td colspan="2">• አርዳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ
• አሶሳ ዩኒቨርሲቲ</td><td></td></tr>
</table>

የማሻሻያ ሀሳብ

ዕቃዎች በአግባቡ እንዲመዘገቡና በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውሉ፤ በግምጃ ቤት ውስጥ በአግባቡ እንዲጠበቁ፤ የተበላሹ ዕቃዎች በወቅቱ እንዲጠገኑና መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

9. የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም

ግኝት

የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተመለከቱት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	የመ/ቤቱ ስም	የተሽከርካሪዎች ብዛት	
		መኪና	ሞተር ብስክሌት /ሌሎች*
ሊብሬ ያልቀረበላቸው *አባሪ 8/2 ሀ*	1. ገዋኔ የግብርና ቴክኒክ ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ		7
	2. አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	1	
	3. ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ	6	
	4. የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	1	
	5. የፌዴራል የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት	4	
	6. የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር	1	
	7. ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ	2	
	ድምር	15	7
ያለአገልግሎት ወይም በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው መ/ቤቶች *አባሪ 8/2 ለ*	1. አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	3	
	2. የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን	1	
	3. የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን	1	
	4. የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር	5	
	5. ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ	3	
	6. የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	1	
	ድምር	14	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	1. አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	14	
	2. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር	1	

አባሪ 8/2 ሠ	3. አርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	2	
	4. አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	2	
	5. የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	1	
	6. የኢትዮያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	1	
	7. የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን	1	
	8. የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን	2	
	9. ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ	9	
	10. የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር	39	
	11. ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ	2	
	12. የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት	2	
	ድምር	**76**	
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው (ጌጅ) የማይሰራ	1. አርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	4	
	2. የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን	2	
አባሪ 8/2 ሸ	**ድምር**	**6**	
አገልግሎት የማይሰጡ/መወገድ/ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች *አባሪ 8/2 ቸ*	1. አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	11	
	2. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር		2
	3. አርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	19	
	4. ገዋኔ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ➢ 1 መኪና ➢ 2 ትራክተር ➢ 5 ሞተር ሳይክል	3	5
	5. አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	5	1

	6. የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን	28	
	7. የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት	2	1
	8. የሰላም ሚኒስቴር	10	
	ድምር	**78**	**9**

የማሻሻያ ሀሳብ

የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) ለሌላቸው ሊብሬ እንዲወጣላቸው፤ በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ እንዲደረግ፤ ሊብሬያቸው በሌላ መ/ቤት ስም የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች በመ/ቤቶቹ ስም ሊብሬ እንዲወጣላቸው እንዲደረግ፤ የኪሎ ሜትር ቆጣሪያቸው (ጌጅ) ለማይሰራው ተሽከረካሪዎች አዲስ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ (ጌጅ) እንዲቀየርላቸው፤ መወገድ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች በመንግስት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ እና ተሽከርካሪዎች በፌደራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ እንዲውሉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10. የክትትል ኦዲት

10.1. እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች

ግኝት

ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በ22 መ/ቤቶች ለመንግስት ካዝና ተመላሽ መደረግ ያለበት ብር 43,055,286.75 ተመላሽ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡
- በ11 መ/ቤቶች የተሟላ የሰነድ ማስረጃ ሊቀርብለት ለሚገባ ብር 1,942,552,951.48 የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የተጠቀሰው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ እና የተሟላ ማስረጃ ላልቀረበለት ሂሳብ የተሟላ የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

11. <u>ልዩ ልዩ</u>

11.1. <u>ኦዲታቸው የተቋረጠ እና ኦዲታቸው ያልተጀመረ መ/ቤቶች</u>

- በፀጥታ ችግር ምክንያት የ1 መ/ቤት የኦዲት ሥራ ተቋርጧል፡፡
- በፀጥታ ችግር ምክንያት የ2 መ/ቤቶች የኦዲት ሥራ ሊከናወን አልተቻለም፡፡

3.5 የልማትና ማህበራዊ ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ

መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የልማትና ማህበራዊ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2015 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 29 መ/ቤቶችና 10 ለተጠሪ ተቋማት ሪፖርት የሚያቀርቡ መሥሪያ ቤቶች በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡ መ/ቤቶቹ በሙሉ ረቂቅ የስራ አመራር ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው የሰጡትን ምላሾች መሰረት በማድረግ 31 የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት ለ 34 መ/ቤቶች እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡

<u>የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን</u>

1.2. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን መ/ቤቶች በሙሉ ኦዲት በማድረጉ በቁጥር ኦዲቱ የዕቅዱን 100 % የሸፈነ ሲሆን በበጀትም 100 % ነው፡፡

2.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2015 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

የበጀት ማጠቃለያ

ተ/ቁ	ልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች	መደበኛ	ካፒታል	የውስጥ ገቢ	ጠቅላላ ድምር
1	የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር	424,361,796.00	2,046,200,000.00		2,470,561,796.00
2	የኢትጵያ ደን ልማት ኢንስቲትዩት	279,642,958.50	130,000,000.00		409,642,958.50
3	የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን	79,910,422.50	-		79,910,422.50
4	የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት	1,360,019,350.00	-		1,360,019,350.00
5	የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	61,977,887.00	138,399,760.00		200,377,647.00
6	የኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒት ባለሥልጣን	378,454,217.23	17,519,000.00		395,973,217.23
7	የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት	115,485,417.00	778,421,593.23		893,907,010.23
8	የኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን	69,340,155.00	-		69,340,155.00
9	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	288,303,365.90	-		288,303,365.90
10	የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን	93,295,262.00	50,000,000.00		143,295,262.00
11	የኢትዮጵያ እንሰሳት ልማት ኢንስቲትዩት	154,811,707.30	29,346,099.24		184,157,806.54
12	የኢትዮጵያ የእንሰሳት ጤና ኢንስቲትዩት	155,615,732.00	20,720,760.00		176,336,492.00

13	አማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	201,865,889.78			201,865,889.78
14	የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን	141,055,562.00	48,739,800.00		189,795,362.00
15	አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	433,164,998.00		30,000,000.00	463,164,998.00
16	የማዕድንና ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	81,044,700.00			81,044,700.00
17	የኢትዮጵያ የደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት	109,872,680.00			109,872,680.00
18	ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	447,429,526.15	4,820,000.00		452,249,526.15
19	የኢትዮጵያ ውኃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	40,194,478.00	46,885,782.00		87,080,260.00
20	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት	85,162,400.00	12,000,000.00		97,162,400.00
21	የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልገሎት	262,400,000.00			262,400,000.00
22	ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት	107,274,286.91	100,000,000.00		207,274,286.91
23	ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል	288,792,287.85			288,792,287.85
24	በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር	640,095,872.73	2,503,581,377.30		3,143,677,250.03
25	የኢትጵያ ኮንስትራከሽን ባለሥልጣን	116,915,168.00	-		116,915,168.00
26	ማዕድን ሚኒስቴር	58,219,162.00	60,000,000.00		118,219,162.00
27	ጤና ሚኒስቴር	5,793,029,790.00	5,987,499,290.00		11,780,529,080.00
28	ታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት		-		

	ጽ/ቤት				
29	ግብርና ሚ/ር	1,724,541,261.50	5,660,911,462.39		7,385,452,723.89
30	ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል	195,975,871,060.00	-		195,975,871,060.00
31	ግብርና ትራንስፎርሜሽን	87,227,742.55	-		87,227,742.55
	-	**210,055,375,135.90**	17,635,044,924.16	30,000,000.00	227,720,420,060.06

2.3. የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ የሆነ ነቀፌታ የሌለበት ኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 20 መሥሪያ ቤቶች፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 9፣ የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት 1 መቤት እና አስተያየት መስጠት ያልተቻለበት 1 መ/ቤት ነው፡፡

2. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ የ2015 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.1 ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.2.2 በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ

ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ

አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በ27 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 8,171,141,833.28 በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፣ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

2.2.2. ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ግኝት

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁንና በ5 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 28,486,737.33 የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርት የተሰብሳቢ ሂሳብ የእርጅና ትንተና ላይ በተገለጸው መሰረት ማስረጃ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋጥ አልተቻለም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በተሰብሳቢ ሂሳብነት የተመዘገው ሂሳብ በተገቢው ማስረጃ ሊደገፍ ይገባል፡፡ በመሆኑም ለኦዲት ያልቀረቡ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሰነዶች ሊቀርቡ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.2.3 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

ግኝት

የፌዴራል መንግስት መስሪያቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2.የወጪ ሂሳብ አያያዝ በፊደል ለ/ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪዉ የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለዉ አካል መፈቀድ አለበት ይላል፡፡

እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 በንኡስ አንቀጽ12/ በተገባው ውል መሰረት የሚከፈል ወጪ ከሆነ ሥራው መጠናቀቁን፤የዕቃው ርክክብ መፈጸሙን ወይም አገልግሎት መሰጠቱን መረጋገጥ እንደለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በ4 መ/ቤቶች የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 7,016,570.32 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በተሰብሳቢ መያዝ የነበረበት የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በወጪ ተመዝግቦ መከፈሉ አግባብነት ስለለሌው ጉዳዩ ተጣርቶ በተሰብሳቢ ተይዞ ለአቅራቢው ከሚከፈለው ክፍያዎች ላይ በመመሪያው መሰረት ሊቀነስ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ማንኛውም ክፍያ ተረጋግጦ እና ተጣርቶ ምዝገባው መከናወን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2..2..4 ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ ያልተደረገ ሂሳብ፤-

ግኝት

የትምህርት ዕድል ተጠቃሚዎች ግዴታቸውን በውሉ መሰረት የሚፈጽሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጤና ሚኒስቴር በድምሩ ብር 1,869,744.20 ግዴታቸውን በውሉ መሰረት ባለመፈጸማቸው እንዲሁም ህጋዊ ወለዱን እና ቅጣቱን ለመ/ቤቶቻቸው መክፈል ሲገባቸው አለመክፈላቸው ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የትምህርት ዕድል ተጠቃሚዉ የሚጠበቅበትን ግዴታ ካልተወጣ ለትምህርት የወጣው ወጪ እና የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም ከግለሰቦቹ ላይ የሚፈለግባቸው የገንዘብ መጠን ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ በላክነው ሪፖር አሳስበናል፡፡

2.2.5 በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ

ግኝት

የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ስለ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል 4.21.1 የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት አዲስ ተመን ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ በኩል ለሚኒስትሮች ም/ቤት አቅርበው ማጸደቅ እንደሚኖርባቸው የተገለጸ ቢሆንም የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎትና በቡናና ሻይ ባለስልጣን በድምሩ ብር 25,502,727.25 በመመሪያው መሰረት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማጸደቅ ገቢውን መሰብሰብ ሲገባው ባልጸደቀ የአገልግሎት ክፍያ ገቢ እየሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 4/16 ቀርቧል፡፡**

የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ባልጸደቀ መመሪያ መሰብሰብ ስለማይቻል አዲስ የቀረበው ረቂቅ የአገልግሎት ክፍያ ተመን አፀድቆ ስራ ላይ እንዲውል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2. የወጪ ሂሳብ

2.1 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በ16 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 17,465,026.87 ስራ ላይ ለመገኘታቸው የፈረሙበት ማስረጃ ሳይቀርብ እንዲሁም የተሳታፊዎች ስም ዝርዝር እና ፊርማ (Attendance) ሳይቀርብ ለመስተንግዶ የተከፈለ የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ሳይቀርብ በአጠቃላይ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎች መከፈል የሚገባቸው የተሟላ ማስረጃ ሲቀርብ መሆኑንና ይህ የማይሆን ከሆነ ተመላስ መደረግ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

2.2 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,364,265.00 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ሲሆኑ ይህም የማእድንና ኢንዱስትሪ ልማት ኢኒስቲትዩትና የኢትዮጲያ አካል ድጋፍ አገልግሎት መ/ቤቶች ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ነው፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ የወጪ ሂሣብ እንዳይወራረድ ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ እና ያለበቂ ማስረጃ በወጪ ለተመዘገበው ሂሣብ በአስቸኳይ ተገቢ ማስረጃ እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.3 ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ከፋይናንስ ደንብና መመሪያ ውጭ (ለተለያዩ ተቋማት የተፈጸመ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ የደንብ ልብስ ማስፈያ፣ የመ/ቤቱ ሰራተኛ ላልሆኑ የተከፈለ ውሎ አበል፤የህክምና መዋጮ በ6 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 512,769.22 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ የመ/ቤቶቹ ሥራ አመራር ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.4 ከመስሪያ ቤቱ ለለቀቁ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ

ግኝት

በተለያዩ 6 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 103,370.29 ከስራ ለለቀቁ ሰራተኞች ያለአግባብ ደመወዝ የተከፈላቸው መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ክፍያዎች ከደንብና መመሪያ ውጪ በብልጫ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡ ለወደፊቱም በደመወዝ ክፍያ ወቅት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.5 <u>በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያልተፈቀደ የቀንና ኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር ግኝት</u>

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው የሚገኙ ሰራተኞችን ቋሚ ለማድረግ በወጣው አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ቅጥር እንደማይፈፀም እንዲሁም ቅጥር ፈጽሞ የተገኘ የስራ ሃላፊ በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንደሚደረግ ይገልጻል፡፡

ሆኖም ግን 2 መ/ቤቶች ዘላቂነት ባላቸውና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኛ በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባቸው ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን ሳያስፈቅዱ የቀንና የኮንትራት ሠራተኞችን በመቅጠር በበጀት ዓመቱ ብር 11,533,056.86 የደመወዝ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀንና የኮንትራት ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በቋሚ ሰራተኞች እንዲያዙ እንዲደረግ፤ ለቀንና ኮንትራት ሰራተኞች እየተከፈለ ያለው ክፍያም እንዲቆም እና ለወደፊቱም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.6 ክፍያዎች በወቅቱ ባለመከፈላቸው የወጣ የቅጣት ወጪ

ግኝት

የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩቱ አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች በብድር እና በእርዳታ ተልከው እንደመጡ የሚመለከተው የስራ ክፍል እቃዎቹን በወቅቱ ባለማንሳቱ እና አመታዊ የተሸከርካሪ ቦሎ ምርመራ በወቅቱ ባለመፈጸሙ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩሽን በባህር ዳር ከተማ ለተከራየው የመጋዘን ኪራይ በተገባ ውል መሰረት መ/ቤቱ በወቅቱ ኪራዩን ባለመክፈሉ ኪራይ እና ቅጣት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት እና በደን ልማት በጠቅላላው ድምር ብር 4,464,654.22 ለቅጣት የተከፈለ መሆኑ ታወቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ እና ቅጣት የሚዳርጉ አሰራሮች እንዲቆሙ ስራው በቀጥታ በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ላይ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ ስራቸውን በአግባቡ ባለመስራት ወይም ሀላፊነትን በተገቢው ሁኔታ ባለመወጣት መ/ቤቱ ያልተገባ ቅጣት እንዲከፍል ያደረጉ የስራ ሀላፊዎችም ሆነ ፈጻሚዎች ተለይተው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.7. ላልተጠቀመበት የቤት ኪራይ የተፈጸመ ክፍያ

ግኝት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በነሀሴ ወር 2009 ዓ.ም ለፌደራል ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች የመንግሥት በጀት ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲተገበር ባስተላለፈው መመሪያ ተ.ቁ 14. የቢሮ ኪራይን በተመለከተ፡- ባለበጀት መ/ቤቶች አዲስ ቢሮ መከራየት አይችሉም ተከራይተው ከፍተኛ ወጪ እየከፈሉ ያሉ መ/ቤቶች ወጪው የሚቀንስበት መንገድ መፈተሽ ይገባቸዋል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ መመሪያው ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ከግንቦት 16/2013 ጀምሮ ከኪራይ ቤቶች ቢሮ የተከራየ ሲሆን ቢሮው ውስጥ ሳይገባ ላልተገለገለበት የቤት ኪራይ በድምሩ ብር 6,570,664.70 ከፍሎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ላልተጠቀምበት ኪራይ የመንግስትን ገንዘብ አለአግባብ መክፈል በሕግ የሚያስጠይቅ በመሆኑ እድሳቱ በአጭር ጊዜ ተከናውኖ የቤት ኪራይ አገልግሎቱን ማግኘት እንዳለበት አሳስብን ይህን ስራ መከታተል ያለበት የስራ ሃላፊ ክትትል ባለማድረጉ ምክንያት መ/ቤቱ ላጣው ጥቅም ተጠያቂ መደረግ እንዳለበት በተጨማሪም በአስቸኳይ ቢሮው አገልግሎት መስጠት የሚችልበትን መንገድ መፈለግ አለያም ውሉን ማቋረጥ እንደሚገባ በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

2.8 በብልጫ የተከፈለ

ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ለውሎ አበል ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች በ10 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,418,987.04 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በብልጫ የተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ ክፍያዎች በጥንቃቄ እንዲፈጸሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.9 ከውል ስምምነት ውጪ የተፈጸመ ክፍያ

ግኝት

የማዕድንና ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 352,000.00 የኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን ብር 651,393.07 በድምሩ ብር 1,003,393.07 የተለያዩ እቃ እና የአገልግሎት ግዥ (ጥገና፣ ማስታወቂያ) ሲፈጽም ከድርጅቶቹ (አቅራቢዎች) ጋር ቀድሞ ውል ያልፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ግዢው በእቅድና በጥናት መከናወን ይኖርበታል፡፡ በውሉ መሰረት ክፍያ ሊፈጽም የሚገባ ሲሆን ተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎች ላይ ስምምነት የሚደረግ ከሆነ የውል ማስተካከያ በማድረግ እንዲሰራና ክፍያውም እንዲስተካከል መደረግ ይገባል፡፡

2.9.1 <u>የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች</u>

<u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁምየገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣውን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው እና

ከታህሳስ 12ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በሶስት መ/ቤቶች ጨረታ ሳይወጣ በብር 25,363,308.52 በ3 መ/ቤቶች ማወዳደርያ ሳይሰበሰብ ብር 356,882.56 የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
- በሁለት መ/ቤቶች መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ ብር 88,684,772.41 ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
- በአራት መ/ቤቶች ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በዋጋ ማወዳደሪያ ብር 4,390,794.75 ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- በአስር መ/ቤቶች ሌሎች የግዢ ሂደቶችን ያልተከተሉ ግዢዎች ብር 38,642,498.50 መኖሩ፡ በድምሩ በብር **157,438,256.74** የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ግዥዎች ተፈጽመው ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 5/25 ቀርቧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- መ/ቤቶቹ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲፈጽሙ፤
- በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት በማድረግ እንዲሁም በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን

ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ከተሳተፉት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ያቀረበው ዋጋ ጋር ተመሳክሮ ዋጋው የተጋነነ መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ግዥውን መፈጸም እንዳለባቸው፤

- የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት በመሆኑ አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እድል እንዲኖራቸው በዙር ሁሉም ሊሳተፉ የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበትና የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

2.10 <u>በናሙናው መሰረት ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ገቢ የሆነ ግዢ</u>

<u>**ግኝት**</u>

በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 31,345,877.42 በናሙናው መሰረት ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ በጥራት ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ተረጋጧል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ**</u>

መ/ቤቶቹ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥ ሲፈጽሙ የሚፈለገዉ ዕቃ ወይም አገልግሎት በሚፈለገው /በተጠየቀው የጥራት ደረጃ መሰረት የቀረበ መሆኑ በሚመለከታቸው የኮሜቴ አባላት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ማረጋገጫውም በጽሁፍ እንዲቀርብ ማድረግ ይገባል፡፡

2.11 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት

ግኝት

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ ከሚገባቸው ጥንቃቄዎች ውስጥ አንዱ ዕቃው ወደ መስሪያ ቤቱ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡን ማረጋገጥ መሆኑን ያብራራል፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት እና ህብረተሰብ ጤና አገልግሎት በዕርዳታ ከለጋሽ ሀገራት ለተገኙ ተሽከርካሪዎች፣ የህክምና ዕቃዎችና መድሀኒቶች ወደ ሀገር ሲገቡ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የቀረጥና ታክስ በድምር ብር 58,653,155.12 የተከፈለ ሲሆን ንብረቶቹ ገቢ ስለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በንብረት ገቢ ደረሰኝ ጥራዙ ላይ የሚገኘው ማስረጃ ከክፍያ ማስረጃ ጋር እንዲያያዝ ሊደረግ ስለሚገባ የሚመለከተው የስራ ክፍል ሰራተኛ የክፍያ ሂሳብ ሲወራረድ ንብረቱ ገቢ የተደረገበት በጥራዙ ላይ በሚገኘው ማስረጃ መሰረት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

2.12 ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተመዘገበ ወጪ

ግኝት

በኢትዮጲያ ጂኦሎጂካል ኢኒስቲትዩት ብር 128,340.95 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በዕቅድ ለተያዙ ስራዎች ማከናወኛ ከተፈቀደው በጀት ያለፈውን በጀት ዓመት ክፍያውን መፈጸም ተቋሙ የበጀት ህጉን ተከትሎ አለመስራቱን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት አሳስበናል፡፡

2.13 በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ

ግኝት

የገንዘብ ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደብ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ ብር 129,731,502.40 የወጪ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያሃሳብ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ማንኛውም ሂሳብ በትክክለኛ የሂሳብ መደብ (ኮድ) መመዝገቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.14 በአንድ የበጀት ዓመት ጥቃቅን ግዥዎች በቀጥታ መግዛት ከሚገባው ጣሪያ በላይ ግዥ ተፈፅሞ ስለመገኘቱ

ግኝት

በቀን 25/01/2014 በቁጥር ገ/ኢ/1/53/86 ተሻሽሎ በወጣው የመንግስት ግዥ አፈጻፀምና ንብረት አወጋገድ የግዥ የገንዘብ ጣሪያ መሰረት ጥቃቅን ግዥዎች የመንግስት መ/ቤት በግዥ እቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር አስር ሺ (10,000.00) ያልበለጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ ቀጥታ ግዥዎች ከማንኛውም ሻጭ ድርጅት መግዛት እንደሚችሉ ሆኖም ግን በዚህ አይነት የሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች በድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር መቶ አምሳ ሺ ብር (150,000.00) መብለጥ እንደሌለበት በሚገልጸው መሰረት በሚኒስቴሩ በበጀት ዓመቱ መመሪያው ካስቀመጠው ጣሪያ በላይ ጥቃቅን ግዥዎች ያልተገዙ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በሁለት መ/ቤቶች በመመሪያው መሰረት መከፈል ካለበት በድምሩ ብር 150,000.00 በላይ ብር 5,014,955.41 በአንድ በጀት ዓመት በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል ፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የግዥ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ጥቃቅን ግዥ እንዳይፈጸም እቅድ በማዘጋጀት የመመሪያውን የገንዘብ ጣሪያ እና እቅዱን መሰረት በማድረግ ግዥዎች እንዲፈጸሙ አስፈላጊ ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.16 ከመመሪያ ውጭ በግንቦት እና በሰኔ ወር የተፈጸመ ግዥ

ግኝት

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በደብዳቤ ቁጥር መግ/ባ/971/11/4 በቀን 17/8/2014 በጻፈው ደብዳቤ ግዥዎችን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ጊዜያት ውስጥ በጥድፊያ መፈጸም የመንግስትን በጀት ለብክነት ሊያጋልጥ የሚችል አሰራር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከሚያዝያ 30 ቀን 2014 በኋላ ባሉት በቀሩት ሁለት ወራቶች ውስጥ ግዥ መፈጸም እንደሌለበት በመንግስት በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን ከሚያዝያ 30/2014 ዓ.ም ጀምሮ የሚቀርቡ የልዩ ፍቃድ ጥያቄዎችን የማያስተናግድ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

ይሁን እንጂ የጤና ሚ/ር በድምሩ ብር 9,122,903.31 ክፍያ የፈጸመ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የመንግስት በጀት ወጪ ሊደረግ የሚገባው ለታቀደለት ዓላማ ብቻ መዋል እንዲችል ማንኛውም ግዥ በዕቅድ ተይዞ ግዥው በወቅቱ ተፈጽሞ ለተፈለገው ዓላማ በተፈለገው ጊዜ ውስጥ መድረሱን የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ሥራ አመራር ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

2.17 ለመ/ቤቱ ላልሆኑ ተሽከርካሪዎች አላግባብ የኢንሹራንስ እና የነዳጅ የተከፈለ

ግኝት

በየዓመቱ ተሽከርካሪዎች በስራ ላይ ስለመሆናቸው እና በመ/ቤቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ለይቶ 3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ሽፋን ኢንዲያገኙ ስለማድረጋቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደርግ፡-

በውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ በህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በድምሩ ብር 1,204,278.95 ከቀረቡልን በመ/ቤቶቹ የመኪና ዝርዝር ውስጥ ላልተካተቱ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ የተቀዳላቸውና የኢንሹራንስ አገልግሎት የተከፈለላችው መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ መቅዳት/የኢንሹራንስ ክፍያ መፈጸም ተገቢነት የሌለው አሰራር በመሆኑ ለወደፊቱ ሊስተካከልና ሊታረም ይገባል፡፡ የጽ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎችም ለተሽከርካሪዎች የሚውለው የነዳጅ ወጪ ከውጤት ጋር በተገናዘበ መልኩ ስለሚሰራጩበትና አገልግሎቱ ስለሚሰጥበት መንገድ ክትትል ሊያደርጉ እና ዝርዝር የውስጥ አሰራርና የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

3.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 216,790,186.58 ውዝፍ የተከፋይ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ ለባለመብቶች አለመክፈል ተጠያቂነትን ሊያስከትል እንደሚችል ጠቁመን ውዝፍ ተከፋይ ሂሳቦች እንዲወራረዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 <u>የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች</u>

3.2.1 <u>ግኝት፤ መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) የሚታይ ተከፋይ ሂሳብ</u>

የገቢና የወጪ ሂሳቦች የሚያዙበትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ: በሁለት መ/ቤቶች ብር 1,049,844.41 መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው እንዲረጋገጥ ክትትል እና ቁጥጥር እንዲደረግ ለተፈጠረው የሂሳብ ምዝገባ ስህተት ተገቢው ማስተካካያ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

3.3 ባለመብቱ ማንና ለማን እንደሚከፈል ያልታወቀ

ግኝት

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ ሀ ‹‹ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት››ይገልጻል ፡፡ ሆኖም በ5 መ/ቤቶች 36,962,641.58 መቼ እንደተመዘገበ እና ለማን እንደሚከፈል ማስረጃ ባለመቅረቡ የተከፋይ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መነሻ ሰነድ ያልቀረበለት ተከፋይ ሂሳብ ሊጣራና ተገቢው የሰነድ ማስረጃ ሊቀርብለት ለሚመለከተው አካል ሊከፈል ይገባል፡፡

4 በጀት

4.1 የበጀት አጠቃቀም

ግኝት

ኦዲት በተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2014 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን ከመደበኛ በጀት ብር 19,355,855.11 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ ሲሆን ከመደበኛ በጀት 1,543,704,842..71 ከካፒታል በጀት ብር 1,860,574,331.51 ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያሃሳብ</u>

መ/ቤቶቹ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ፤የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸውም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5 የዕቃና ንብረት አስተዳደር

5.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት

<u>ግኝት</u>

የዩኒቨርሲቲዎች የንብረት አያያዝና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተመለከቱት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	• የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር • የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት • የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት • ማዕድን ሚኒስቴር	
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	• የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን • የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት	
<u>ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ</u>	• የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት • የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን • የኢትዬጵያ ግብርና ባለስልጣን • ማዕድን ሚኒስቴር • የአቤት ሆስፒታል	
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ መቀመጣቸው፣	• የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት • የኢትዮጰያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት • ታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት • ውኃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	• የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር • የኢትዮጵያ ደን ልማት	

የግኝቶች መግለጫ	**መ/ቤቶች**	**ቅ/ጽ/ቤቶች**
መ/ቤቶች	• የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት • የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት • የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን • የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት • የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን • የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት • አማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል • የኢትዮጵያ የደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት • የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤ	
ከመ/ቤቱ ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች(ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ	• ኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን • የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት • የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን • የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት • የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን • ውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር • ታላቁ ህዳሴ ማስተባበሪያ ፕሮጄክት ጽ/ቤት • የኢትዮጰያ ውኃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት • ጤና ሚኒስቴር • ግብርና ሚኒስቴር	
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	• የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት • የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር • የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት • የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን • የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት • አማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል • የኢትዮጵያ የደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት • የእንስሳ ጤና ኢንስቲትዩት • ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆፒታል • የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልገሎት • ታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት • ቅዱስ ጴጥሮሰ እስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል • የኢትዮጰያ ውኃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
	• የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት • የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር • ማዕድን ሚኒስቴር • ጤና ሚኒስቴር • የወራቤ ሆስፒታል	
ሊብሬ (የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር) ያልቀረበላቸው	• ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆፒታል • ማዕድን ሚኒስቴር • የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	የኢትዮጵያ ደን ልማት	
	የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት	
	የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን	
	የኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት	
	የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን	
	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	
	ውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር	
	አማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	
	የኢትዮጵያ የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት	
	የእንስሳ ጤና ኢንስቲትዩት	
	ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል	
	የኢትዮጰያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት	
	የኢትዮጰያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን	
	የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የወራቤ ሆስፒታል	
	አቤት ሆስፒታል	

5.1.1 የማሻሻያሀሳብ

ዕቃዎች በአግባቡ እንዲመዘገቡና በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውሉ፤ በግምጃ ቤት ውስጥ በአግባቡ እንዲጠበቁ፤ የተበላሹ ዕቃዎች በወቅቱ እንዲጠገኑና መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6 የክትትል ኦዲት

6.1 ግኝት፤ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች

ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ20 መ/ቤቶች ለመንግስት ካዝና ተመላሽ መደረግ ያለበት ብር 54,788,983.40 ተመላሽ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡

6.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የተጠቀሰው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

3.6 የንግድ እና አስተዳደር መ/ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

1.1. የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			ድምር
			መደበኛ	ካፒታል	የውስጥ ገቢ	
1	ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	09/02/16	85,116,907,737.42	200,000,000.00		85,316,907,737.42
2	ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	08/12/16	4,447,145,650.60	200,099,011.52	61,258,507.00	4,708,503,169.12
3	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን	07/05/16	1,227,325,031.15	762,174,639.48		1,989,499,670.63
4	ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	11/01/16	247,820,845.10			247,820,845.10
5	ንግድና ቀጣናዊ	21/02/16	372,831,112.25	800,000,000.00		1,172,831,112.25
6	የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	05/02/16	552,045,475.41	37,445,833.34		589,491,308.75
7	የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለሥልጣን	03/03/16	13,915,033.00	3,112,000.00		17,027,033.00
8	ባህልና ስፖርት	07/01/16	274,922,060.93	448,483,000		723,405,060.93
9	ጠቅላይ ፍ/ቤት	12/11/15	189,308,613.00	276,258,667.00		465,567,280.00

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			ድምር
			መደበኛ	ካፒታል	የውስጥ ገቢ	
10	የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት	27/05/16	331,662,966.87	10,000,000.00		341,662,966.87
11	ከፍተኛ ፍ/ቤት	22/12/15	314,898,163			314,898,163.00
12	የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት	25/12/16	21,514,372.48			21,514,372.48
13	የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት	22/01/16	36,157,743.99			36,157,743.99
14	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	26/02/16	1,503,764.42	9,200,000.00		10,703,764.42
15	የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት	12/12/16			199,835,439.85	199,835,439.85
16	ፍትህ ሚኒስቴር	15/02/16	690,582,183.00	433,188,998.39		1,123,771,181.39
17	መንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት	05/03/16	101,697,105.00			101,697,105.00
18	የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን	28/01/16	68,289,220.00			68,289,220.00
19	ፌዴሬሽን ምክር ቤት	08/01/16	270,420,633.93	153,075,453.93		423,496,087.86
20	የኢትዮጵያ ቤተ መዘግብትና ቤተመጻህፍት	18/12/15	237,299,025.00	161,140,000.00		398,439,025.00
21	የዲያስፖራ ኤጀንሲ	28/01/16	109,047,870.00	-----		109,047,870.00
22	የህገ መንግሥትና ፌዴራሊዝም አስተዳደር	-----	-------	-------	--------	

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			ድምር
			መደበኛ	ካፒታል	የውስጥ ገቢ	
23	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር	25/06/16	65,201,944.76	----	----	65,201,944.76
24	የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት	01/13/15	20,893,631.00	16,740,200.00		37,633,831.00
25	የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት	08/01/16	32,250,360.00			32,250,360.00
26	የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን	15/12/15	30,414,884.00			30,414,884.00
27	የፕሪዘዳንት ጽህፈት ቤት	09/02/16	44,687,866.36			44,687,866.36
28	የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ	29/01/16	184,328,394.94			184,328,394.94
29	የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት	13/03/16	25,729,156.00			25,729,156.00
30	የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት	10/03/16	88,452,625.00			88,452,625.00
31	የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን	19/06/16	72,614,552.00			72,614,552.00
32	የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት	08/12/15	57,443,875.35			57,443,875.35
33	የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ	10/12/15	19,277,488.00			19,277,488.00

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			ድምር
			መደበኛ	ካፒታል	የውስጥ ገቢ	
34	የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት	27/02/16	149,126,061.58	27,734,918.75		176,860,980.33
	ጠቅላላ ድምር		95,415,715,445.54	3,538,652,722.41	261,093,946.85	99,215,462,114.80

1.2 በ2014 በጀት ዓመት ኦዲት ለተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

1.2.1 ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት /Adverse opinion/ የተሰጣቸው መ/ቤቶች

1. የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት
2. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን
3. የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
4. የፕሬዝደንት ጽ/ቤት

1.2.2 የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለበት (Disclaimer Opinions)

- የሀገር መከላከያ ሚ/ር

1.2.3 ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሂሣባቸው አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) የተሰጣቸው

1	ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
2	ማሪታይም ባለስልጣን
3	የኢትዮጲያ ዲያስፖራ አገልግሎት
4	የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና መጻህፍት አገልግሎት
5	የፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
6	የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት
7	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር
8	የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

9	የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን
10	የኢትዮጵያ ሥነ ልክ ኢንስቲትዩት
11	የኢትዮጲያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት
12	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
13	ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር
14	ፍትህ ሚኒስቴር
15	የፌዴራል የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት
16	የኢትዮጵያ ሰፖርት አካዳሚ
17	የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
18	የኢትዮጵያ ፀረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን

ነቀፌታ የሌለበት ኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች (Clean Opinion)

1	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
2	የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
3	የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት
4	የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን
5	የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት
6	የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት
7	የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት
8	የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት
9	የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት
10	የኢትዮጲያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት

1.3 በተተለያየ ምክንያት ኦዲታቸው ያልተከናወነ

1. የህገ መንግሥትና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል

<u>ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች</u>

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል (መ) ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባው እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

በ28 መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

• ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት የቆየ፣	ብር	262,087,959.20፤
• ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሆነው፣	ብር	97,415,163.98፤
• ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት	ብር	39,562,669.31፤
• ከአስር ዓመት በላይ የሆናቸው	ብር	2,734,631.17፤
• በእድሜ ቆይታ ያልተተነተነ	ብር	6,891,098.94
በድምሩ	ብር	194,611,029.54

በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ተሰበሳቢ ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት ተገልጿል፡፡

2.2 <u>ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 24,564,721.95 ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በተሰብሳቢ ተይዞ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብለት እና እንዲወራረድ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

3. **የገቢ ሂሣብ**

ያልተሰበሰበ ገቢ

3.1 ገቢ ያልተደረገ የጉዳት ካሳ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር ብር 39,716.10 አቅራቢዎች በውላቸው መሰረት ዕቃዎችን በወቅቱ ባለማቅረባቸው ላዘገዩባቸው ቀናት ገቢ መደረግ የሚገባው የጉዳት ካሳ ሳይሰበሰብ መገኘቱ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ገቢ መደረግ የሚገባው የጉዳት ካሣ ገቢ መደረግ ይገባዋል፡፡ እቃዎች ገቢ ሆነው ለአገልግሎት ለማዋል እንዲቻል ተገቢው እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

3.2 **ገቢ ያልተደረገ የሕክምና መዋጮ**

በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት ብር 7103.04 ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ደመወዝ ተቀናሽ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ገቢ መደረግ የሚገባው የሕክምና መዋጮ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ደመወዝ ተቀናሽ ተደርጎ ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.3 **ገቢ ያልተደረገ የሥራ ግብር**

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በድምሩ ብር 31,299,446.06 ከሎካል ሰራተኞች ደመወዝ ያልተቀነሰ እና ለሚመለከተው አካል ገቢ ያልተደረገ የሥራ ግብር መገኘቱ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ገቢ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ደመወዝ ተቀናሽ ተደርጉ ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 2,232,043.78 የትምህርት ዕድል አግኝተው ወደ ተለያዩ አገራት ለሄዱ ሰራተኞች ለደመወዝ፣ ለትምህርት ክፍያ፣ ለመጓጓዣ፣ ለፓስፖርት እና ለሌሎች ተያያዥ ወጪዎች የተከፈለ ቢሆንም ሰራተኞቹ በውላቸው መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በማዕከሉ የተሸፈነላቸውን ወጪ ተመላሽ አለማድረጋቸው ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቱ ከሰራተኛው ጋር በፈጸመው ውል አንቀጽ 3.4.7 መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡

የተለያዩ የገቢ አያያዝና አመዘጋገብ ችግር የሚታይባቸው መ/ቤቶች

3.5 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ወይም ያልቀረበለት የገቢ ሂሳብ

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 1,708,998.00 የገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ተይዞ መገኘቱ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ገቢ ለመደረጉ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3.6 የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ

በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 47,662,814.70 ገቢ የተደረገ ሲሆን፣ የዋጋ ተመን ያልቀረበለት በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለእያንዳንዱ የገቢ ምንጭ የተፈቀደው የዋጋ ተመን እንዲቀርብ እና ገቢው በተመኑ መሰረት መሰብሰቡ እንዲረጋገጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.7 ገንዘብ ለመሰብሰብ ውክልና ባልተሰጣቸው ሠራተኞች የተሰበሰበ ገቢ

በነዳጅ ኢነርጂ ባለስልጣን ብር 103,222.19 ገንዘብ የመሰብሰብ ውክልና እና ስልጣን ባልተሰጣቸው ሰራተኞች ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡

3.8 የውል ስምምነት ያልቀረበለት ክፍያ

በነዳጅ ኢነርጂ ባለስልጣን ብር 219620.76 የውል ስምምነት ያልቀረበለት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

በ14 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **7,566,866.08** የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ማስረጃ ላልቀረበላቸው ወጪዎች ማስረጃ እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.2 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ የወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **17,813,342.28** ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ማስረጃ ላልቀረበላቸው ወጪዎች ማስረጃ እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.3 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች

በ5 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **18,505,848.39** በሚመለከተው አካል የፀደቀ የክፍያ መመሪያና ተመን ሳይኖር አለአግባብ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በሚመለከተው አካል የክፍያ ተመን እንዲፀድቅ በማድረግ ክፍያ ሊፈፀም ይገባል፡፡

4.4 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች

በ8 መ/ቤቶች ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ የተፈፀመ በመሆኑ በድምሩ ብር 4,597,329.21 ወጪ መደረጉ ታውቋል፡፡-

የማሻሻያ ሀሳብ

መመሪያን ያልተከተሉ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ያደረጉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ክፍያዎች በመንግስት የአከፋፈል መመሪያዎች እና ደንቦች መሠረት እንዲፈፀሙ ሊደረግ ይገባል፡፡

4.5 ከመመሪያ ውጪ የተፈጸሙ ክፍያዎች

በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 279,915.90 መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎች በመንግስት የአከፋፈል መመሪያዎች መሠረት እንዲፈፀሙ ሊደረግ ይገባል፡፡

4.6 ለኦዲት ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በድምሩ ብር 1,531,711,064.94 ሰነዶች ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.7 በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ (አባሪ 5/4)

በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 233,758.05 ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች አለአግባብ ደመወዝ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

4.8 ግብር እና ሌሎች ክፍያዎች በወቅቱ ባለመከፈላቸው አለአግባብ ለመቀጫ እና ወለድ ወጪ የሆነ

በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,799,497.77 የመንግስት ግብር በወቅቱ ገቢ ባለመደረጉ አለአግባብ ለተከፈለ ቅጣት እና ወለድ ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መ/ቤቶች የሚፈለግባቸውን ክፍያ በወቅቱ ባለመክፈላቸው ለቅጣት ክፍያ በመዳረጋቸው የሚመለከታቸው ሠራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በውላቸው መሠረት በወቅቱ እንዲከፈሉ በማድረግ የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዳይደረግ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

4.9 **የስራ ዝርዝር መግለጫ (Bill of quantity) ሳይቀርብ ወጪ የሆነ**

በውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት ብር 7,300,000.02 የስራ ዝርዝር መግለጫ (Bill of quantity) ሳይቀርብ ለቢሮ እድሳት ወጪ የሆነ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለተሰራ ስራ የተፈፀመ ክፍያ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የስራ ዝርዝር መግለጫ /Bill of quantity/ ለኦዲቱ ሊቀርብ ይገባል፡፡

4.10 **በብልጫ የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎች**

በ7 መ/ቤቶች ለተለያዩ ለውሎ አበል፣ ለደመወዝ፣ ለዕቃና ለአገልግሎት ግዥዎች በድምሩ ብር 4,602,019.23 ያለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

4.11 **የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች**

በ14 መ/ቤቶች

• ያለጨረታ በቀጥታ የተገዛ	ብር	29,488,547.80፣
• መስፈርቱን ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ	ብር	8,205,807.10፣
• በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ	ብር	17,115,052.69፣
• የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ	ብር	1,957,836.82፣
• ሌሎች የግዥ ሂደትን ያልተከተሉ	ብር	1,463,496.89፣
በድምሩ	ብር	58,230,741.30

የግዥ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ** 5/16)

የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.12 በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ የግዥ ክፍያዎች

በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,325,868.90 የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሠረት ገቢ መደረጋቸው ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.13 ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች

በ3 መ/ቤቶች የተገዙ ዕቃዎች ገቢ ለመደረጋቸው የዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ሳይቀርብ በድምሩ ብር 521,498.94 ክፍያ ተፈፅሞ ሂሳቡ በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ በማስረጃነት ሊቀርብ ይገባል፡፡

4.14 በትክክል ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ

በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 7,815,207.57 በማነስ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ በኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት ብር 19,115.31 ያልተመዘገበ ወጪ ተገኝቷል፡፡

4.15 ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተመዘገበ ወጪ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በ5 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 6,248,304.16 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎች በጀት በተፈቀደበት በጀት ዓመት ውስጥ እንዲፈፀሙ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.16 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

በ15 መ/ቤቶች ብር 14,190,253.91 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡ (አባሪ 5/30)

የማሻሻያ ሀሳብ

የወጪ ሂሳቦች በወጪ ከመመዝገባቸው በፊት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመያዛቸው መረጋገጥ እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

በወጪ ሂሳብ ላይ የታዩ ዋና ዋና የአሰራር ድክመቶች

4.17 አግባብ ባለው ባለሥልጣንና ቦርድ ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 430,560.00 በሚመለከተው ባለሥልጣንና ቦርድ ሳይፈቀድ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎች በሚመለከተው ባለሥልጣንና ቦርድ እንዲፈቀዱ በማድረግ ሊከናወኑ ይገባል፡፡

4.18 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

በፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ብር 625,632.90 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

4.19 መነሻ ሰነድ የሌለው የወጪ ሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ

በፕሬዝደንት ጽ/ቤት የመጀመሪያ ምዝገባ የተከናወነበት የሂሳብ ሰነድ ሳይቀርብ ለብር 2,528,831.74 የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ ተከናውኖ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የመነሻ ምዝገባ የተከናወነባቸውን ሰነዶች በመጥቀስ እና ምዝገባው የተሰረዘበትን ምክንያት በመግለፅ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ እንዲከናወን መደረግ ይኖርበታል፡፡

የሽያጭ መመዝገቢያ ደረሰኝ ያልቀረበለት ክፍያ

በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 6,197,739.63 ክፍያ ለመፈፀሙ ተገቢው የሽያጭ መመዝገቢያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ

የተከፋይ ሂሣቦች በወቅቱ ለባለመብቱ የሚከፈሉ መሆኑን እና የተከፋይ ሂሣቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

5.1 ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ

በ22 መ/ቤቶች የቆይታ ግዜያቸው

• ከአንድ ወር እስከ አንድ አመት	ብር	60,163,163.35፤
• ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት	ብር	39,508,877.65፤
• ከ 5 ዓመት በላይ እስከ 10 ዓመት	ብር	971,674.82፤
• ከ10 ዓመት በላይ	ብር	2,341,827.20፤
• የቆይታ ጊዜው ያልተተነተነ	ብር	1,062,360.45፤
በድምሩ	ብር	104,047,903.47

የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ሳይወራረድ መገኘቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቶቹ በወቅቱ እንዲከፈሉ የሚመለከተው አካል ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች

5.2 በተከፋይ ሂሳብ ያልተካተተ የተከፋይ ሂሳብ

በሀገር መከላከያ ሚ/ር በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ብር 294,269.00 ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

6. የበጀት አጠቃቀም

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ

በተለያዩ የወጪ አርእስቶች ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ በመደረጉ፣ በ3 መ/ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር 28,603,101.15 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በጥናት ላይ የተመሰረተ የበጀት ዕቅድ በማዘጋጀት የተፈቀደለትን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲያውል እና አስቀድሞ የተፈቀደ በጀት አለመኖሩ ሲረጋገጥ በዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ በቂ በጀት እንዲኖር በማድረግ ክፍያ እንዲፈፀም መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

በተለያዩ የወጪ አርእስቶች የተፈቀደው በጀት ስራ ላይ ያልዋለ በመሆኑ፤
ከመደበኛ በጀት በ27 መ/ቤቶች ብር 226,212,189.36፤

ከካፒታል በጀት በ13 መ/ቤቶች ብር 557,072,233.86

በድምሩ ብር 783,284,423.22 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የተፈቀደው በጀት በመመሪያው መሰረት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል የሥራ አመራሩ ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

7. ንብረት

የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 6/1/ለ እና 11/1 የቋሚ ንብረት አስተዳደር በተመለከተ እንዲሁም የመመሪያው አንቀጽ 16 የስቶክ

አስተዳደርን በተመለከተ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት በታዘዘው መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

7.1 **<u>ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ፤</u>**

በ4 መ/ቤቶች ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑን፤

7.2 **<u>በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች፣</u>**

በ2 መ/ቤቶች በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) የማይዘጋጅ መሆኑን፤

7.3 **<u>የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ያላደረጉ መ/ቤቶች፤</u>**

በ7 መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑን፤

7.4 **<u>ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ፣</u>**

በሀገር መከላከያ ሚ/ር የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ቢደረግም በቆጠራ ያልተካተቱ ንብረቶች መኖራቸውን፡፡

7.5 **<u>ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም በቆጠራዉ ያልተካተቱ ንብረቶች የተገኘበት መ/ቤት፤</u>**

የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና መጻህፍት አገልግሎት፤

7.6 **<u>ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ፤</u>**

በ2 መ/ቤቶች ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያልተቋቋመ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑን፤

7.7 **<u>ተገቢው የንብረት ርክክብ ባለመደረጉ የንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣</u>**

በ2 መ/ቤቶች በአግባቡ የንብረት ርክክብ ባለመደረጉ የንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

7.8 ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች፣

በ7 መ/ቤቶች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የተለያየ ዓይነት ንብረቶች ያለአገልግሎት የተቀመጡ መኖራቸው፣

7.9 አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው፣

በ11 መ/ቤቶች የተለያዩ ዓይነት ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙ

7.10 ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች አዲስ ተገዝተው ከሚገቡ ንብረቶች ተለይተው የማይቀመጡባቸው መ/ቤቶች፣

በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በንብረት ክፍል (እስቶር) ውስጥ ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች አዲስ ተገዝተው ከሚገቡ ንብረቶች ተለይተው የማይቀመጡ መሆኑን፤

7.11 ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰው ተደርበው የሚከናወኑባቸው፣

በ3 መ/ቤቶች ተያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰው ተደርበው እንዲሰሩ መደረጉን፤

ሌሎች የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅ ክፍተቶች፤

7.12 የቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ መቀመጣቸው፣

በፍትህ ሚኒስቴር የቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለው መቀመጣቸው፣

7.13 በ3 መ/ቤቶች መ/ቤታቸውን የለቀቁ ሰራተኞች(ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ በእያንዳንዳቸው መ/ቤቶች 2 ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች እንዲመለሱ አለመደረጉን፤

7.14 ቋሚ ንብረት በቋሚ መዝገብ ላይ ያልመዘገቡ እና በቋሚ ንብረት በቆጠራ ሪፖርት ያልተካተቱ መ/ቤቶች፣

በማሪታይም ባለስልጣን በንብረት ቆጠራ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ብር 354,219.99 ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

7.15 የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች፣

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

7.16 <u>አገልግሎት የማይሰጡ እና የሚያገለግሉ ንብረቶች በአንድ ላይ የተቀመጡባቸው መ/ቤቶች፤</u>

በ3 መ/ቤቶች ንብረቶች ሳይለ በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑን፤

7.17 ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች የተገኙባቸው መ/ቤቶች

በ2 መ/ቤቶች በመመሪያው መሰረት ተያዥ ወይም ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች የተገኙባቸው መሆኑን፤

7.18 <u>በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎች ዋጋ ያልተመኑ መሥሪያ ቤቶች፤</u>

የፌዴራል የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት፤

7.19 <u>ለኦዲት ያልቀረበ ፋይል፣</u>

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

የዳኞች፣ የሬጅስተራርና ረዳት ዳኞች የግል ማህደር

7.20 <u>የቤተ-መጽሐፍት አጠቃቀምና አያያዝ ዋናዋና ችግሮች፣</u>

የመጽሃፍት ውሰት ጊዜያቸውን ጠብቀው ተመላሽ የማያደርጉ መ/ቤቶችን በተመለከተ

የፌዴራል የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት 24 መጽሐፍት ተመላሽ አለመደረጋቸው፤

<u>የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም</u>

7.21 <u>ሊብሬ ያልቀረበላቸው፣</u>

በ2 መ/ቤቶች 2 መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ወይም ሊብሬ የሌላቸው መሆኑን፤

7.22 <u>ያለአገልግሎት ወይም በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው መ/ቤቶች</u>

በ7 መ/ቤቶች 40 መኪናዎች እና 5 ሞተር ሳይክሎች የሚገኙ መሆኑን፤ (አባሪ 31)

7.23 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ፤</u>

በ6 መ/ቤቶች የሚገኙ 11 መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ስም የሚገኝ መሆኑን፤

7.24 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው ሞተር መካከል ልዩነት ያለ መሆኑ፤

የፌዴራል የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት 1 መኪና በባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው ሞተር መካከል ልዩነት ያለ መሆኑ፤

7.25 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት፤

በ4 መ/ቤቶች የሚገኙ 10 መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት ያለው ሆኖ መገኘቱ፤

7.26 የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው (ጌጃቸው) የማይሰራ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው መ/ቤቶች፤

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው (ጌጃቸው) የማይሰራ 3 ተሽከርካሪዎች መገኘታቸውን፤

ሌሎች የተሽከርካሪ አያያዝ እና አጠባበቅ ክፍተቶች፤

7.27 ለተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ መዝገብ ያልተዘጋጀላቸው፣

የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ለተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ መዝገብ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑን፤

7.28 በኃላፊነት ተወስዶ ተመላሽ ያልተደረገ ተሽከርካሪ የተገኘበት መ/ቤት፣

በማሪታይም ባለስልጣን 1 መኪና በመ/ቤቱ ኃላፊ ተወስዶ ለመ/ቤቱ ሳይመለስ መቅረቱን፤

7.29 ጥገና ለተደረገላቸው ተሽከርካሪዎች ተመላሽ እቃ ገቢ ያላደረጉ፣

በነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ጥገና ለተደረገላቸው የተቀየሩ መለዋወጫዎች ወደ መ/ቤቱ ግምጃ ቤት ተመላሽ የማይደረጉ መሆኑን፤

7.30 የሚወገዱ የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፤

በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፤

7.31 የውስጥ ቁጥጥር ክፍተት የታየባቸው መ/ቤቶች

- የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ተቋማዊ መዋቅር (Organizational Chart) የሌለው መሆኑን፤
- 2 መ/ቤቶች የሰነድ አያያዝ እና የምዝገባ ስርዓት ችግር የታየባቸው መሆኑን፤
- በፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በወቅቱ የማይቀርብ መሆኑን፤
- በፍትህ ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲት ክፍል በሰው ሀይል ያልተሟላ መሆኑን፤
- በ4 መ/ቤቶች **የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር ዕቅድ** /Risk Management Policy / ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

<u>**ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣ (አባሪ 9)**</u>

ተ/ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ
1	የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን	180,681.66
2	የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት	79,364.56
3	የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና መጻህፍት አገልግሎት	131,602.38
4	የፕሬዝደንት ጽ/ቤት	
5	የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት	27,577.06
6	የፌዴሬሽን ምክር ቤት ፅ/ቤት	67,085.40
7	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር	583,350.08
8	የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት	270 621.58
9	የኢትዮጲያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት	80,263.15
10	የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት	35,383.84
11	ማሪታይም ባለስልጣን	97,926.50
12	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	40,292,065.04
13	ፍትህ ሚኒስቴር	261,097.50
14	የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን	4,500.00
	ጠቅላላ ድምር	**41,842,362.82**